# ሐመር

# ''ኦሪት ወነቢያት ወወንጌል ሰበኩ በክርስቶስ''



## በውስጥ ገጾች


- ✞ ኦሪት ወነቢያት ወወንጌል ሰበኩ በክርስቶስ
- ✞ እመኚ እንጂ አትፍሪ
- ✞ ጾመ ነቢያት
- ✞ ቤተ ክርስቲያን ለአእምሮ ሕመምተኞች ያላት አስተዋጽኦ
- ✞ ዕቅበተ እምነት


ኅዳር ፳፻፲፫ ዓ.ም.

# ሐመር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣
ሥርዓት እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት
ጠብቆ የሚወጣ

ኅዳር ፳፻፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመትና
ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ዋና ክፍል
በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ
ትምህርታዊ መጽሔት




## ማውጫ


የማኅበሩ መልእክት
"በስሜም ሰላም በሉት" ፫

ዐውደ ስብከት
ጾመ ነቢያት ፬

ትምህርተ ሃይማኖት
ኦሪት ወነቢያት ወወንጌል ሰበኩ በክርስቶስ ፰

ዐቢይ ጉዳይ
ዕቅበተ እምነት (Apology) ፲፫

እናስተዋውቃችሁ
የተከዜ ምዕራፈ ቅዱሳን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት እና መድኃኔዓለም ዘአቡነ ሐዋርያ ክርስቶስ አንድነት ገዳም ፲፯

የጥያቄዎቻችሁ መልስ ፳፪

ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት
ግብረ ሰዶማዊነት ፳፰

ከዓለም ማዕዘናት
ጾመ ነቢያት በዓለም ማዕዘናት ፴፮

ኪነ ጥበብ
"እመኚ እንጂ አትፍሪ" ፴፯

የነገዋ ቤተ ክርስቲያን
ቤተ ክርስቲያን ለአእምሮ ሕመምተኞች ያላት አስተዋጽኦ ፴፯

አቡጊዳ የግእዝ ትምህርት
ቅጽል ፵፩


"ማኅበረ ቅዱሳን" እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይኽን ስያሜ አግኝቷል።


## የዝግጅት ክፍሉ

ስልክ ፲፩፩-፰-፩፪-፪፰-፬፱
ፖ.ሣ.ቁ ፰፲፲፯፰
ኢ-ሜይል magazine@eotcmk.org
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት ስልክ
፲፩፩-፩-፭፭-፫፪-፫፱
የልማት ተቋም የስርጭት ክፍል ስልክ
፲፩፩-፩-፪፫፬፭-፪፱
የማስታወቂያ ዝግጅት ክፍል ስልክ
፲፱፬፪-፫፰-፩፯-፱፩

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ
አድራሻ፡- ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ
ወረዳ ፲፭ የቤት ቁ. ፯፪፲

**ምክትል ዋና አዘጋጅ**
ዲ/ን ኅሊና በለጠ

**ከፍተኛ ሪፖርተር**
ዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

**ሌይ አውት ዲዛይነር**
ግደይ ገብሬ

**ጸሓፊ**
ገነት ታደሰ

## የማህበሩ መልእክት

# ''በስሜም ሰላም በሉት''

፪ኛ ሳሙ.፳፭፥፭

ለሰው ልጆች ህልውና እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች መካከል ሰላም ዋናው ነው፡፡ ሕይወትና ኑሮ ሊታሰብ የሚችለው ራሱ ሰላም ሲኖር ነው፡፡ ሰላም ከሌለ መምህሩ ማስተማር፣ ተማሪው መማር፣ ነጋዴው መነገድ፣ ሸማቹም መሸመት አይችልም፡፡ ሐኪሙ ማከም፣ መሐንዲሱ መገንባት የሚችለው ሰላም ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ሐኪሞ አክሞ የሚያድነው ሟችን፣ መሐንዲሱ የሚገነባውም ፈራሽን ይሆናል፡፡ ሰላም ከሌለ ገበሬው ዘርቶ ሀገር መመገብ አይችልም፤ የሃይማኖት አባቶችም ያልተማረውን ለማስተማር የተማረውንም ለማጽናት ፈተናው ይበረታባቸዋል፡፡ የሰላም ዋጋው እጅግ ውድ ነው፡፡ የትኛውም ሰው የዕለት ግብሩን ለመፈጸም በቅድሚያ ሰላም ሊኖረው ይገባዋል፡፡ ለዚህ ነው መዝሙረኛው ‹‹ከክፉ ሽሽ መልካምንም አድርግ፤ ሰላምን ሻት ተከተላትም፤›› ሲል የዘመረው፡፡ (መዝ.፴፫፥፲፬)፡፡

አብዛኛው የሀገራችን ታሪክ በጦርነት የታጀበ ነው፡፡ ብዙ ጠላቶች በየዘመናቱ እየተነሡብን የመከትነውን ያህል፡ እርስ በእርስ የተገዳደልንባቸው ታሪኮቻችንም ትንሽ የሚባሉ አይደሉም፡፡ በሁሉም ጦርነቶች ግን ወንድሞች ተገዳድለዋል፣ ሕፃናት በወላጅ እጦት ተርበው አልቀዋል፣ ወገን ተጨፍጭፏል፣ ሀገር ወድማለች፡፡ ይህ ሁሉ ክስረት በየዘመናቱ የተከሰተው እርስ በእርስ ወንድማማቾች ተጣልተው መሆኑ ደግሞ ሕመሙን የከፋ ያደርገዋል፡፡

ሰላም በጠፋባቸው በእነዚህ የታሪካችን ክፍሎች ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጉዳትም ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡ እንዲያውም የመከራዎቹ ዋናዋ ገፈት ቀማሽ እርሷ፣ አገልጋዮቿና ምእመናኗ ነበሩ፡፡ በመሆኑም የሰላምን መልካም ጣዕምና የጦርነትን መራራነት በተግባርም ጭምር ታውቀዋለች፡፡ ስለዚህም የሰላምን አስፈላጊነት በአገልግሎቷ ሁሉ ትሰብካለች፡፡ ስለ ሀገር ሰላም ዘወትር ትጸልያለች፡፡ በጸሎት ብቻም ሳይሆን ድርሻዋን በተግባር በመወጣትም ዘወትር ግንባር ቀደም ናት፡፡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በተቃጠሉባትና አገልጋይ ካህናቷና ምእመኖቿ በተሠዉበት ባለፉት ቅርብ ዓመታት እንኳን በተለያዩ ሀገር ዐቀፍ የሰላም ጉባኤያት ስለ ሰላም ሰብካለች፡፡ ልበ አምላክ ዳዊት ናባል የተባለውን የምስጉኗ የአቢግያ ባልን የማጥፋት ኀይል እያለው ‹‹በስሜም ሰላም በሉት›› ብሎ ብላቴኖቹን የላከበት ከዚህ የቤተ ክርስቲያንና የቅዱሳን ባሕርይ የተነሣ ነው፡፡

በሀገራችን እየተካሄደ ያለው ጦርነትም ቤተ ክርስቲያንንና እኛ ልጆቿን በእጅጉ የሚያሳስብ ነው፡፡ በዚህ ጦርነት ስለሚጠፉት ነፍሳትና ስለሚወድመው የሀገር ሀብት ማሰብ እጅግ ያስጨንቃል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ስለ ሰላም ሰብካለች፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በልጆቿ አማካይነት ይህ ጦርነት እንዳይመጣ በተግባርም ብዙ ደክማለች፡፡ አሁንም የበለጠ እልቂትና ውድመት ሳይከሰት ይህ ጦርነት በአጭሩ እንዲቋጭ ጸሎቷና ምኞቷ ነው፡፡ ይህንን ምኞቷንም ሁሉም አካላት እንዲጋሩላት ትፈልጋለች፡፡ የሀገራችን ዜጎች ሁሉ እንደ ገና በሰላምና በመተሳሰብ እንዲኖሩ፣ ምእመኖቿም ያለ ሥጋት ‹‹የሰላም አለቃ›› የተባለ አምላክን እንዲያመልኩ ትፈልጋለች፡፡ ለዚህም ደግሞ በየትኛውም ጽንፍ ያለ ወገን የመዝሙረኛውን ቃል በማስተዋል ‹‹በስሜም ሰላም በሉት›› እንደ ተባለ ሁሉም ‹‹ከክፉ ሽሽቶ መልካምንም አድርጎ›› ስለ ሰላም ፈጣሪውን እንዲጠይቅ፣ እርስ በራሱም ሰላም እንዲባባል ትሻለች፡፡ በኃጢአት የጎሰቆሉ ልጆቿ በንስሓ ወደ መልካሙ መንገድ ሳይመለሱ እንዳይጠፉ ዘወትር ትጸልያለች፡፡

ወቅቱ የጾም እንደ መሆኑም ካለንበት የክፉት ዘመን ያወጣን ዘንድ ሁሉም ሰው በጾም፣ በጸሎትና በልቅሶ ወደ እግዚአብሔር ሊጮህ ይገባል፡፡ ስለ ጠፉት ነፍሳት፣ ስላሉት ወገኖች፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ሀገርና በአጠቃላይ ስለ ሰላም ሁሉም በአንድነት ከጮኸ፡ እግዚአብሔር የምንዱባንን ጩኸት የሚሰማ አምላክ ነውና ወደ እኛ ይመለከታል፡፡ ‹‹ሰላምን እንደ ወንዝ፥ የአሕዛብንም ክብር እንደሚጐርፍ ፈሳሽ እመልስላታለሁ›› የሚል አምላክ ‹‹በጾምና በልቅሶ›› ወደ እርሱ ለሚመለሱ ሁሉ ፊቱን ሊመልስላቸው የታመነ ነው፡፡ እርስ በርሳችን ከመወቃቀስና ከመጠፋፋት ይልቅ ሰላምን ልንጠያየቅ፣ ወደ እርሱም በጾምና በልቅሶ ልንመለስ ይገባናል፡፡ (ኢሳ. ፷፮፡፲፪ ፣ ኢዩ.፪፡፲፪)፡፡

✞ ✞ ✞

# ጾመ ነቢያት

## ዐውደ ስብከት

ዲ/ን ዮሐንስ ጌታቸው

በኢትዮያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ሰባት የአዋጅ አጽዋማት አሉ። እነዚህን የአዋጅ አጽዋማት በተመለከተ ፍትሐ ነገሥት (ፍትሕ መንፈሳዊ) አንቀጽ ፲፭፥፭፻፷፬ ጀምሮ ተጽፏል። በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፲፭፥፭፻፷፰ "ከልደት አስቀድሞ የሚጾም ጾም ነው፡ መጀመርያው የኅዳር እኩሌታ፡ ፋሲካው፡ የልደት በዓል ነው።" ተብሎ የጾመ ነቢያት መነሻውና መድረሻው ተገልጿል። ይህ ማለት በሦስቱ ወንጌላውያን ማለትም በዘመነ ማቴዎስ፣ በዘመነ ማርቆስና በዘመነ ሉቃስ ከኅዳር ፲፭ ጀምሮ ኅዳር ፳፱ የሚፈስክ ሲሆን በዘመነ ዮሐንስ ደግሞ መነሻው ያው ከኅዳር ፲፭ ጀምሮ ይሆንና ኃዳር ፳፰ ቀን የሚፈሰክ ይሆናል ማለት ነው።

ጾመ ነቢያት በሌሎቹ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናትም ሆነ በተለምዶ ካቶሊክ እያልን በምንጠራቸው ዘንድ የታወቀ ነው። እኛ ጾመ ነቢያት የምንለውን ሌሎቹ የልደት ጾም (The Nativity Fast) በማለት ይጠሩታል። ይህ ጾም የሚጾምበት ዋና ምክንያት የክርስቶስን ልደት ለመቀበልና ነቢያት አስቀድመው ልደቱን በመመኘት የጾሙትን ጾም ለማስታወስም ነው። ይህን ጾም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የምጽዓት ጾም (The Advent Fast) በማለት ትጠራዋለች። ምክንያቱም አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም ለመወለድ መምጣቱን በማሰብ የሚጾም ነውና።

ይህ ጾም ከክርስቶስ ልደት በፊት ለ፵፬ ቀናት ያህል የሚጾምና የክርስቶስን ልደት ለመቀበል የሚደረግ ጾም ነው። ፵ው ቀናት ሊቀ ነቢያት ሙሴ በሲና ተራራ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ለመቀበል የጾመውን የሚያስታውስና ለሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ደግሞ የክርስቶስን ልደት መሠረት በማድረግ የሚጾም ነው።

በዚህ ጾም ውስጥ ከ፵ው ቀናት በተጨማሪ አራት ቀናት ተያይዘው ይጾማሉ። ሦስቱ ጾመ አብርሃም ሶርያዊ ይባላል። በግብፅ ውስጥ በሊቀ ጳጳሱ በአባ አብርሃም ዘመን አሕዛባውያን "የሰናፍጭ ቅንጣትን የሚያህል እምነት ካላችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ተነሥተህ ወደዚያ ሂድ ብትሉ ይሆንላችኋል" (ማቴ.፲፯፥፳) የሚለውን በማንሣት ክርስትናን ለመገዳደር ሲሞክሩና ሊቀ ጳጳሱንም ጠርተው ይህን ማድረግ ትችላላችሁን ብለው ጠየቁት። ሊቀ ጳጳሱም አዎን ብሎ መለሰ። ከዚያም ከምእመናኑ ጋር የሦስት ቀን ጸሎት አድርጎ በሥዕለ ቅድስት ድንግል ማርያም ፊት ተማጽኖንም ባቀረበ ጊዜ ይህን ማድረግ የሚችለው በግብፃውያን ቅዱስ ስምዖን ቆዳ ፋቂው Simon Tanner (በእኛ ትርጓሜ ስምዖን ዘአሐቲ ዐይኑ ይለዋል) ተብሎ የሚጠራው ተራራውን እንዲንቀሳቀስ አድርጎታል። ከ፵ው ቀናት በፊት ሦስት ቀናት የሚጾሙት ይህን ድንቅ ተአምር ለማዘከር ነው። አንዱ ቀን ጾመ ገሃድ ይባላል። ይህም ልደት አርብ ወይም ረቡዕ የሚውልበት ጊዜ ስላለ አባቶች ለዚህ ምትክ እንዲሆን ሲሉ እንዲጾም ወስነዋል።

> **"የሰናፍጭ ቅንጣትን የሚያህል እምነት ካላችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ተነሥተህ ወደዚያ ሂድ ብትሉ ይሆንላችኋል"**

ጾመ ነቢያት መሠረቱ የሙሴ ጾም ነው:: ሙሴ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ጹሞ በጽላት ላይ የተጻፈን የእግዚአብሔር ቃል ተቀብሏል:: (ዘፀ.፴፬÷፲፪-፲፰) ከዚያም ነቢያት የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት ተስፋ በማድረግ ጹመውታል:: አስቀድመው ነቢያት የጌታችንን የልደት ዕለት ተስፋ በማድረግ ልደቱን በጉጉት ለማየት የጾሙትን የልደት ጾም ከግብዝነት ሕይወት ራሳችንን ለይተን ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር አስገዝተን ብንጾም ነቢያት ያገኙትን በረከት እናገኛለን:: ጾመ ነቢያት ለሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ከነቢያት በጎ ምኞት ጋር መገናኛ መሥመር እና ወደ እነርሱ ትንቢት ፍጻሜ መጓጓዣ ነው:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ የተመሠረተች እንጂ፣ በሐዋርያት መሠረት ላይ ብቻ የታነጸች አይደለችም:: ጾመ ነቢያት የሐዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን ከነቢያት ጋር ያላትን አንድነት የሚገልጽ፣ የነቢያትም የሐዋርያትም ጉዞ ወደ ንጉሥ ክርስቶስ የልደት ስፍራ መሆኑን እንድንረዳ የሚያግዝ ምርኩዝ ነው::

**አስቀድመው ነቢያት የጌታችንን የልደት ዕለት ተስፋ በማድረግ ልደቱን በጉጉት ለማየት የጾሙትን የልደት ጾም ከግብዝነት ሕይወት ራሳችንን ለይተን ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር አስገዝተን ብንጾም ነቢያት ያገኙትን በረከት እናገኛለን::**

ሰባቱ የአዋጅ አጽዋማት ክርስቲያኖች የግድ ይጾሟቸው ዘንድ የታዘዙ ናቸው እንጂ በቸልታ የሚታለፉ አይደሉም:: አንዳንድ ወንድሞች የአዋጅን ጾም "የቄሶች ጾም" ብለው በራሳቸው ለራሳቸው ምክንያት አበጅተው ከጾም ሲርቁ ይታያሉ:: ጾመ ነቢያት ለኦርቶዶክሳውያን በሙሉ የታወጀ የግድ ሊጾም የሚገባው እንጂ በሰበባ ሰበብ ሊዘነጋ ፈጽሞ አይገባም:: ይህን ጾም "የቄሶች" ብሎ አለመጾም ማለት በአንድ በኩል ለጾም ያለን ውስጣዊ ፍላጎት እጅግ የደከመ መሆኑን ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ ጾም የሚገኘውን በረከት አለመረዳትም ነው:: በጥልቀት ከተመረመረ ደግሞ የሌለን ሥርዓት ሠርቶ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ጋር መጋጨትም ነው::

የሰማይና የምድር ንጉሥ ሰው ሆኖ የሚወለድበትን ቀን ለማየትና በዚያ ቀን ከሚገኘው ፍጹም ደስታ ለመሳተፍ አስቀድሞ በጾምና በጸሎት መትጋት ያስፈልጋል:: የክርስቶስን ሕማም ሳናስብ ትንሣኤው ጋር ዘልለን መሄድ እንደ ማንችለው የክርስቶስን የልደት ዕለት ለማግኘት በነቢያት ትንቢትና ጾም በር በኩል ማለፍ ግድ ይለናል:: የክርስቶስን የልደቱን በዓል ለማክበር ለበዓሉ የሚሆን ዝግጅት ማድረግ በእጅጉ አስፈላጊ ነው:: አንድ ታላቅ ወዳጅ የምንለው ሰው ወደ ቤታችን መጥቶ ያርፍ ዘንድ ካወቅን አስቀድመን ቤታችንን አስተካክለንና አሳምረን ወዳጃችንን ለማስደሰት የምንሻ አይደለንምን? ሌላው ቀርቶ የእኛን የልደት ዕለት ለማክበር እንኳን ከልደታችን ዕለት አስቀድመን የምንዘጋጅ መሆናችን ይታወቃል:: እንግዲያው ዓለማትን በእጁ የያዘ እርሱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋና ነፍስን በፍጹም ተዋሕዶ ነሥቶ ሰው ሆኖ በቤተ ልሔም የተወደበት ዕለት በመንፈሳዊው ደስታ ደስ ለመሰኘት አስቀድመን ፍጹም ጥንቃቄና ዝግጅት ልናደርግ ያስፈልገናል::

ጾመ ነቢያት ከሰባቱ የአዋጅ አጽዋማት መካከል መሆኑን የሚሰሙ አንዳንድ ተቃዋሚዎች ደግሞ የአዋጅ የሚል ጾም የለም ብለው ሲሞግቱ ይሰማል:: ይህ ሐሳባቸው ሌላው ቀርቶ ራሳቸው እናምናለን ብለው ከሚያስቡት መጽሐፍ ብቻ (Scripture alone) ከሚለው ጋር የሚጋጭ መሆኑን ቢረዱት መልካም ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ በአዋጅ የመጾምን ጉዳይ በተደጋጋሚ ዘግቦ ያስቀመጠልን ስለሆነ በእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ መወዛገብ የለብንም:: መጽሐፍ እንዲህ ይላል "… የእግዚአብሔርን ቃል በጾም ቀን በእግዚአብሔር ቤት

በሕዝቡ ጆሮ በክርታሱ አንብቡ፤ … በኢየሩሳሌም የተቀመጡ ሕዝብ ሁሉ ከይሁዳም ከተሞች ወደ ኢየሩሳሌም የመጡ ሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ለመጾም አዋጅ ነገሩ::" (ኤር. ፴፮፥፮-፱):: ነቢዩ በግልጽ "በጾም ቀን" ማለቱ የታወቁ የጾም ቀናት መኖራቸውን ያስረዳል:: ከዚህም ጋር አያይዞ "በኢየሩሳሌም የተቀመጡ ሕዝብ ሁሉ ከይሁዳም ከተሞች ወደ ኢየሩሳሌም የመጡ ሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ለመጾም አዋጅ ነገሩ::" ማለቱ ደግሞ ነገሩን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል::

ነቢዩ ኢዩኤል "ጾምን ቀድሱ፣ ምህላንም አውጁ፣ ሽማግሌዎችንና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሰብስቡ፣ ወደ እግዚአብሔርም ጩኹ" በማለት ሲገልጽ (ኢዩ. ፩፥፲፬) :: ነቢዩ ዘካርያስ ደግሞ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የአራተኛው ወር ጾም፣ የአምስተኛውም፣ የሰባተኛውም፣ የዐሥረኛውም ወር ጾም ለይሁዳ ቤት ደስታና ተድላ የሐሤትም በዓላት ይሆናል::" በማለት የበለጠ ጉዳዩን አጠንክሮ ገልጿል:: (ዘካ. ፰፥፲፱):: ነቢዩ ዘካርያስ አጽዋማትን ወይም የአጽዋማት ወቅቶችን የደስታ ጊዜያት ሲያደርጋቸው ከጾም ሕይወት ፈጽመው የራቁ ሰዎች ደግሞ በራሳቸው ስሜት ሐሳቡን ገልብጠው የጾም ወቅቶችን የኀዘንና የትካዜ ያደርጓቸዋል:: ገና ጾም ሳይገባ እንዳይገባ በር በመዝጋት ላለመጾም ጥብቅና ይቆማሉ:: ይህ በእጅጉ መኀዳት መሆኑን ልብ ብለው ያስተውሉ ዘንድ ከላይ የተገለጹትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳቦች መቀበል ግድ ይላቸዋል:: ምናልባት ከላይ የተገለጹትን የአዋጅ አጽዋማትን ሰምተው ‹‹እነዚህማ በብሉይ ኪዳን የተገለጹ እንጂ በሐዲስማ እንዲህ ያለ ሥርዓት የለም›› እንዳይሉ ቅዱስ ሉቃስ "የጦም ወራት አሁን አልፎ ስለ ነበር . . ." በማለት ገልጿል:: (ሐዋ. ፳፯፥፱) :: ይህ ሁሉ የሚያሳየው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ምን ያህል በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት የምትመራ መሆኗን ነው:: እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑንና ማንኛውም ዓይነት ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳብ ሊያነዋውጻት አለመቻሉን ምእመናን በአግባቡ ልንረዳ ይገባል::

በኀሊናችን ውስጥ ስለ ጾም መልካም ስፍራ ማዘጋጀት አለብን:: በውስጣችን ለጾም ያዘጋጀነው ቦታ ጠባብ ከሆነ እንኳን "አይ ይህ ጾም ቢጾምም ባይጾምም አይጎዳም" ልንል ቀርቶ እንዲህ ዓይነቱ ሐሳብ በውስጣችን እንዲመላለስ አንፈቅድም:: አንድ ሊቅ "ጸሎትና ጾም በሌለበት ሰው ውስጥ ሰይጣን አለ ብለን ማሰብ እንችላለንን?" ብሎ ይጠይቅና ሲመልስ "አዎ፣ አጋንንት ወደ ሰው ውስጥ ሲገቡ መግባታቸውን በገሃድ አያሳውቁም፣ መግባታቸው እንዳይታወቅባቸው ለማድረግ ሲሉ ግን ራሳቸውን ይደብቃሉ እንጂ፤ ሆኖም የገቡበትን ያን ሰው ክፉውን ነገር ሁሉ በስውር ከውስጥ ያስተምሩታል፣ መልካም የሆነውን ነገር ደግሞ ያስጠሉታል:: ያ ሰው የሚፈጽመው የጠላትን ፈቃድ ሆኖ ሳለ እርሱ ግን ራሱ እያደረገው እንደ ሆነ ያስባል:: ጠላት የሚወጣውና ሌላ መመለሻ አጋጣሚ እስኪያገኝ ድረስ ከእርሱ ርቆ የሚጠባበቀው ጸሎትና ጾምን ሲታጠቅ ብቻ ነው:: ጸሎትና ጾም ከተተው ግን እንደ ገና ተመልሰው ይመጣሉ::" በማለት የጾም ጥቅሟን ይገልጻል::

**ጾምን ቀድሱ፣ ምህላንም አውጁ፣ ሽማግሌዎችንና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሰብስቡ፣ ወደ እግዚአብሔርም ጩኹ**

ጾም ኃይሏን ባልተረዷት ሰዎች ዘንድ ተራና የማትጠቅም ተደርጋ ልትወሰድ ትችላለች፤ ነገር ግን የሰዎቹ አለማወቅ የጾምን ታላቅነት ሊያስቀር ፈጽሞ አይችልም:: ጾምን ለመረዳት ከጾም ውጭ መሆን የለብንም፤ አንድን ምግብ

ጣዕሙን በመስማት ሳይሆን የምንለየው በመቅመስ ነውና፡፡ ጾምም ባልቀመሷት ዘንድ ጣዕሟ አለመታወቁ አይደንቅም፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ጠቃሚነቷን ሳይቀበሉ ሊያጣጥሏትና ምንም ረብና ጥቅም እንደ ሌላት አድርገው ሊያሳምኑም ይሻሉ፡፡ ጥንቱን በበሽተኛ ሰው የተቀመሰ ጣፋጭ ምግብ መች ጣፍጦ ያውቅና ነው! ምግቡ ጣፋጭ ስላይደለ አይደለም፤ ቀማሹ በሽተኛ ስለ ሆነ ነው እንጂ፡፡ የውጫዊ ዐይን ዕውርነት የውስጣዊ ዐይንን ብሩህነት አይከለክልም፡፡ የውስጣዊው ዐይን ዕውርነት ግን የውጫዊውንም ዐይን የማሳወር ኃይል እንዳለው መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ጾም በሆዳሞች ዘንድ ብትጠላም፤ ሆዳምነታቸውን ዐውቀው እንደ መድኃኒት ቢጠቀሟት ኖሮ በሽታቸውን የማራቅ ኃይል እንዳላት ይረዷት ነበር፡፡

ላለመጾም ሆን ተብለው የሚቀርቡ ምክንያቶች በሙሉ ካለመጾሙ የበለጠ ጎጂዎች ናቸው፡፡ ይህ እኮ ብዙ ሰዎች የማይጾሙት ጾም ስለ ሆነ "አይካበድም" እያሉ በታወቀ ቸልተኝነት አልጋ ላይ በምግብ ፍቅር በጾም ጥላቻ ከመተኛት ጥቅሟን በማሰብ እውነተኛውን ጾም መጾም አለብን፡፡ ይህ የሽማግሌ ወይም የቄስ ጾም ነው ተብሎ ሳይገለጽ አንዳንዶች ባለመጾማቸው ከመጣባቸው የኅሊና ክስ ለማምለጥ ከሚያቀርቡት ተራ ምክንያታዊነት መላቀቅ አለብን፡፡ ኢትዮጲያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ጾምን አስመልክቶ እንዲህ ይላል "ጾም ትፌውስ ቁስለ ነፍስ ወታጸምምኵሎ ዘሥጋ ፍትወታት ትሜህሮሙ ለወራዙት ጽሙና፤ ጾም የነፍስን ቁስል ታድናለች፤ የሥጋን ፍላጎት ታስታግሣለች፤ ለወጣቶችም ጽሙናን ታስተምራቸዋለች"፡፡ እንግዲህ ይህን ያህል ለመንፈሳዊነታችን የምትጠቅመውን ጾምን አለመውደድ እንዴት ያለ ጉዳት ይሆን! እንዲሁም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ "እስመ በጾም ወበጸሎት ይሠረይ ኵሉ ኃጢአት በጾም ድኅኑ አበው ቀደምት ኤልያስ ዐርገ ውስተ ሰማያት፤ በጾምና በጸሎት ኃጢአት ሁሉ ይሠረያል፤ ቀደምት አባቶች በጾም ዳኑ፤ ኤልያስም በጾም ወደሰማያት ዐረገ" በማለት ያስረዳል፡፡ (ጾመ ድጓ) ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ጾም ምን ያህል አስፈላጊና ሁልጊዜም ልንመርጠው የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በሠራችልን ሥርዓት ውስጥ ሆነን ጾምን እጅግ በመውደድ ልንይዛትና ልንኖራት ይገባናል፡፡ በኅሊናችን ውስጥ የሚመጡትን የጾም ተቃራኒ ሐሳቦች በሙሉ እንሽሽ ዘንድ ጾምን በራሱ መሸሸጊያ አድርገን እንግባባት፡፡ በውስጣችን የሚቀጣጠሉትን እኩያት ፍትወታት እናስወግድ ዘንድ በጾም ቤት ውስጥ ገብተን እንኑር፡፡ ይህን የነቢያት ጾም በመጾም እንደ ነቢያት የክርስቶስን የልደት ዕለት ለማክበር ከልባችን ልንፈልግ፣ ልንመኝ፣ በጉጉት ልንጠብቅ ይገባናል፡፡

**ጾም የነፍስን ቁስል ታድናለች፤ የሥጋን ፍላጎት ታስታግሣለች፤ ለወጣቶችም ጽሙናን ታስተምራቸዋለች፡፡**

በአጠቃላይ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የልደትን በዓል አስመልክቶ የተናገረውን ማወቅ አስቀድሞ ተጠንቅቆና ተዘጋጅቶ መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ለመረዳት እጅግ ይጠቅማል፡፡ እንዲህ ይላል "ከበዓላት ሁሉ ይልቅ እጅግ የተከበረውና የተወደደው በዓል እየደረሰ ነው፡፡ አንድ ሰው ይህን በዓል "ርእሰ በዓላት" ብሎ ቢጠራው የተመቸ የቀና ነው፡፡ ለምን ቢሉ ወልደ እግዚአብሔር በሥጋ የተወለደበት ዕፁብ ድንቅ በዓል ነውና፡፡" በማለት የልደትን በዓል ታላቅነት ገልጿል፡፡ (ገብረ እግዚአብሔር ኪደ (ተርጓሚ)፡ አምስቱ የንስሓ መንገዶች (፳፻፲፩ ዓ.ም. ገጽ ፴፮) ፡፡ እንግዲህ ይህን በዓል ለማግኘት በነቢያት ጾም በኲል በጥልቅ መመኘት መጓዝ ያስፈልጋል፡፡ አንድ ሰርግ በሚኖርበት ጊዜ የሰርጉ ዕለት ከመድረሱ አስቀድሞ ዝግጅቶችን ማድረግና ለዋናው የበዓል ቀን ራስን ማመቻቸት እንደ ሚያስፈልግ፣ ይህን ታላቅ በዓል በሐሤት ለማክበር በጾም ቅድመ ዝግጅታችንን ማመቻቸትና ለበዓሉ ዕለት የተገባን እንድንሆን በጾም መጓጓዣነት ተግተን መድረስ አለብን፡፡ አምላካችን እግዚአብሔር ላለመጾም ከምናቀርበው ምክንያት ጠብቆ ጹመን እንድንጠቀም ይርዳን አሜን፡፡

✞ ✞ ✞

# ኦሪት ወነቢያት ወወንጌል ሰበኩ በክርስቶስ

*(ሃ.አ. ምዕ ፫ ክፍል ፩ ቁጥር ፪)*

*በመ/ር ተስፋማርያም ቢሰጥ*

የተወደዳችሁ ኦርቶዶክሳውያን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢር ሲገባ ኅሊናን ሰብሰብ አድርጎ መቃኘት ተገቢ ነው። ለምን ቢባል የሰው ልጅ ልቡና በአራት ነገር ተመስሏል። ይህውም በመንገድ፣ በዓለት፣ በእሾህና በመልካም መሬት ነው። (ማቴ. ፲፫፥፬-፱) ከነዚህ መካከል ለዘር ተስማሚው ማሳ መልካም መሬት የተባለው ነው። ይህም የዘሩበትን የሚያበቅል አንድ ቅንጣት ተዘርቶበት ሠላሳ፣ ስድሳና መቶ ፍሬ የሚያፈራ የታደለ መሬት ነው። የሰው ልቡናም መልካም መሬት ሲሆን መምህራን ሊቃውንት የዘሩበትን ቃለ እግዚአብሔር ያበቅላል ከውኃ ዳር የተተከለች ዛፍ ሁልጊዜ ልምላሜ እንደማይጠፋባት ፍሬን ከመስጠት ከዓመት እስከ ዓመት እንደማትጎድል ሁሉ እኛም የሰው ልጆች በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኘን በቤተ መቅደስ ተተክለን በእግዚአብሔር ቃል ታርመንና ተኮትኩተን የምናድግ ከሆነ ልምላሜ ሃይማኖትን፣ ጽጌ ትሩፋትን፣ ፍሬ በረከትን (ምግባርን) ከመስጠት ወደ ኋላ አንልም።

ይህንም ለማድረግ ከሥጋዊ ሐሳብ ተላቆ ለሰይጣን የሚሆነውንና ሰይጣን የሚወደውን ለሰይጣን አሽቀንጥሮ በመጣል የእግዚአብሔር የሆነውን በመያዝ ልቡናን አስተካክሎና አጽንቶ መቅረቡ ተገቢ ነው። የሰይጣን ገንዘቦች የሚባሉት ጣዖት ማምለክ፤ ዝሙት፤ ርኵሰት፤ ሟርት፤ ጥል፤ ክርክር፤ ቅንዓት፤ ቁጣ፤ ራስ ወዳድነት፤ መለያየት፤ አድመኝነት፤ ምቀኝነት፤ ስካር፤ መናፍቅነት ይህን የሚመስል ነው። እነዚህን ለሰይጣን መልሶ የእግዚአብሔር የሆኑትን ዘጠኙን የመንፈስ ፍሬዎች ታጥቆ መኖር ልቡናን የተስተካከለ ያደርጋል። ወደ ርእሰ ጉዳያችን ስንመለስ ልቡናው የቀናለት ቅዱስ ሄሬኔዎስ የሐዋርያት ደቀ መዝሙራቸው ሲሆን ኤዶም በምትባል ሀገር በኤጲስ ቆጶስነት ተሹሞም አገልግሏል። ይህ ሊቅ የክርስቶስን ነገር ሲነግረን ‹‹ኦሪት፣ ነቢያትና ወንጌል ክርስቶስን ሰበኩ›› በማለት ገልጾታል።

ሊቁ የተናገረውን ዘርዘር አድርገን ስንመለከት "ውእቱ ኅሊናሁ ለአብ ፍጹም ቃለ እግዚአብሔር ዘተወልደ እምኔሁ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ ገባሬ ኵሉ ምስለ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ፈጣሪሁ ለሰብእ ዘህልው በኵሉ ግብር ሊቀ አበው በውስተ ሊቀ አበው ሐጋጌ ሕግ በውስተ ሕግ ፤ የአጥቢያ ኮከብ ሳይፈጠር ከሱ የተወለደ የአብ ኅሊናው ፍጹም ቃለ እግዚአብሔር እርሱ ነው ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሜ ከሆድ ወለድሁህ እንዳለ (መዝ. ፻፱፥፫) ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ሁሉን የፈጠረ በሥራ ሁሉ ያለ በአበው አለቆች ዘንድ የአበው አለቃ እርሱ ነው። ሕግን በመሥራት ጊዜ ሕግን የሠራ እርሱ ነው። ካህናትን የሚሾም ሊቀ ካህናት ነገሥታትን የሚገዛ በነቢያት አድሮ የሚናገር በመላእክት ላይ ንጉሥ እርሱ ነው። በሰው ባሕርይ ሰው የሆነ፣ ከአብ የተወለደ፣ ከባሕርይ አምላክ የተገኘ፣ የባሕርይ አምላክ የዘለዓለም ንጉሥ እርሱ ነው። ኖኅን የጠበቀው፣ አብርሃምን የመራው፣ ከያዕቆብ ጋር እንግዳ የሆነና ከዮሴፍ ጋር የተሸጠ እርሱ ነው" (ሃ.አበ.፯፥፬-፱) በማለት፡-

፩. ሕግን በመሥራት ጊዜ ሕግን የሠራ እርሱ ነው (በኦሪት)፤

፪. የአጥቢያ ኮከብ ሳይፈጠር ከሱ የተወለደ የአብ ኅሊናው ፍጹም ቃለ እግዚአብሔር እርሱ ነው (በነቢያት) (መዝ.፻፱፥፫)

፫. በሰው ባሕርይ ሰው የሆነ እርሱ ነው (በወንጌል)

በሦስቱም በኦሪት በነቢያት በወንጌል የተሰበከ ክርስቶስ እንደሆነ ቅዱስ ሄሬኔዎስ በግልጽ አስተማረ። ሦስቱን በቅደም ተከተል ከማየታችን በፊት ከስሙ ትርጓሜ እንነሣ ክርስቶስ ማለት መሲሕ ማለት ሲሆን መሲሕ ማለት ደግሞ ቅቡዕ ማለት ነው ቅቡዕ ማለትም ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆኖ የተዋሐደ ማለት ነው ስለዚህ አምላክ ሰው ሲሆን የወጣለት ስም ነው።

## ፩. በኦሪት እንዴት ተሰበከ?

ለሰው ልጅ የተሰጠው ተስፋ (በኋላ በክርስቶስ ፍጻሜ ያገኘው) ከዘመነ ኦሪት በፊት ከአዳም ጀምሮ ለነበሩ አባቶች የተናገረውን በኦሪቱ ላይ ተገልጾ እናገኘዋለን። ‹‹በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘሩ መካከል ጠላትነትን

አደርጋለሁ። ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ›› (ዘፍ.፫፥፲፭) ብሎታል። ይህውም ‹‹ባንተና በሴቲቱ›› ማለት በእባብና በሔዋን ጠላትነት አደርጋለሁ ብሎ በሔዋንና በዲያብሎስ መካከል የሚሆነውን ታላቅ ጸብና ክርክር ለአዳም ነግሮታል። እግዚአብሔር እንዲህ ማለቱ ሔዋን ከዲያብሎስ ጋር ተጣልታ ድል የምትነሳው ሆኖ አይደለም። ከሔዋን ባሕርይ ከተገኘች ዳግማዊት ሔዋን ከምትባል ከቅድስት ድንግል ማርያም የዲያብሎስን ምክር የሚያፈርስ፣ ኃይሉን የሚያደክም፣ መርዙን የሚያጠፋ ቤዛ ኩሉ ዓለም ክርስቶስ የመወለዱን ነገር መናገሩ ነው።

እንዲሁም ‹‹በዘርህ እና በዘሯ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ›› በማለትም የዲያብሎስ የግብር ልጅ በተባሉት ዲያብሎስ ክፉ ሥራውን በሠራባቸው በአይሁድ መካከል እና ከሔዋን ባሕርይ ከተገኘ ከዳግማዊት ሔዋን ከድንግል ማርያም በድንግልና በተወለደው ልጇ በክርስቶስ መካከል ፀብና ክርክር እንደሚሆን አስቀድሞ ገለጠ ።

ይህውም ኃጢአት በመሥራት የተጎዱ አዳምና ሔዋን ሲሆኑ ተስፋውም የእነርሱ ሲሆን ሔዋንን ብቻ ለይቶ ‹‹በዘርዋ›› ተስፋውን የሰጠበት ምክንያት የእግዚአብሔር ልጅ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ተወልዶ የሚያድናቸው ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት እንደተወለደው ሁሉ ድኅረ ዓለም ደግሞ ያለ አባት ከዳግሚት ሔዋን ከድንግል ማርያም ብቻ በድንግልና ተወልዶ ነውና ለሔዋን ብቻ ሰጥቶ ተስፋውን ገልጾላታል። አካላዊ ቃል ለአዳም በሰጠው ተስፋ መሠረት ከሔዋን ዘር ይወለድ ዘንድ ስላለው ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር ‹‹እንግዲህ ሕግ ምንድን ነው ? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ›› (ገላ.፫፥፲፱) በማለት የሰጠውን ተስፋ አጉልቶ ከተናገረ በኋላ በሰጠው ተስፋ መሠረት ከቅድስት ድንግል ማርያም የመወለዱን ነገር ሲገልጽ ‹‹ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ›› (ገላ. ፬፥፬) ሲል ገልጾአል። “እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናውን ትነድፋለህ” በማለት የተናገረው ሊፈጸም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ሰው በሆነ ጊዜ ዲያብሎስ በገዳመ ቆሮንቶስ በአካል በመምጣትና በመፈተን ከዚያም በልበ አይሁድ አድሮ ሰኰና ትምህርቱንና ሰኰና ተአምራቱን በመቃወም በመስቀል ሲያሰቅለው ጌታ በመስቀል ተሰቅሎ በመስቀሉ የእባቡን የዲያብሎስን ራስ ቀጥቅጦ ድል በመንሳት ዓለምን አድኖ ለአዳምና ለሔዋን የሰጠውን የተስፋ ቃሉን ፈጽሞታል ።

ቅዱስ ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር ተመርቶ ‹‹እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ አንተ ባሕርን በኃይልህ አጸናሃት አንተ የእባቦችን ራስ በውኃ ወስጥ ሰበርህ አንተም የዘንዶውን ራስ ቀጠቀጥኽ›› (መዝ. ፸፫፥፲፪-፲፬) በማለት ለአዳም ተስፋ በሰጠው መሠረት በመስቀሉ ዲያብሎስንና ሠራዊቱን ድል የማድረጉን ነገር ተናገሯል።

መሲህ ክርስቶስ ከአብርሃም ወገን እንደሚወለድ እንዲህ ተብሎ ተገልጾአል። ‹‹የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፤ ቃሌን ሰምተሃልና›› (ዘፍ. ፳፪፥፲፰) ይላል። እንዲህ ተብሎ የተነገረውን ፍጻሜ ‹‹የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ›› (ማቴ.፩፥፩) ተብሎ በወንጌል የተገለጸ ሲሆን ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስ “እነርሱም አባቶቻችን ናቸው፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ ተወለደ፤ እርሱም ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘለዓለም ቡሩክ አምላክ ነው›› (ሮሜ ፱፥፭) በማለት አስረደቷል።

ክርስቶስ ከአብርሃም ዘር ከነገደ ይሁዳ እንደሚወለድ እንደሚወለድ ብቻ ሳይሆን ተወልዶ የሚያከናውናቸው ተግባራትም ተገልጸዋል። ይህን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ “መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፤ ምስፍናም ከአብራኩ ለእርሱ የሚጠብቀውን እስኪያገኝ ድረስ፤ የአሕዛብ ተስፋቸው እርሱ ነውና፤ አህያይቱን በወይን ግንድ ያስራል፤ የአህያይቱንም ግልገል በወይን ሐረግ፤ ልብሱን በወይን ያጥባል፤ መጎናጸፊያውንም በዘለላው ደም።” (ዘፍ. ፵፱፥፲-፲፩) በማለት ከአይሁድ ዘር መወለዱን ብቻ ሳይሆን በውርንጫ የተመሰሉ አሕዛብን በአህያይቱ ግልገል የተመሰሉ እስራኤል ዘሥጋን በማየ ገቦው (ከጎኑ በሚፈሰው ውኃ ) ልጅነትን በመስጠት ማለትም ‹‹ልብሱን በወይን ያጥባል›› በማለት ልጅነትን ‹‹መጎናጸፊያውንም በወይን ደም›› በማለት በሥጋውና በደሙ ሕዝብንና አሕዛብን እንደሚያከብር ተገለጸ። ፍጻሜውንም ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ጌታችን ከአይሁድ ነገድ እንደወጣ የተገለጠ ነውና›› (ዕብ. ፯፥፲፬) በማለት ገልጾታል እስራኤል ዘሥጋም በምድረ በዳ ሲጓዙ በበረሃ ውስጥ ከዐለት ያፈለቀው ውሃ ክርስቶስን የሚገልጽ ነው። ሙሴም እጁን ዘርግቶ ድንጋዩን

ሁለት ጊዜ በበትሩ መታው ከዚህም ውኃ ወጣ ማኅበሩም ከብቶቻቸውም ጠጡ (ዘኍ. ፳፥፲፩) ፤ (ዘፀ. ፲፯፥፩) ተብሎ የተገለጸው ለክርስቶስ እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና ያም ዐለት ክርስቶስ ነበር›› (፩ቆሮ.፲፥፬) ሕዝቡም አሕዛቡም ጠጥቶ የሚረካበት ውኃ የፈለቀበት ዐለት ክርስቶስ እንደሆነ ነገረን።

## ፪. ክርስቶስ በነቢያት አስተምሮ

ቅዱሳን ነቢያት በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝተው አምላካችን ከእመቤታችን እንደሚጸነስ፣ እንደሚወለድ፣ እንደሚሰደድ፣ በዮርዳኖስ እንደሚጠመቅ፣ ወንጌልን ዙሮ እንደሚያስተምር፣ መከራን እንደሚቀበል፣ እንደሚሰቀል፣ እንደሚሞት፣ እንደሚነሣ፣ እንደሚያርግ፣ ዳግም እንደሚመጣ በሰፊው አስተምረዋል። የእግዚአብሔር ልጅ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ ደረሰ ሥጋን አልተዋሐደም ፤ አስቀድሞም በነቢያት አድሮ ትንቢትን አናግሯል ፤ ሱባኤንም አስቆጥሯል የሥጋዌውም ምስክር ቀደምት ነቢያት ናቸው። በመሆኑም የነቢያትን ትምህርት ማወቅ ምሥጢረ ሥጋዌን በትክክል ለመረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው። እንዲህ ከሆነ ነቢያት ስለክርስቶስ ከአስተማሩት የተወሰኑትን እንመልከት።

ልዑል ቃል ኢሳይያስ የሰው ልጅ ከነፍስ መቅሰፍት የሚድንበትን ምልክት "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" (ኢሳ. ፯፥፲፬) ብሎ የገለጸው እመቤታችን በድንግልና ጸንሳ መውለዷን ለማስረዳት ነው። ይህንም ‹‹ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል›› (ኢሳ. ፱፥፯) በማለት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ገና ሳይወለድ እንደተወለደ አድርጎ በመግለጽ ደረቅ ሐዲስ የሚባለውን ትምህርት አስተማረን። ይኸውም የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራልና የተባለለትና ሥልጣን የባሕርይ የሆነለት ሕፃን መስቀልን በጫንቃው ተሸክሞ አጋንንትን ከሰው ልቡና በማውጣትና በማሳደድ ለዓለም ሰላምን ሰጠ።

ነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅየልም በኅቱም ድንግልና የመወለዱን ነገር እንዲህ ብሎ ገልጾታል ‹‹እግዚአብሔር ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል›› (ሕዝ. ፵፬፥፪) በማለት አምልቶና አስፍቶ የተናገረው (ማቴ. ፩፥፳፪-፳፫) ተፈጽሟል። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትም ‹‹እነሆ በኤፍራታ ሰማነው በዱር ውስጥም አገኘነው›› (መዝ. ፻፴፩፥፯) በማለት በዱር ተጥሎ በጨርቅ ተጠቅልሎ በግዕዘ ሕፃናት ሲያለቅስ ሰማነው ሲል ያልተፈጸመው እንደተፈጸመ ሆኖ ተገልጾለት ስለመሲሀ ክርስቶስ ሰብኮልናል። ስለዚህ ነቢያት አምልተውና አስፍተው የተናገሩት ትንቢት የመሰሉት ምሳሌ ማለትም በሐመልማልና ነበልባል አምሳል፣ በጠልና በፀምር፣ በቆመ ድንጋይና በሚያስፈራ አንበሳ አምሳል መስለው የተናገሩት መድኅን ክርስቶስን የሚሰብክ ነው። ስለዚህ ታላቁ ቅዱስ አባት ሄሬኔዎስ ‹‹አሪት ነቢያት ወንጌል ክርስቶስን አስተማሩ›› በማለት ሦስቱንም በማሰናሰል የተናገረው በተለይ ከወንጌል በፊት የነበሩት ኦሪትና ነቢያት በወንጌል የሚፈጸመውን በሰፊው እንደገለጹና ወንጌል ዳግም አካሉ የተገለጸባት ስለሆነች ቀጥሎ እንመልከት።

## ፫. ክርስቶስ በወንጌል

የሰው ልጅ በመጀመሪያ ትእዛዘ እግዚአብሔርን በመጣሱና በሕገ ልቡና መተዳደር ቢያቅተው በሙሴ አድሮ ሕገ ኦሪን በደብረ ሲና ሠርቶ እርሱ እንዲቀርብ እስራኤል ዘሥጋ እንዲመሩበትና ከሙሴም ቀጥሎ ነቢያትን በመሾም በእነርሱ እንዲማሩ እንዲገሠጹና ተስፋውን እንዲጠባበቁ ቢናገራቸውም በሕጉ መኖር እና ሕጉን መጠበቅ ትእዛዙን መፈጸም አልቻሉም ነበር። ስለዚህ ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ወልደ እግዚአብሔር በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ወደዚህ ዓለም መጣ፤ አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ፤ ሕገ ወንጌልንም ሠራ። በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ የሠራት ሕገ ወንጌል ስለ ክርስቶስ ምን መሰከረች? የሰው ልጅስ ክርስቶስን እንዴት ተቀበለው? የሚሉትን ጥያቄዎች አንሥተን መመልከት ተገቢ ነው።

ወንጌልን የሠራልን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለራሱ ሲናገር "እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ። (ዮሐ. ፮፥፵፰)፤ መልካም እረኛ እኔ ነኝ። (ዮሐ. ፲፥፲፩)፤ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ። (ዮሐ.፰፥፲፪)፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ። (ዮሐ. ፲፥፴፮)፤ እኔና አብ አንድ ነን። (ዮሐ.፲፥፴)፤ ትንሣኤ እና ሕይወት እኔ ነኝ። (ዮሐ.፲፩፥፳፭፤ "የእውነትና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ።" (ዮሐ.፲፬፥፮)፤ እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ ያለ እኔ ምንም

ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የማትኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል፤ ይደርቅማል (ዮሐ.፲፭፥፭-፯) በማለት ስለራሱ አስተማረን።

በተለይም ‹‹ነኝ›› ‹‹እኔ ነኝ›› በማለት በማስረገጥ ስለርሱ ካስተማረ በኋላም እኔ የወይን ግንድ ነኝ ብሎ እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ በማለት እና ያለ እርሱ መኖር እንደማንችል ፍሬ ምግባር ማፍራት እንደማይቻለን እና ከወይን ግንድ የተለየ ቅርንጫፍ እንደሚደርቅ ሁሉ እኛ የሰው ልጆችም ከሱ ከተለየን ምንም ዓይነት ሕይወት እንደማይኖረን በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል፤ ይደርቅማል በማለት ነገረን። ስለሆነም የወይን ቅርንጫፍ የተባሉ ሐዋርያት፣ ሰብአ አርድእት፣ ሰማዕታት፣ ሊቃውንት፣.....በአላውያን አደባባይ ሳይፈሩና ሳያፍሩ ስሙ ሕይወት መድኃኒት ካለው ከክርስቶስ መከራ መስቀሉን ተሸክመው የራሳቸውን ፈቃድ ሳይሆን የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ክርስቶስን ሰበኩ ስለ ጽድቅ ብለው በዚች ዓለም እንየተንከራተቱ ኖሩ።

## ያልተቀበሉት እነማን ናቸው?

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኦሪትም በነቢያትም በወንጌልም ቢሰበክም በአንጻሩ ደግሞ ያልተቀበሉትም ነበሩ። ከወይኑ ግንድ የተለዩት የገዛ ወገኖቹ አልተቀበሉትም ‹‹እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ አልተቀበላችሁኝም›› (ዮሐ. ፭፥፵፫) በማለት እንደገለጸው የሰው ልጅ በመንጸፈ ደይን መውደቁን በእግረ አጋንንት መጠቅጠቁን አይቶ፣ ልዑል ባሕርዩን ዝቅ አድርጎ ይህን ዓለም ሊያድን መጣ። እነርሱ ግን አልተቀበሉትም ቅዱስ ዮሐንስም ይህን ሲገልጽ ‹‹የእርሱ ወደ ሆነው መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀሉትም›› (ዮሐ.፩፥፲፩) ብሎ ገልጾታል። ይህንም አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራትን እያደረገ፣ አጋንንትን ከሰው ልቡና እያስወጣ፣ ድውይ እየፈወሰ፣ ለምፃም እያነፃና ኅብስት አበርክቶ እየመገበ ቢያስተምራቸው ትምህርቱን አንቀበልም አምላክነቱን አናምንም አሉ። እነዚህም ጸሐፍት ፈሪሳውያን እንዲሁም ከነሱ በኋላ እስከ ዓለም ፍፃሜ የሚነሡት ሲሆኑ እንዲህ ይላቸዋል ‹‹እናንተ እርስ በርሳችሁ ክብር የምትቀባበሉ ከአንዱም ከእግዚአአብሔር ያለውን ክብር የማትፈልጉ እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ? እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ ። የሚከሳችሁ አለ እርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር እርሱ ስለእኔ ጽፏልና መጻሕፍትን ካላመንችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ›› (ዮሐ. ፭፥፵፬-፵፯) ቤተ አይሁድ ሙሴም ስለ እነርሱ ጽፎላቸው ባለቤቱ ክርስቶስም እያስተማራቸው ስለራሳቸው ዝናና ክብር ብለው አንቀበልም አሉት።

በተቀራኒው አሕዛብ ግን ስለ ክርስቶስ አንድም ነገር ያልሰሙ ስለ እግዚአብሔር አንዳች ነገር የማያውቁ ተአምራቱን ያላዩ በፍልስፍና መጻሕፍቶቻቸው በገጣሚዎቻቸው በጥበበኞቻቸው ስለክርስቶስ አንዲትም መስመር ያልተጻፈላቸው ሆነው ሳለ አመኑት፤ ወደዱት፤ ተቀበሉትም፤ ክብርንም አገኙ ። ‹‹ቀራጮችና አመንዝሮች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመግባት ይቀድሟችኋል›› (ማቴ.፳፩፥፴፩) በማለት የገሠጻቸው ለዚህ ነው። የስሙን ዝና ተሸክመው ቤተ አይሁድ ስለራሳቸው ክብር ሲሉ ለመቀበል ወደኋላ ሲሉ አሕዛብ ግን ምንም ዓይነት ዝና ሳይኖራቸው ስሙ ሕይወት መድኃኒት ነው ብለው አምነው ከበሩበት ቤተ አይሁድ ቢንቁትም እንኳን ‹‹ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ›› (መዝ.፻፲፯፥፳፪) እንደተባለ ክርስቶስ የማእዘን ራስ ሆኗል።

ስለዚህ ቅዱስ ሄሬኔዎስ እንዳለው ኦሪት ‹‹ነቢያት ወንጌል ክርስቶስን አስተማሩ›› ነገር ግን አይሁድ ግን ኦሪትን ነቢያትን በጆሮአቸው ሰምተው ወንጌል በአካል ተሰብኮላቸው እነርሱ ግን እያዩ የማያዩ እየሰሙ የማይሰሙ ዝንጉአነ አእምሮ ሆነዋል። ይህንም ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጸው ‹‹የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውን ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም የማያምኑም ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና›› (ሮሜ ፲፥፫-፬) በማለት እነዚህ የራሳቸውን ጽድቅ የሚያቆሙ ለራሳቸው ዝና የሚሞቱ ሕግ እናከብራለን እያሉ የሕግ ፍጻሜ ክርስቶስን ግን መቀበል ያቃታቸው እንደሆኑ ያስረዳናል። ሐዋርያው አያይዞም ‹‹እንግዲህ ምን እንላለን? ጽድቅ ያልተከተሉ አሕዛብ ጽድቅን አገኙ እርሱ ግን ከእምነት የሆነ ጽድቅ ነው እስራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም›› (ሮሜ ፱፥፴-፴፩) በማለት አስረዳን። በጣም የሚያሳዝኑት የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ እምነት ማደግ አለመቻላቸውና እያደሩ እየቀጨጩ መሄዳቸው ነው። እንዲሁም መስቀል ላይ በደሙ ፈሳሽነት

የገለጸውን ፍጹም የሆነውን የክርስቶስን ፍቅር ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እምቢ አሻፈረኝ ማለታቸው በተነገረላቸው ተስፋ መጠቀም አለመቻላቸው ነው፡፡

ለሕዝብም ለአሕዛብም የሚበቃውን ክርስቶስን አልተመለከቱም ይልቁንም በግዝረት የሚያምኑ አይሁድ ‹‹ከኃጢአተኞች ጋር ይበላል›› ብለው ክርስቶስን ተቃወሙት ምሥጢሩ ባይረዳቸው ነው እንጂ ቢረዳቸውማ ‹‹በስውር ከአይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው መገረዝም በመንፈስ የማድረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም›› (ሮሜ ፪፥፳፱) ተብሏል፡፡ ግዝረት ማለት ይህ ነው ታዲያ ይኽን መቀበል ካቃታቸው የአይሁዳዊነት ብልጫው ምንድን ነው?›› ስለዚህ እኛም በሕይወተ ሥጋ እያለን ክርስቶስን በሥራው ልንከተለው ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ እነርሱ የአይሁዳዊነት ብልጫው ምንድን ነው? ተብለው እንደተጠየቁ እኛም የክርስትና ብልጫው ምንድን ነው ተብለን እንጠየቃለን?፡፡

ሳንፈልገው የፈለገን፣ ሳንወደው የወደደን፣ ስንገፋው ያልገፋን፣ ስንርቀው ያልራቀን አምላካችን ለእኛ የከፈለውን ዋጋ ማስታወስ ተገቢ ነው ሊቁ ‹‹ኦሪት ነቢያት ወንጌልም ክርስቶስን አስተማሩ›› አለ ኦሪትና ነቢያት አስቀድመው ክርስቶስ ለእኛ የከፈለውን ዋጋ አስተማረች ያውም በክርስቶስ ወርቀ ደም መገዛታችን ነው፡፡ (፩ ጴጥ. ፩፥፲፱) ታዲያ እርሱ ይህን ዋጋ ለመክፈል ወደሰው ልጅ ሲመጣ ለራሱ የሚሆን ማደሪያ አልነበረውም ይህንም ‹‹ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይ ወፎች መስፈሪያ አላቸው ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም›› (ማቴ.፰፥፳) በማለት መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ ተናግሯል፡፡

ፍጥረታት እያንዳንዳቸው እንደ አቅማቸው የራሳቸው የሆነ ማረፊያ አላቸው፡፡ ለሰው ልጅ (ክርስቶስ) ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም ሲባል ሰዎች ራሳቸውን የሚያስጠጉበት የሳር ጎጆ አጣ ማለት አይደለም ለምን ቢባል ቀን በምኩራብ ያስተምራል ሌሊት በደብረ ዘይት ዋሻ ሲጸልይ ያድራል አጣ የተባለው የሰው ልቡና ነው የሰው ልቡና ለማደሪያ ቢመርጠውም ሰው ግን ልቡናውን በኃጢአት ቆልፎ አላሳድርም አለ እንደዶቹም ተአምራትን ሲያደርግ እባክህ ከዚህ አልፈህ ሂድልን ይሉ ነበር ‹‹ከአገራቸው እንዲሄድላቸው ለመኑት (ማቴ. ፰፥፴፬) ይህም የሆነው የሰው ልጅ ከመክፋቱና የሚፈልገውን አምላክ አለመፈለጉ ነው፡፡

ይህ ካልሆነ ግን በሥጋ የተገለጠው፣ በመንፈስ የጸደቀው፣ ለመላእክት የታየውን፣ በአህዛብ የተሰበከውን፣ በዓለም የታመነውን፣ በክብር ያረገውን፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚሰጠውን ክብር ማግኘት አይቻልም፡፡ መሐሪነቱን እያሰብን ወደ እርሱ መቅረብ ይገባል፡፡ “ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ” የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስም አምላኬ መከራውን የተቀበለው ለእኔ ነው በማለት መከራ ሳይበግረው እስከ ፅንፈ ምድር ድረስ ክርስቶስን ሰበከ ስለዚህ ኦሪት ነቢያት ወንወጌል ክርሰቶስን ሰብከውላቸው ያላመኑ አይሁድ ከክብር እንደራቁ አሕዛብ ግን በማመናቸው በክብሩ እንደተጎናጸፉ ሁሉ በእኛም ላይ የአምላካችን የክብሩ ሙላት በላያችን ሞልቶ የሚፈሰው ወደ እርሱ መቅረብ ስንችል ነው፡፡ ወደ እርሱ የምንቀርበው በኑሮአችን፣ በቤተሰብ፣ በባህል፣ በአለባበስ፣ በትዕግሥት፣ በፍቅር፣ በፈተና፣ በመከራ፣ ሲመችን ሳይመችን፣ በጊዜውም አለጊዜውም ሰንደክም ስንበረታ፤ ክርስቶስን የምንሰብከው በግድ አይደለም ፡፡ ነፃ ፍቃድ ለሁላችን ያለዋጋ ተሰጥቶናል ይህን ነፃ ፈቃዳችን ተጠቅመን የአምለካችንን ምሕረት አጋዥ አድርገነው ሁሉን ነገር ማድረግ የምንችለው፡፡ ይህንንም ለማድረግ፣ ልጅነታችንን ለመጠበቅ፣ በንስሐ ሕይወት ለመኖር፣ ልምላሜ ሃይማኖት፣ ፍሬ ምግባር ሁልጊዜ ከእኛ እንዳይጠፋ በወይኑ ግንድ በክርስቶስ መኖር ይጠበቅብናል፡፡ በዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ቸርነቱ ይጠብቀን፡፡ ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን !!

✞ ✞ ✞

# ዕቅበተ እምነት (Apology)

## ዐቢይ ጉዳይ

*በሕግና ዕቅበተ እምነት አገልግሎት ማስተባበሪያ*

ዕቅበት፤ ዐቀበ ከሚለው ግሥ የተገኘ ሲሆን ፡፡ ትርጉሙም መከላከል፣ መጠበቅ (Apology) ማለት ነው፡፡ ዕቅበተ እምነት እምነትን መጠበቅ ማለት ሲሆን እምነትም የሚጠበቀው ከኢአማንያንና ከከሓድያን የሐሰት ትምህርት፤ ከመናፍቃን ቅሰጣ፤ ከዓለማዊ ፍልስፍና፤ ከዓለማዊነት (Secularism) ከግለሰባዊ ፍላጎትና ጥርጣሬ ሁሉ ነው፡፡ ዕቅበተ እምነት፤ በእምነት ሕይወት ላይ የጸና የግለሰቡን ሰብእና፣ ዕውቀትና ጥበብ መሠረት አድርጎ የሚቀርብ አገልግሎት ነው፡፡ እምነት በአማኙ ሁሉን አቀፍ የሕይወት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በተግባር የሚገለጽና በግንኙነቶች የሚታወቅ እንደ መሆኑ መጠን ዕቅበተ እምነትም እንደዚሁ በትምህርትና በምግባር አርአያነትን የሚፈልግ ለቤተ ክርስቲያን የመቆም የባለ አደራነት ሥራ ነው፡፡

ዕቅበተ እምነት በሰፊው የሚታወቀው ከሐዋርያት ተከትለው፣ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ወይንም በዘመነ ሰማዕታት ከነበሩ "ዐቃብያነ ሃይማኖት፣ የእምነት ጠበቆችና ቀዋምያን ለቤተ ክርስቲያን (Apologists)" በሚሉ መጠሪያዎች ከሚታወቁ አባቶች ጋር በተገናኘ ነው፡፡ (ቀ/ዶ/ር ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ በምድር ላይ (ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ)፣ አንደኛ መጽሐፍ፣ ፳፻፫ ዓ.ም፣ ገ. ፪፻፳፯) በዋናነት ሁለተኛውን ክፍለ ዘመንና እነዚህን ቀዋምያን እናንሣ እንጂ ጥብቅናው የጀመረው በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን፣ ክብር ይግባውና በራሱ በጌታችን ስለ ራሱ በቀረቡ ክርክሮች ነው፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ም.፩ እስከ ም. ፯ የተዘገቡት ጉዳዮች ለዚህ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ሐዋርያቱም በዚሁ መንገድ ቀጥለው ለዐቃብያነ እምነት አስረክበዋል፡፡ ሃይማኖታችንና ክብራችን ተነካ ከሚሉት ከማኅበረ አይሁድ፣ ራሳቸውን ሲያስመልኩ ከነበሩት የሮም ነገሥታትና የግሪክ ፈላስፎች የተጋረጠውን የወቅቱን ታላቅ ፈተና ተረድተው ለቤተ ክርስቲያን የቆሙት እነዚህ አባቶች ከቀደምቶቻቸው ከሐዋርያት የወረሱት ብዙ ነገር አለ፡፡

በእነዚህ ዘመናት የነበሩ በርካታ ክርስቲያኖችን፤ በአማናዊው እምነት ላይ ይቀርቡ የነበሩ ክሶችና የሐሰት ውንጀላዎች እንዲፈሩና እንዲጠራጠሩ ያደርጓቸው ነበር፡፡ እነዚህን ፈተናዎች እየተጋሩ የነበሩት ዐቃብያነ እምነት፤ በሕይወት፣ በቃል ትምህርትና በመጻሕፍት የክርስትናን ልዕልና ለዓለም አሳይተዋል፡፡

## ዕቅበተ እምነት በዘመነ ሐዋርያት

ጌታችን ከዓለም መርጦና አስተምሮ የሾማቸው ሐዋርያት፤ እነርሱ ያመኑትን በማያምኑ፣ ነገራቸውን በማይቀበሉና አልፎ ተርፎም በሚዘባበቱባቸው ሰዎች ይፈተኑ ነበር፡፡ ይህን ፈተና ምክንያት በማድረግ ቅዱስ ጴጥሮስ ተቃዋሚዎቹን ዝም የሚያሰኝ  ሁሉን አቀፍ ምላሽና ኋላ ለሚመጡት ዐቃብያነ እምነት ታላቅ አርአያ የሆነ ተግባር ይዞ ተገኘ (ሐዋ. ፪፥፲፬፤ ፫፥፲፪ ፤ ፬፥፱)፡፡ የክርስትናን ትክክለኛ ምንነት ይዞ ለሁሉም በግልጽ የቀረበው ይህ ምስክርነት እምነትና እውነትን ለመጠበቅ የሚያስፈልግ ቁርጠኝነት በተነሣ ቍጥር በዋናነት ይታወሣል፡፡ በሐዋርያት ሥራ ውስጥም ተመሳሳዩን አገልግሎት በሰፊው ማየት ይቻላል፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ በአይሁድ መካከል ያደረገው ረጅም ንግግርም ሌላው ማሳያ ነው፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስ በዘመኑ ከነበሩና በራሱና በሚያስተምራቸው ምእመናን ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ከሚችሉ ነገሮች እንዴት ሊጠበቅ እንደሚገባ ሁለት መልእክታትን ጽፎለታል፡፡ በመጀመሪያው መልእክት፡ "ጢሞቴዎስ ሆይ በውሸት ዕውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ" እያለ ሲመክረው እናስተውላለን፡፡ (፩ጢሞ. ፮፥፳)፡፡ ይህም ከተረፈ አይሁድ፣ አዋቂዎች ነን ብለው ከሚመኩ ግኖስቲኮችና ከዓለም ፍልስፍና ሃይማኖትን እንዴት ሊጠብቅ እንደሚገባው ሲያስጠነቅቀው ነው፡፡ "ከንቱ ነገርን የሚያመጡ ድል የተነሡ ሰዎችን ተለያቸው፣ ጽድቅን በኃጢአት፣ እውነትን በሐሰት፣ አምልኮትን በክሕደት፣ ወንጌልን በኦሪት የሚለውጡትን ተለያቸው" እያለ የነበረውን አደጋ በግልጽ ያሳየዋል፡፡ እንዲሁም "መልካሙን አደራ በእኛ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ጠብቅ" ይለዋል  (፪ጢሞ.፩፥፲፬)፡፡

እምነትን በየጊዜው ከሚመጡ ሰው ዘራሽ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ጠብቆ መጀመሪያ የተገለጸችውን፥ በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ የጸናችውን ሃይማኖት አጽንቶ መጠበቅና ለትውልድ ማስተላለፍ ያስፈልጋል፡፡ የኦርቶዶክሳውያን ዓይነተኛ መገለጫ የመጀመሪያዋን እውነት በማይለዋወጥና ባልተቆራረጠ ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ ይዞ መገኘት ብሎም ማስቀጠል ነውና፡፡ "የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናልና፡፡" እንዲል ሐዋርያው (ዕብ. ፫፥፲፬)፡፡

**"ጢሞቴዎስ ሆይ በውሸት ዕውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ"**

ሐዋርያትን ተከትለው የተነሡ ተላውያነ ሐዋርያት (Apostolic Fathers) ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ በማስቀጠልና በማጽናት አገልግሎታቸው ውስጥ ለዕቅበተ እምነት የሚውሉ በርካታ ትምህርቶችን በቃልም በጽሑፍም አበርክተዋል፡፡ ለምሳሌ ፖሊካርፐስ በሐሰት ትምህርት ብዙዎችን ሲያስቱ የነበሩትን ቫለንቲየስና መርቅያን የተባሉ መናፍቃን እንዴት እንዳሳፈራቸውና ብዙዎችን ከክሕደት እንደ መለሰ ማስታወስ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ አበርክቶ ብዙዎችን ማንሣት ቢቻልም የተላውያነ ሐዋርያት ሥራዎች በአብዛኛው ውስጡን የማጽናት ዓላማ የነበራቸው ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ በውጭ የነበሩ ተግዳሮቶችን በሚገባ በመለየትና የእነርሱን ማርከሻ ከትምህርተ ሐዋርያት ምንጭ በመቅዳት በጠንካራ ጽሑፎች የተገለጡት ዐቃብያነ እምነት ናቸው፡፡ እነዚህ አባቶች ክርስትናን አምነው ከመቀበላቸው አስቀድሞ በነበረ ሕይወታቸው ፍልስፍናን፣ የተለያዩ ሳይንሳዊ ዕውቀቶችንና ባሕሎችን ጠንቅቀው የተማሩ ነበሩ፡፡ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ውስጥ በመጡ ጊዜ፤ ያንን ዕውቀት ተገን አድርገው ክርስትናን ለማጥቃት የተነሡትን ሁሉ የሚያሳፍሩ ለመሆን ቻሉ፡፡ ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው እምነትን እንዴት መጠበቅ እንደሚቻልና ከምን መጠበቅ እንደሚገባ ያስተምራል፡፡ በየዘመናቱ የተነሡና ቤተ ክርስቲያንን ከወቅታዊ ፈተናዎች ለመታደግ ሲጥሩ የነበሩ አባቶችም አርአያነታቸውን በሚገባ ተከትለው ተጠቅመዋል፡፡ ዐቃብያነ እምነትን የተመለከተ የሕይወት፣ የጽሑፎቻቸው ይዘትና ተያያዥ ዳሰሳን የምናስከትል ቢሆንም በእነርሱ አርአያነት እንዴት የዕቅበተ እምነት አገልግሎት ልንሰጥ እንደምንችል ጥቂት ነጥቦችን እናንሣ፡፡

## እምነት ከምንና እንዴት ይጠበቃል?

ማመን፤ አለማመን የተባለ ባላንጣ አለው፡፡ አለማመንን መርሐቸው ያደረጉ ኢአማንያንም በራሳቸው አጥር ከመወሰን ይልቅ ወደ አማንያን ሕይወት እየገቡ መሠረት በሌለው ምክንያት ሊሞግቱ ይሞክራሉ፡፡ ስለዚህ በቅድሚያ እምነት የሚጠበቀው ከኢአማንያን ተንኮልና ሤራ ነው፡፡ እምነትንና ቤተ ክርስቲያንን ከምንና እንዴት መጠበቅ እንደሚገባ ከዐቃብያነ እምነት ብዙ መማር ይቻላል፡፡ በወንጌል እንደ ተነገረውና በሚነሡ ጥያቄዎች አንፃር በዐቃብያነ እምነትም እንደ ተረጋገጠው ክርስትና የመጨረሻው እውነትና ብቸኛው የድኅነት መንገድ ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ማሠሪያ በእያንዳንዱ ምእመን ልቡና ውስጥ ገብቶ በእምነቱ ራሱን እስከሚገልጥበት ድረስ መታወቅ አለበት፡፡ በመሆኑም ዐቃብያነ እምነት በብዙኃን ከሳሾቻቸው መካከል ጥቂት ሆነው እምነትን መሠረት ባደረገው ከፍተኛ ዕውቀታቸው የሠሯቸው ሥራዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ፦

አንደኛ፡- የመጀመሪያ ሥራ ይህ ራሳቸውን ክርስቲያኖችን የማጽናት ሥራ ነበር። በዚሁ ጊዜ ክርስትናን አመክንዮአዊ መሠረት የለሽ አድርገው በመቊጠር ጥያቄ ሲያነሡ የነበሩ የግሪክ ፈላስፎች ነበሩ። እነዚህንም በራሳቸው መሣሪያ ማለትም አስቀድመው የተማሩት ቢሆንም ለክርስትና ባስገዙት የፍልስፍና ዕውቀታቸው ፈላስፎችን መሞገት፣ መርታትና ብዙዎችን መመለስ መቻላቸው ታላቅ ድል ሆነ። አገልግሎታቸው በውስጥ ያሉትን ሲያጸና በውጭ የነበሩትን ማምጣት ቻለ። ከዚህ የምንማረው እምነትና እውነት በሕይወታችን ውስጥ በቅለው ፍሬ የሚያፈሩት በብዙ ደጋፊዎች ስለ ተከበብንና ብዙ ስላወቅን ሳይሆን ራሳችን በእምነት በተተከልንበት መጠን መሆኑን ነው። ለሌሎችም ልናስገነዝበው የሚገባውና በኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያኑ ሕይወት ውስጥ ሠርጾ በተግባር ሊገለጥ የሚፈለገው የክርስትና የመጨረሻ እውነትነት ነው።

ሁለተኛ፡- ክርስትናን እንደ አዲስና እንግዳ ትምህርትና እምነት ለሚቈጥሩ ወገኖች ራስን መግለጽ የሚቻልባቸውን መንገዶች አደራጅቶ ማሳየት ነው። ትችቶች የተጨበጠ ማስረጃ ይዘው የቀረቡ ነበሩ ወይስ ካለመረዳትና ከተሳሳተ ግንዛቤ የመነጩ ነበሩ የሚለውን ማሳየት የዚህኛው መንገድ ትኩረት ነው። ስለዚህ የጥያቄዎቹ አመንጪ ለነበሩት አይሁድ የክርስትናን የትንቢተ ነቢያት ፍጻሜነት ለሚከተሉት ክርስቲያኖች በማስረዳትና በምክንያት ለሚሞግቱትም ገቺ የሆነ ምላሽ ማቅረብ ዐቃብያነ እምነት የሚነሡበት የተዋጣ ሥራ ነው። በተመሳሳይ መንገድ ለሚመጡ ፈተናዎች እንዴት መዘጋጀትና እምነትን መጠበቅ እንደሚቻልም ያስተምራል።

ከቀደመው ጋር በይዘታቸው ሊለያዩ ቢችሉም ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ላይ በርካታ የሐሰት ውንጀላዎች ይሠነዘራሉ። በተለያየ ምክንያት እውነታውን የሚሸሹና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን የሚጠሉ ሰዎች ለጊዜው ሊረብሹና ሊያስጨንቁ በሚችሉ ነገሮች ውስጥ በንቃት እየተሳተፉ ነው። ያልተገባ ስም በመስጠት፣ የሐሰት ትርክቶች በመፍጠር፣ አልፎ ተርፎም በኃይል ተግባር ኦርቶዶክሳዊ ክርስትናን እየተዋጉ ነው። ይህን በመሰለው ጊዜ ላይ የቀደሙትን አባቶች አርአያነት ተከትሎ ለቤተ ክርስቲያን መቆምና እውነትን ይዞ መሞገት ያስፈልጋል። በመሆኑም አገልግሎቱን በተረዱ በርካታ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች የዕቅበተ እምነት አገልግሎቱ እየተሰጠ ሲሆን በሰፊው ተጠናክሮ ሊቀጥልም ይገባል።

ሦስተኛ፡- የበለጠ ዝግጁነትንና ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ አገልግሎት ሲሆን ክርስትናን በአዋጅ ከከለከሉትና የሚያስከትለውንም የሞት ቅጣት ከደነገጉት ነገሥታት ጋራ መጋፈጥ ነበር። እነዚያ የዘመኑ ጉልበተኞች በምክንያት የሚያምኑ አልነበሩም፣ ትምህርትን አይቀበሉ፣ ወደ እምነትም እንዳይቀርቡ በጣዖቶቻቸው ተሸፍነዋል። የተቃወማቸውን ሁሉ ይገድላሉ፣ በንጹሐን ክርስቲያኖችም መከራ ይዝናናሉ። በዚህ እሳትና ሠይፍ ውስጥ ሳይፈሩና ሳይሳቀቁ በቀጥታ ለነገሥታቱ እየጻፉ የክርስትናን እውነት ይዘው የሞገቱ ዐቃብያነ እምነት ነበሩ። ዛሬም ቢሆን የዕቅበተ ዕምነት አገልግሎት ይህን መሰሉን ጽናትና ቁርጠኝነት ይፈልጋል።

> **"ከንቱ ነገርን የሚያመጡ ድል የተነሡ ሰዎችን ተለያቸው፣ ጽድቅን በኃጢአት፣ እውነትን በሐሰት፣ አምልኮትን በክሕደት፣ ወንጌልን በኦሪት የሚለውጡትን ተለያቸው"**

# ዐቃብያነ እምነት፡ ሕይወትና ጽሑፎቻቸው

በዋናነት በሁለተኛው ዘመን የተነሡ ጸሐፍያንን ይመለከታል። ሥራዎቻቸውም በግሪክና ሮም ባሕል ምክንያት፥ በፈላስፎች/ፍልስፍና እንዲሁም በግኖስቲኮች ምክንያት ለተፈጠሩት ተጽእኖዎች መልስ ይሰጣሉ። አንዳንዶቹ በቀጥታ ለነገሥታት የተጻፉና ክርስትና የሚከሰስባቸውን ሐሳቦች ሐሰተኝነት በማሳየት የሚሞግቱ ናቸው። በክርስቲያኖች ላይ ይቀርቡ ከነበሩ ክሶች መካከል አንዱ "አማልክት የለሾች" የሚል ነበር። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ክርስትና የሚያምነውና የሚያስተምረው አምላክ ከሳሾቹ እንደሚሠሯቸው ጣዖታት የሚታይና የሚዳሰስ ስላልሆነላቸው ነው። ሁለተኛም፣ ክርስቲያኖቹ ምሥጢራትን በሚፈጽሙበት ጊዜ ስለ ክርስቶስ ሥጋና ደም የሚያስተምሩትንና የሚያደርጉትን ሳይረዱት የቀሩት ከሳሾች "የሰው ሥጋ የሚበሉ" ይሏቸው ነበር።

ለመንግሥት አስተዳደር አስጊና ለሥልጣኔ እንቅፋት እየተደረጉ የተወነጀሉበት ሁኔታም ሌላው ፈተና ነበር። እነዚህ ሁሉ ከተሳሳተ ግንዛቤና ከጥላቻ የመነጩ እንደ ሆኑ ቢታወቅም ለጊዜው እውነት መስሏቸው ለሚስቱ ወገኖች መድረስ የሚገባ ነበረ። ስለዚህ በክርስትና ሕይወት ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች እውነተኛውን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመልኩ እንደ ሆኑ፣ የክርስትናን ጥንታዊ መሠረት፣ የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ መሆኑንና በአንጻሩ የከሳሾች እምነት መሠረት የለሽ መሆኑን የሚገልጽ ምላሽ ይዘው ቀረቡ። ቤተ ክርስቲያን የመንግሥታት ሥጋት ሳትሆን እንዲያውም የማኅበራዊ አንድነት መሠረት እንደ ሆነች፣ ከሀገራት ይልቅ የዓለም ሰላም የሚረጋገጠው በክርስትና እንደ ሆነ በምክንያት ሞገቱ።

በመቀጠል ለከሳሾቹ ቀጥተኛ አጸፋ የሚሆኑ የአምልኮ ጣዖታቸውን ከንቱነት፣ የሥነ ምግባራቸውን ብልሹነትና ከአንድ አምላክ እምነት የወጡበትን ርቀት በይፋ ማጋለጥ ጀመሩ። ይህም በወቅቱ ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ የጠቀመ አገልግሎት ነበር። ምክንያቱም ከሳሾች ጊዜና አመቺ ሁኔታ ባገኙ ጊዜ የራሳቸውን ነውር ይረሳሉ። ለራሳቸው የነገ ዕጣ ፈንታ የሰጉበትን ነገር በብዙዎች ተገብተው ይወነጅላሉ። ታዲያ እንደነዚህ ዓይነት የእውነት ጠበቃ የተነሣባቸው ጊዜ የሸፈኑት ግብራቸው ሁሉ ይገለጣል። በዚህ መሠረት ያን ጊዜም የዐቃብያነ እምነት ጽሑፎች የዘመኑን ክፉ ጠባይ የገለጡና የክርስትናን ሉዐላዊነት ለዓለም ያሳዩ ነበሩ። ዛሬም የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች የሚሠነዝሯቸውን የሐሰት ውንጀላዎች ከንቱነት የሚያጋልጥ ተመሳሳይ አገልግሎት በበረከተ ቍጥር ለማስነወር የተነሡት ሁሉ ነውራቸው ይገለጣል። አባቶች የክርስቶስን አምላክነት በታሪካዊ ዐውድ ፍንትው አድርገው እንዳሳዩ የእኛ ዘመን የወለዳቸውን መሠረት የለሽ ታሪኮችን በታሪካዊ ዐቃቤ እምነትነት ማጋለጥ ያስፈልጋል።

ታሪክ ከሰዎች የማንነት መገለጫ መንገዶች አንዱ ነው። የታሪክ ተፋልሶ ደግሞ የሰዎችን ማንነት የተመለከተ መሠረትን ለማናጋት ሆን ተብሎ የሚደረግ አጥፊ ተግባር ነው። ስለዚህ ከሃይማኖት መሠረታዊ ጉዳዮች ጎን ለጎን ለታሪክም ዋጋ ሰጥቶ መቆም ከዐቃብያን የምንማረው ሌላው ቁም ነገር ነው።

**ታሪክ ከሰዎች የማንነት መገለጫ መንገዶች አንዱ ነው። የታሪክ ተፋልሶ ደግሞ የሰዎችን ማንነት የተመለከተ መሠረትን ለማናጋት ሆን ተብሎ የሚደረግ አጥፊ ተግባር ነው።**

የዐቃብያን እምነት አጠቃላይ ሕይወትና ሥራዎች በዚህ መሰል አጭር አቀራረብ ተሟልቶ ሊገለጽ የሚችል አይደለም። በመሆኑም በቀጣዩ የእያንዳንዳቸውን አባቶች ሕይወትና ሥራዎች ይዘን እንመለሳለን ፤ እስከዚያው ይቆየን!

✞ ✞ ✞

# የተከዜ ምዕራፈ ቅዱሳን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት እና መድኃኔዓለም ዘአቡነ ሐዋርያ ክርስቶስ አንድነት ገዳም



*በወግደረስ አዳል*

## *ክፍል ሁለት*

ውድ አንባብያን ባለፈው ዕትማችን በእናስተዋውቃችሁ ዓምዳችን “የተከዜ ምዕራፈ ቅዱሳን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት እና መድኃኔዓለም ዘአቡነ ሐዋርያ ክርስቶስ አንድነት ገዳምን ከአመሠራረቱ ጀምሮ በርከት ያሉ ጉዳዮችን ማቅረባችን ይታወሳል። ቀሪውንና ክፍል ሁለትን በዚህ ዕትማችን እናቀርባለን። መልካም ንባብ።

### ፫. ገዳሙ ካለፉት ፳ ዓመታት ጀምሮ ያሉ እንቅስቃሴዎች

ገዳሙ ከተዳከመበት ተነሥቶ ዳግም በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ከቀናበት ዓመት ጀምሮ እስካሁን እጅግ አርአያ የሚሆን ፈጣን ዕድገት ላይ ያለ ገዳም ነው። በገዳሙ ውስጥ የአባቶችን የገዳማዊ ሕይወት አጥብቆ በመያዝ አሁን ላይ ያሉ የዘመኑ ፈተናዎችን ለመቋቋም የሚያስችል አሠራርን የሚከተልና ገዳማዊ ሕይወት እውነትም በጸሎትና በሥራ የሚገለጽ መሆኑን ተመጽዋችነት የገዳማውያን ባህል አለመሆኑን የሚያሳይ አርአያ ገዳም ነው። በዚህም ጠንካራ የሥራና የጽኑ አንድነት ሥርዓት በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ከሦስት ወደ ፲፬ ከፍ ያደረጋቸውን የመነኰሳት ቁጥር በ፳፻፲፩ ዓ.ም. ፩፻፲፯ መናንያንና ከ፹ በላይ የአብነት ተማሪዎች እንዲኖሩት አስችሎታል።

ከ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. ጀምሮ በማኅበር “ልመና እስከ መቼ?“ በሚል መሪ ቃል ሁሉም በአንድነት ቃል ከገቡ በኋላ ብዙ ፈተናዎችን ተቋቁመው ራሳቸውን ከመቻል አልፈው ሌሎችን እየደገፉ ይገኛሉ።

### ፫. ፩. የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዘርፉ የሥራ እንቅስቃሴ

በዚህ ዘርፍ የሚመራው የገዳሙ አገልግሎት በሦስቱም የገዳሙ አብያተ ክርስቲያናት ስብሐተ እግዚአብሔር ሳይቋረጥ እየተገለገለ ይገኛል። ለገዳማውያኑና በገዳሙ ዙሪያ ባሉ ፲፬ አጥቢያዎች በቋራ የገዳሙ የእርሻ ልማት ኢንቨስትመንት ባለበት አካባቢ ባሉ አድባራት የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ይሰጣል። ለ፲፫ አድባራት ለእያንዳንዳቸው በዓመት የሁለት ሰው ኮታ አዘጋጅቶ ሙሉ ወጪአቸውን ሸፍኖ ከንባብ እስከ ምስክር ጉባኤ ድረስ እንዲማሩ ያደርጋል። በዚህም ገዳሙ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ጥሩ ግንኙነትና ተቀባይነት እንዲኖረው አስችሎታል። የውስጥ አገልግሎትም እንዳይስተጓጎል ተተኪ አገልጋዮችን ለማፍራት በመንፈቅ ፯ መናንያንን ከየትኛውም የገዳሙ ሥራ ነጻ አድርጎ የአብነት ትምህርት ብቻ እንዲማሩ ያደርጋል። የነገውን የገዳሙን አገልግሎት በማሰብም አንድ የቅዳሴ መምህር እንዲያስመሰክሩ ወደ ደብረ ዓባይ ሌላ የቅዳሴ መምህር መጻሕፍት እንዲማሩ ወደ መጻሕፍት ቤት ልኳል።



### ፫. ፪. የቤተ እግዚአብሔር ዘርፍ የሥራ እንቅስቃሴ

ገዳምውያኑ በጽኑ የገዳም አንድነትና ሥርዓት መኖራቸውን፣ ሁሉም መናኝ ከገዳሙ ሊያገኝ የሚችለውን እንክብካቤ እያገኘ መሆኑን፣ አረጋውያንና ታማሚዎች በትክክል ድጋፍና እንክብካቤ እየተደረገላቸው መሆኑን እና ገዳሙን ብለው የመጡ እንግዶች በተገቢው ሁኔታ መስተናገዳቸውን እየተከታተለ ገዳሙን አሁን ካለበት ደረጃ ላይ አድርሶታል።

ከዚህም በተጨማሪ ወላጅ አልባ ሕፃናትን በገዳሙ ወስጥ ከማሳደግ አልፎ በአካባቢው ለሚገኙ የድሃና የአቅመ ደካማ ልጆችን የመማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ሀገራዊና ክርስቲያናዊ ግደታውን እየተወጣ ይገኛል፡፡




## ፫. ፫. የግብርና ልማት ዘርፉ እንቅስቃሴ

ገዳሙ ራሱን እንዲችል በቋራ አካባቢ በ፲፰ ሄክታር መሬት ላይ የእርሻና የእርባታ ሥራን ያከናውናል፡፡ በገዳሙ ክልልም ውስጥ በቀጭን አበባ ሥላሴ እና በመድኃኔዓለም የአባቶች ገዳም የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በሁሉም የገዳሙ ቅጽር ውስጥ የደን ልማት ሥራዎችን ይሠራል፡፡ በተለይ በዚህ ዘርፍ እጅግ የሚያስደንቀው የውኃ አጠቃቀሙ ነው፡፡ ምንም እንኳ ገዳሙ ከሥሩ የተከዜና የቀጭን አበባ ወንዞች የሚፈሱ ቢሆንም ከሸለቆው ጥልቅነት የተነሣ ለመጠቀም አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ያሉትን የውኃ አማራጮች የሚጠቀምበት መንገድ ግሩም ነው፡፡ ተከዜ ገዳም ላይ ያለው የውኃ አጠቃቀም ለገዳማት ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለምም አስተማሪ ነው፡፡ በተራቀተው የተከዜ ተፋሰስ ላይ የገዳሙን ቅጽርና አካባቢ አረንጓዴ ለማልበስ የሚያደርገው ጥረት ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡



## ፫. ፩. የግንባታ ዘርፉ የሥራ እንቅስቃሴ

በዚህ ዘርፍ ገዳሙ የራሱን የቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ከዲዛይን እስከ ኮንክሪት ሙሊት ግንባታ አንሥቶ የትኛውንም የገዳሙ ግንባታዎች በራሱ መነኰሳት ባለ ሙያዎችና የሰው ኀይል ያከናውናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በግሸን ማርያም የአንቀጸ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን በማስገንባት ላይ፣ በቋራ አካባቢ ፬ (ማር ውሃ ሚካኤል፣ ሰገነት ሚካኤል፣ አዲስ ዓለም ጊዮርጊስና ምርት ገለጎ ኪዳነ ምሕረትን) በላስታና በመቄት ወረዳዎች ፯ (ቂላ ሚካኤል፣ ወይጣ ዲባ ሚካኤል፣ ሻሎ ጊዮርጊስ፣ ዶሮ ላባ ማርያም፣ አሮጌ አምባ በዓለ እግዚአብሔር እና ዙፋን አምባ ማርያም) አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ በሙሉ ወጪቸውን ሸፍኖ ገንብቶ እና ለአዋ ሚካኤል የግንባታ የገንዘብ ድጋፍ አድርጎ ለአካባቢው ምእመናን መገልገያነት አስረክቧል፡፡



## ፫. ፭. የእደ ጥበብ ዘርፉ የሥራ እንቅስቃሴ

ይህ ዘርፍ የገዳሙ የልማት እንቅስቃሴዎች ሁሉ መነሻ መሠረት ነው፡፡በ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. በሁለት የሽመና እቃና በአንድ አሮጌ የስፌት ማሽን ሥራውን የጀመረው ይህ ዘርፍ በአሁኑ ሰዓት ገዳሙ ራሱ የሚሠራቸውን ጨምሮ በርካታ የሽመና

የሹራብ፣ የስፌት ማሽኖችን የያዘ ሁለት ሸድ በገዳሙ ውስጥ ያለው ዘርፍ ነው፡፡ የተለያዩ የባህል አልባሳት በማምረትና በመሸጥ ከፍተኛ ዕድገት ላይ ነው፡፡ በወልዲያ ከተማ የፋብሪካ መትከያ ቦታ ተሰጥቶት የነበር ቢሆንም ከገዳማዊ ሕይወት ጋር አጣጥሞ ለመሄድ ፈተና ይሆንብኛል ብሎ ስለሰጋ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ከገዳሙ የተመረቱ አልባሳትን መሸጫ በወልዲያ ፪ በመቄት ፩ በላሊበላ ፩ በደሴ በቅርብ ሥራ የሚጀምር ፩ ሱቅ አለው፡፡ በየሱቆቹ በየ፬ ወር የጊዜ ሠሌዳ አስቀምጦ የሽያጭ ባለ ሙያዎችን ይቀይራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለሌሎች ገዳማት የእደ ጥበብ ሥራ ሥልጠና በመስጠትና የመሥሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ሌሎች ገዳማትን ራሳቸውን እንዲችሉ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ያለ ዘርፍ ነው፡፡ ይህንኑ አገልግሎት በጥቃቅን ተደራጅተው ለሚመጡ ሠልጣኞችም የገዳሙን ሕግ አክብረው እስከ ኖሩ ድረስ ሥልጠና ይሰጣል፡፡ ገዳሙ ምንም እንኳ በዚህ ዘርፍ የራሱን ጉድለቶች ለመሙላት እንጂ ‹እሸለማለሁ› ብሎ ባይሠራም በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ሀገር አቀፍ ውድድሮች ላይ በመጋበዝ በሀገር ውስጥና በጎረቤት ሀገር ሱዳን ባዛሮችና ሲምፖዚየሞች በመገኘት ብዙ ሽልማቶችን፣ ዋንጫዎችን፣ ሜዳሊያዎችንና የምስክር ወረቀቶችን አግኝቷል፡፡



## ፫. ፮. የቴክኒክና የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሥራ እንቅስቃሴ

ይህ ዘርፍ በገዳሙ የሚገኘን ምርት ወደ መሸጫ ቦታ በገዳሙ ተሽከርካሪዎች ያደርሳል፣ ጋራዡ ባለው አቅም ልክ የተሽከርካሬዎችን ጥገና ያደርጋል ፡፡ በገዳሙ ውስጥ ያለውን ወፍጮ ጨምሮ በገለሶት በወይጣ ድባ በምርት ገለጎ ለማኅበረሰብ አገልግሎት የሚሰጡ ወፍጮዎችን ይሠራል ይጠግናል፡፡ የእደ ጥበብ ማምረቻ ማሽን ይሁን ሌላ ለገዳም አገልግሎት የሚውል ማሽን በሱ አቅም የሚሠሩትን ያመርታል፤ ጥገናዎች ያከናውናል፡፡ ከእንጨትና ከብረት የሚሠሩ መገልገያዎችን፤ በርና መስኮቶችን፣ ወንበርና ጠረንጴዛዎችን ያመርታል፡፡





## ፫. ፯. የሥነ ጽሑፍና የቅንብር ዘርፍ የሥራ እንቅስቃሴ

በዚህ ዘርፍ ለገዳማውያኑ የሚሆኑ የምስል ወድምፅ ምርቶችን አቀናብሮ ለማስተማሪያነት እያቀረበ የሚገኝ ቢሆንም ከገዳሙ ውጭ በዓለም ላሉ ክርስቲያኖች ወንጌልን ለማዳረስ እንዲረዳው በቀረጻና በማቀነባበር የሚሠሩ ባለ ሙያዎችን ወደ ተቋማት ልኮ እያስተማረ ይገኛል፡፡

## ፫.፰.የሒሳብ አያያዝ

✞. ከዘርፍ አደረጃጀት ውጭ ያለው የገዳሙ የሒሳብና ኦዲት ክፍል በየ አራት ወሩ ቆጠራና ርክክብ ያካሂዳል በየሲሶ ዓመት የሒሳብ ሥራ ይሠራል:: በዓመት አንድ ጊዜ ከሀገረ ስብከት በተላኩ ሦስት ኦዲተሮች ኦዲት ያስደርጋል::

በአጠቃላይ ሁሉም ዘርፎች የገዳሙ ገዳማዊ ሕይወትና ክርስቲያናዊ ተልእኮ በምንም ምክንያት ሳይስተጓጎል እንዲቀጥል በማድረግ በኩል የሚያሳዩት ትጋት ሁላችንም በገዳሙ ላይ ተስፋ እንድንጥል የሚያደርግ ነው::

## ፬. ገዳሙ እንዲሰፋና እንዲጠነክር አስተዋጽኦ ያደረጉ አካላት

ለገዳሙ መጠንከር ትልቁን ድርሻ የሚወስዱት ገዳሙ ወደ ቀድሞ ክብሩ እንዲመለስ ከ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ጀምሮ ብዙ የደከሙት የገዳሙ አበ ምኔት አባ ኪዳነ ማርያምና የገዳሙ ሁሉም መነኰሳትና መነኮሳይያት ናቸው:: ነገር ግን የእነሱን ትጋት በማገዝ በኩል ስንመለከት የገዳሙን ትጋትና የሥራ ባህል በተለያዩ ጊዜያት በየመድረኩ የሰሙት የአማራ ክልል ርእሰ መስተዳድር የነበሩት አቶ ገዱ አንዳርጋቸው መጋቢት ፯/፳፻፯ ዓ.ም ገዳሙን ጎብኝተው የገዳሙን ትጋት ካደነቁ በኋላ ከመንግሥት በኩል ምን እንዲደረግላቸው እንደሚፈልጉ ጠይቀው በተረዱት መሠረት የመንገድ፣ የውኃ፣ የመብራትና የተከዜ ወንዝ ድልድይ ጥያቄን አብረዋቸው ለመጡት የክልሉ የሥራ ኃላፊዎች ትእዛዝ በመስጠት ሥራው እንዲጀመር አድርገው ታኅሣሥ ፳፻፰ ዓ.ም. ላይ የውኃው ብቻ ሲቀር መንገዱም፣ መብራቱም፣ የተከዜ ተንጠልጣይ ድልድይም ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል:: በተለይ የተከዜ ተንጠልጣይ ድልድይ፣ የአባቶችንና የእናቶችን ገዳም ከማገናኘትም አልፎ ተከዜ ሲሞላ የሚለያዩትን የላስታና የመቄት ወረዳን ማገናኘት ተችሏል:: ገዳማውያኑንም በክረምት በውሻ ፖስተኛ ከመገናኘት በአካል ወደ መገናኘት አሸጋግሯቸዋልና ትልቅ እገዛ ነው:: በእደ ጥበብ በግብርና የሚያመርቱትን መርጠው የሚገዙም ደንበኞች ለገዳሙ ትልቅ እገዛ አድርገዋል::

## ፭. የገዳሙ የወደ ፊት ዕቅድ

ገዳሙ በ፳፻፴፪ ዓ.ም. ላይ ሊደርስበት ካሰበው ግብ ላይ ለመድረስ የሚያግዘው የ፳ ዓመት ዕቅድ አውጥቷል:: በዚህ ዕቅዱ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠባቸው ዐበይት ጉዳዮቹን ብንመለከት

✞. በአብነት ትምህርት በኩል ሁሉንም ጉባኤያት ያካተተ ት/ቤት ለመገንባትና አስፈላጊውን ግብአት ለማሟላት፤ የስብከተ ወንጌል ተልእኮ ተደራሽነትን ማስፋት፤

✞. በግንባታው በኩል በቀጭን አበባ የተጀመረውን የቤተ ክርስቲያን ዋሻ ፍልፈላና የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ግንባታ ማጠናከር፣ ከ፳፻፲፫ ዓ.ም. ጀምሮ የመነኰሳትና የተማሪዎች መኖሪያ በዓት ግንባታ፣ የመንገድ ሥራ ግንባታ፣ የመስኖና የመጠጥ ውኃ ግንባታ፣ የዓሣ ገንዳ ግንባታና የማምረቻ ቤቶች የማስፋፊያ ግንባታ እንዲሁም ለእንግዶች ማረፊያ አገልግሎት የሚሰጥ ከመናንያን በዓት የተለየ በገዳሙ መግቢያ አካባቢ የሚገነቡ የቤቶች ግንባታ፤

✞. በእደ ጥበብ ዘርፍ የማምረት አቅምንና ጥራትን በማሳደግ የምርት ተፈላጊነትን በማሳደግ በገዳሙ የማምረቻ ማስፋፊያ ማድረግ፣ ሌሎችንም መደገፍ፤

✞. በግብርናው ዘርፍ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርትን ማሳደግና ማስፋፋት፣ የመደብ እርከን በመሥራት የደን ሽፋንን በሰፊው ማሳደግ፣ የዓሣና የዶሮ እርባታ መጀመርና ጥሩ ምርትን ለገበያ ማቅረብ፣ የቋራውን የእርሻ ፕሮጀክት በሰፊው ማጠናከር፤

✞. በቴክኒክና ኢንዱስትሪ ዘርፍ የዘርፉን ክፍሎች በማጎልበት የገዳሙን ማንኛውንም የማምረቻ መሣሪያ በራስ አቅም ማምረትና ጥገና ማካሄድ፤

✞. በቤተ እግዚአብሔር ዘርፍ የገዳሙን አንድነትና ገዳማዊ ሕይወት አጠናክሮ ለማስቀጠል በቅርብ የተከለሰውን የገዳሙን ሥርዓተ ገዳም ማሳተምና ማንኛውም ወደ ገዳሙ የሚመጣ አካል በዚህ እንዲመራ ለማድረግ ሥራው የተጠናቀቀ ቢሆንም በዚህ የዕቅድ ዘመን ለኅትመት ገብቶ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ:: የገዳሙን አባቶችና እናቶች የማገልገሉ ተልእኮ ለምናኔ የሚመች አድርጎ አጠንክሮ ከማስቀጠል ባሻገርም የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የሆነውን የደከሙትን መርዳትን አጠንክሮ የሚያስቀጥልበትን መንገድ ማመቻቸት::

✞. የሥነ ጽሑፍና ቅንብር ዘርፉ እያሠለጠናቸው ያሉት የገዳሙ መናኝ ባለ ሙያዎች ከሥልጠና ሲመለሱ የስብከተ ወንጌል ተደራሽነቱን ለማስፋት ማደራጀትና የድምፅ፣ የድምፅ ወምስልና የኅትመት ሥራዎችን በሰፊው መሥራት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ የገዳሙ የ፳ ዓመት ዕቅድ ሰፊ፣ የገዳሙን ገዳማዊ ሕይወት የሚያጠናክርና ለሌሎችም ገዳማት ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡

**ገዳምውያኑ በጽኑ የገዳም አንድነትና ሥርዓት መኖራቸውን፣ ሁሉም መናኝ ከገዳሙ ሊያገኝ የሚችለውን እንክብካቤ እያገኘ መሆኑን፣ አረጋውያንና ታማሚዎች በትክክል ድጋፍና እንክብካቤ እየተደረገላቸው መሆኑን እና ገዳሙን ብለው የመጡ እንግዶች በተገቢው ሁኔታ መስተናገዳቸውን እየተከታተለ ገዳሙን አሁን ካለበት ደረጃ ላይ አድርሶታል፡፡**

## ፯. ገዳሙ ሊያስተካክላቸው የሚገቡ ክፍተቶች

✞. የአገሬው መንገድ በገዳሙ ውስጥ ያውም በመነኰሳት መኖሪያዎችና በአብያተ ክርስቲያናቱ አጠገብ በመሆኑ ገዳማዊ ሕይወትን ከመረበሽ አልፎ ለሌሎች ግጭቶች በር የሚከፍት እንደሚሆን ታውቆ ለሁሉም የሚመች መንገድ ቢቀየስ ፡፡

✞. ከገዳሙ ውጭም ይሁን ከገዳሙ ውስጥ አቅጣጫ ጠቋሚና ገላጭ ምልክት ባለመኖሩ ወደ ገዳሙ ለመግባትም ይሁን በገዳሙ ወስጥ ሥርዓተ ገዳሙን ጠብቆ በሥርዓት ለመንቀሳቀስ አስቸጋሪ ስለሚያደርገው የአቅጣጫ ጠቋሚና ገላጭ ምልክቶች ጉዳይ ቢታሰብበት፡፡

## ፰. ገዳሙ ገዳማት ላይ ለሚሠሩና ለሁሉም የቤተ ክርስቲያን አካላት ያስተላለፈው መልእክት

✞. በዐውደ ምሕረት ትምህርቶች፣ በሰንበት ት/ቤቶችና በግቢ ጉባኤያት ሥርዓተ ትምህርቶች፣ በክርስቲያናዊ ኮርሶች፣ በአብነት ት/ቤቶች እና በመሳሰሉት ላይ ስለ ገዳማዊ ሕይወትና ምናኔ ትምህርቱ ተካቶ ቢሰጥ፤

✞. ሕፃናትንና ወጣቶችን በመሰብሰብ የዕረፍት ጊዜያቸውን በገዳማት እንዲያሳልፉ በማድረግ ፍቅረ ገዳማዊ ሕይወት እንዲያድርባቸው ቢሠራ፤

✞. በገዳማት ዙሪያ ጥናት የሚሠሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የእናቶችንም ችግሮች ቢያጠኑት መልካም ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የተከዜ ምዕራፈ ቅዱሳን ቅ/ ኪዳነ ምሕረት፤ አቡነ ሐዋርያ ክርስቶስ አንድነት ገዳም ብዙ ቅዱሳንን ያፈራ ታላቅ ገዳም ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዘመናት ፈተና ተዳክሞ ለመበተን ደርሶ የነበረ መሆኑም ይታወሳል፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት በቅዱስ አቡነ ሐዋርያ ክርስቶስ ረዳትነት በትጉሃን መነኰሳትና መነኰሳይያት ብርቱ ጥረት በ፳ ዓመት ውስጥ ጥሩ ደረጃ ላይ የደረሰ ለሌሎችም አርአያ የሚሆን ገዳም ነው፡፡

*እግዚአብሔር አምላክ ገዳሙን በረድኤት ይጠብቅልን፡፡*

*በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን የሰ/ት/ቤቶች ማ/መ/*

*ማኅበረ ቅዱሳን*

*የወልዲያ ማእከል ቅዱሳት መካናት ዋና ክፍል ገዳማት ክፍል*

✞ ✞ ✞

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ



*በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን*



መምህር ግርማ ባቱ

*ውድ አንባብያን በጥያቄዎቻችሁ መልስ ዓምዳችን ወቅታዊውን የሀገራችረን ጉዳይ በተመለከተ የሚነሡ ጥያቄዎችን መሠረት አድርገን ምላሽ ይሰጡን ዘንድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑትን መምህር ግርማ ባቱን ጋብዘን። ቆይታችንን እንዲህ አዘጋጅተነዋል፤ መልካም ንባብ።*

***ሐመር፡-*** መምህር ወቅቱን መሠረት ያደረገና በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚነሡ ጥያቄዎችን መሠረት አድርገን ለምናነሣቸው ሐሳቦች ምላሽ ለመስጠት ፈቀደኛ ስለሆኑልን አስቀድመን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን።

***መምህር ግርማ ባቱ፡-*** እኔም ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።

***ሐመር፡-*** በሀገራችን እየተስተዋለ ያለው ጦርነት በቤተ ክርስቲያን እይታ ሲታይ ከምን የመጣ ነው ብለው ያምናሉ?

***መምህር ግርማ ባቱ ፡-*** ታሪኩ ረጅም ነው በተቻለ መጠን በአጭሩ ለመመለስ አሁን እየታየ ያለው ውጤት የረጅም ጊዜ ሂደት ነው። ሂደቱ ያስከተለውን የብዙ ችግሮች ውጤት ነው አሁን እየተመለከትን ያለነው። ይህም ማለት ለምሳሌ ላለፉት ከ፴-፵ ዓመታት ያህል ሀገሪቱ ስትከተለው የነበረው የፖለቲካ ሥርዓት፡-

ሀ. የቤተ ክርስቲያንን ሚና ያገለለና ቤተ ክርስቲያኒቱን እንደጠላት የፈረጀ ነበር ማለት ይቻላል። ቤተ ክርስቲያን የምታስተላልፈውን ትምህርቷን፣ ሥርዓቷን፣ ባህሏን በሙሉ የናቀው አካሄድ ይህን አላመጣም ማለት አይቻልም። የረጅም ጊዜ ሂደት የሚያሰኘውም ይህ ነው።

ለ. ይህን ካነሣን ዘንድ በእነዚህ የፖለቲካ ሥርዓቶች ውስጥ ደግሞ ሰዎች በእኩልነት ተከባብረውና ተረዳድተው ከሚኖሩበት የኑሮ መስመር ይልቅ ልዩነታቸው ላይ የሚያተኩሩበትን መስመር ማቀንቀን ስለነበር ይህ ሁሉ ተደማምሮ አሁን የምናየውን ችግር አስከትሏል።

ሐ. የኋላ ታሪክ አጻጻፋችን፣ አጠናናችን በተለይ ከመካከለኛው ዘመን ፲፯ኛው እና ፳፩ኛው ክፍለ ዘመን ለዘመናዊ ቀረብ ባሉ ጊዜያት የተጻፉ የታሪክ መጻሕፍት፣ የተሳሳቱ ትርክቶችን ደጋግሞ በማጠንጠን ብሔር ከብሔር እንዲጋጭ፣ ክልላዊ መዋቅሮች የበለጠ በተካረረና በተለያየ ሁኔታ እንዲቆሙ የተደረገበት የፖለቲካ ሥርዓት ለዚህ ትልቁን ዋጋ አስከፍሏል። ይህ እንደ መነሻ ከተጠቀምነው ዋናው ነገር ግን ሊታረቅ የማይችል ሆኖ ሳይሆን እንዳይታረቅ አስታራቂ የነበሩ አካላት ተገልዋል ከመድረኩም ወጥተዋል።

በአስታራቂነት ደግሞ ተቀዳሚ ሚና ስትወጣ የበረችው ቤተ ክርስቲያን ሚናዋን እንዳትጫወት፣ እንዳትወጣ የተደረገችበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ የቅርቡን እንኳ ብናነሣ በ፲፰፻፸ዎች ውስጥ በአፄ ዮሐንስና በአፄ ምኒልክ መካከል ትልቅ የተካረረ ጠብ ነበር። ወደ ጦርነት ይገባሉ የሚል ስጋትም ነበር። በዚህ መሀል ገብተው ጉዳዩን በእርቅ

የፈጽሙትና አፄ ዮሐንስንና አፄ ምኒልክን በአንድ ጉባኤ እንዲቀመጡ ያደረጓቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ናቸው፡፡

ወደ ኋላ እንሂድ ቢባልም በሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥትና የዛጉዌ ሥርወ መንግሥታት በሁለቱ መካከል ከፍተኛ ግጭቶች ይኖራሉ ተብሎ በታሰበበት በዚያ ጊዜ እንኳን እነ አቡነ ተክለሃይማኖት እነ አቡነ ኢየሱስ ሞዐ የሠሯቸው የአስታራቂነት ሥራዎች የቤተ ክርስቲያናችንን ተደማቀጩነትና የአስታራቂነት ሚናዎች በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ስለዚህ ይህ እየተካሄደ ያለው ጦርነት ከምን የመጣ ነው? ተብሎ ሲታሰብ ሰው በሰውነቱ አንድ ሆኖ ተከባብሮ እንዲኖር የምታስተምረው ቤተ ክርስቲያን የአደባባይ ሥራዋ የዐወደ ምሕረት ሚናዋም እንዲያው በማኅበረሰቡ ውስጥም ጠንክሮ ባለ መልኩ የምትጫወተው ሚና ተገፍቶ ሰዎች ተለያይተው እንዲቆሙ እየተፈቀደ ያለበት ሥርዓት ነው፡፡

**ሐመር፡-** ይህ እየተስተዋለ ያለው የእርስ በእርስ ጦርነት በቤተ ክርስቲያን ላይ ሊያስከትለው የሚችለው ችግር ምን ሊሆን ይችላል?

***መምህር ግርማ ባቱ ፡-*** የምንዘረዝራቸው ብዙ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ የጦርነት መልካም ነገር ወይም መልካም ውጤት የለውም፡፡ ጦርነት የመጨረሻ አማራጭ ነው፣ የህልውና ጉዳይ፣ በሕይወት መጠበቂያ፣ በአንድ ሀገር ውስጥ፣ የድንበር ማስከበሪያ ያም ሲከፋና አማራጭ ሲጠፋ የሚወሰድ ምርጫ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ምን ምን ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል የሚለውን ስንመለከት

፩. የሰው እልቂት፡- ጦርነት ሰላማዊነት ስለሌለው ደም አፍሳሽም ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ላይ ሊያስከትለው የሚችለው ችግር ብዙ ነው፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ መታወቅ ያለበት የሰው ልጆች አጠቃላይ ችግር የቤተ ክርስቲያን ችግር መሆኑ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሰው ልጆችን ሁለንተናዊ ደኅንነት ለማስጠበቅ የቆመች መንፈሳዊ ተቋም ናት፡፡ ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያስከትለው የመጀመሪያው ችግር ሰዎችን በአንድነት እንደ ኢትዮጵያዊነት እንዳይኖሩ ማድረግ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የአንድነት መሠረት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን በአንድነት ለማስተማር ወደ ድኅነት መንገድ ለመምራት በምታደርገው ጥረት ውስጥ የመጀመሪያው ችግር ግልጥ ሆኖ የሚታየው ሕዝቦች በተለያየ አቅጣጫ ቆመው ስላሉ አንድ አድርጋ ማስተማርና ሥርዓቱን መፈጸም የማትችል መሆኑ በዚህ ወቅት ከባዱ ችግር እርሱ ነው፡፡

፪. የቤተ ክርስቲያን ክፍፍል፡- አሁን እየተስተዋለ ያለውን ነገር እንኳን ብናይ አንዳንድ ፖለቲካውንም ሆነ ይህን የምናነሣውን ነገር እንደ ልዩነት በመቁጠርና አጋጣሚውን እንደ መልካም እድል በመጠቀም ጦርነቱ እየተካሄደ ያለባቸው አካባቢዎች ላይ የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን መሰል ተቋም ለማቋቋም እየተሯሯጡ ያሉ ሰዎች አሉ፡፡ ይህ ከፍተኛ ችግር ነው፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አሁን ጦርነቱ እየተካሄደበት ያለው አካባቢ የክርስትናውም ሆነ ከክርስትና በፊትም የብሉይ ኪዳን እምነት መሠረት የሆነችው አክሱም የምትገኝበት አካባቢ ነው፡፡ ጥንታውያኑ ቀደምት ቅዱሳት መካናት፣ ገዳማት የሚገኙትም በዚያው አካባቢ ነው፡፡ ከነዚያ አካባቢዎች ነው ብዙ ጊዜ ሥርዓት፣ ትውፊት፣ ታሪክ የሚመነጨው፡፡ ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ይህንን እንዳጋጣሚ በሚቆጥሩ አካላት ስትከፋፈል መታየቱ በምእምናኑም በሊቃውንቱም ልቡና ውስጥ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ እጅግ በጣም ከባድ ነው፡፡

፫. የሕዝቦች መከፋፈል፡- ቀጥሎ ደግሞ በጦርነቱ ማግስት እግዚአብሔር ፈቅዶና እግዚአብሔር ታድጐን በአጭሩ ከተቋጨ ይዘዋቸው የሚመጡ ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡ - ተቃርኖ ይፈጥራል፤ ሕዝብ ከሕዝብ ሊያቀያይም ይችላል፡፡ ምክንያቱም ነገሮችን ሰዎች ሁሉ በአንድ አቅጣጫ አይረዱምና፡፡ አሁንም እንደምናስተውለው ቤተ ክርስቲያኒቱን የአጥፊ ወገን አጋርና ተባባሪ አድርገው የሚመለከቱ አሉ፡፡ ያ ምን ድረስ ይቀጥላል እነዚያ ተንኮለኞችስ ሥራቸው ምንድነው? አካሄዳቸውስ በአሰቡት መልኩ ያስኬዳቸዋል ወይ የሚለውን አሁን ስለማናውቀው እንዲያው ብቻ እንደ ክፉ ጐን ቆጥረነው ልንሄድ እንችላለን፡፡

፬. የገዳማት መፍረስ፡- ገዳማት ሊፈርሱ ይችላሉ፡፡ የገዳማት መፍረስ በሁለት ወገን ሊከሠት ይችላል፡፡ የመጀመሪያው በቀጥታ ከአባቶች ሞትና እልቂት ጋር ተያይዞ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ጦርነት ነውና ምን ድረስ ጥንቃቄ ታክሎበታል የሚለውን ማወቅ ስለማይቻል ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው

ደግሞ በጦርነቱ ወቅት የሚቃጠሉና የሚወድሙበት ሁኔታ ሊከሠት ይችላል፡፡ ስለዚህ ገዳማቱ በቀጥታ በጦርነቱ ሲቃጠሉ የአገልጋዮችም ሕይወት በዚህ መልኩ ሲቀጠፍ ገዳማቱና አድባራቱ ሊፈርሱ ይችላሉ፡፡

፫. የምእመናንን ስደት፡- አሁንም እንደምንሰማው ብዙ ምእመናን ወደ ባዕድ ሀገር እየተሰደዱ ነው፡፡ የምእመናን ስደት በሃይማኖትም በባህልም ወደማይመስሏቸው ሕዝቦች እየተሰደዱ ስለሆነ የመጨረሻ ዕጣ ፈንታቸውን አሁን ላይ ቆመን አናውቀውም፡፡ ገና ወደፊት ታሪክና ውጤቱ የሚያመጣው የሚተነትነው ስለሆነ እንዲያው በቀላሉ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያመጣውን ችግር ማንሣት እንችላለን፡፡

***ሐመር፡-*** ቤተ ተክርስቲያን መዋቅራዊ የሆነ ጭቆና ሲደርስባት እንደነበር ይታወቃል፡፡ ምን አልባት ከዚህ ጦርነት በኋላ የተሻለ ለውጥ ሊኖር ይችላል ብለን ማሰብ የሚያስችል ነገር ይኖር ይሆን?

መምህር ግርማ ባቱ፡- ሌላ ትርጉም እንዳይሰጠው ጉዳዩን በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሆኖ ግን እንችላለን፡፡ ግልፁን ለመናገር አሁን የጦርነቱ ዋና ምክንያት የሆኑት ጥቂት ሰዎች (ቡድኖች) ላለፉት ፴-፵ ዓመታት በቤተ ክርስቲያን ላይ ትልቅ መከራ ሲደርስ የመከራው ምክንያቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እነርሱ ናቸው ብለን ማንሣት እንችላለን፡፡ በእነዚህ ቡድኖች ቤተ ክርስቲያን ጠላት ተደርጋ ተፈርጃለች፡፡ በግልፅ በየ አደባባዩ አንዳንዴ “እንዳታንሰራራ አድርገን መታናት ሲሉ” አንጓዴ ደግሞ “መጥፋት አለባት” ብለው ለወደፊቱ ሲተነብዩም ሲዝቱም የሰማንባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡

ስለዚህ መጨረሻውን የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው፡፡ ግን እግዚአብሔር ፈቅዶ እነዚህ ቡድኖች ለሕግ ቀርበው ጉዳዩም በሕግ ተይዞ መገሮች በሰላም ተቋጩ ብለን ብናስብ ቤተ ክርስቲያን የምታገኘውም እፎይታ አለ፡፡ በሌላ መልኩም ደግሞ እነዚህ ሰዎች የሚናገሩት እውነት፣ የሚያደርጉት ነገር ሁሉ እንዲያውም ለሀገር የሚበጅ መስሎት የሚከተለው ወገን ደግሞ አለ፡፡ ለዚህስ ምን ያህል ጉዳዩን አስተውሎ ለጥያቄዎቹ ሁሉ መልስ ሰጥቶ መስደድ ይቻላል? የሚለው አነጋገሪ ነገር ስለሆነ በጥልቀት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እነዚያም ተጐጂዎች ናቸውና፡፡ ነገር ግን እነርሱም እውነታው ገብቷቸው ወንጀለኞችም ለፍትሕ ቀርበው ጉዳዩ በሰላም ቢጠናቀቅ ቤተ ክርስቲያን እፎይታ ታገኛለች፡፡ ላለፉት የሕይወት መጥፋቶች፣ የካህናቱ ሞት እልቂት የአብያተ ክርስቲያናቱ መፍረስ መቃጠል ወዘተ እነዚህ ሁሉ ማን አመጣቸው ቢባል አሁን መረጃዎች ግልፅ እያደረጓቸው ነው፡፡

እነዚህን ካነሣን ዘንድ እነዚህን ችግሮች የሚያመጡ አካላት በሕግ ጥላ ሥር ሆኑ ማለት ቤተ ክርስቲያን እፎይታ ታገኛለች፡፡ ግን በአንድ አቅጣጫ እንዳናየው በየክልሉ የእነርሱን ሥራ የሚያስፈጽሙ ቅጥረኞች አሉ፡፡ ጉዳዩ ሰፊ በመሆኑና ዘላቂ ሥራ ከመጠየቁ አንጻር በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዳንመለከተው እንጂ ለጊዜው መጠነኛ እፎይታ ታገኛለች፡፡ ግን አሁንም እንዲሠመርበት የምፈልገው ጉዳይ ምን አልባት ዋናው ሰንኮፉ ከተነቀለ ሌሎቹ ግብር አበሮቹም አብረው ይጠፋሉ የሚለውን መውሰድ ይቻል ይሆናል እንጂ ሥራው ብዙ ጥረትን የሚጠይቅ ነው ፡፡

***ሐመር፡-*** ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለ ነገር ሲከሠት ሊኖራት የሚችለው ሚና በዘመናት ሲቃኝ ምን ይመስል እንደነበር ቢገልጹልን?

***መምህር ግርማ ባቱ፡-*** ቀደም ሲል በመጠኑ ለመግለፅ ሞክሬያለሁ፡፡ ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ ሁሉ ጎልቶ የተስተዋለው ሚናዋ አስታራቂነት ነው፡፡ አሁን ካለው ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በቀጥታ ለማገናኘት የቤተ ክርስቲያን ሚና አስታራቂነት፣ መካሪነት፣ መላሽነት ነው፡፡ አሁን በወቅታዊ ሁኔታ እንኳ በተቻለ መጠን ቤተ ክርስቲያን ያደረገቻቸው ጥረቶች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም፡፡ በሚጠቀሰው አካባቢ ማለትም ጦርነቱ ባለበት አካባቢ ሁሉ ምንም እንኳን ባይሳካላቸውም አባቶች ሄደዋል፡፡ በሁለቱም ወገን ሰዎችን ለመምከር ለመመለስም ጥረዋል፡፡ በታሪክ ውስጥ በተወሰነ አጋጣሚ ብናነሣውም ቀደም ሲል ያነሣኋቸው አጋጣሚዎችም አሉ፡፡

ቀደም ሲል በነበረው በአክሱማውያን ዘመናትም በነገሥታትና በመሳፍንት በመኳንንቱ መካከል በሚፈጠረው ግጭት በአመፀውና በሸፈተው ሁሉ መሀል እየገቡ እልቂት እንዳይፈጠር ሲያደርጉ ኑረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ነው የዛጉዌና የሰሎሞን ሥርወ መንግሥትና የአፄ ዮሐንስንና የአፄ ምኒልክን ግጭት እንደማሳያ አድርገን የጠቀስነው፡፡ ከዚያም ወደዚህ የቀረቡትን ሁሉ ማንሣት ይቻላል፡፡ እንዲሁ

በአጭሩ ለማንሣት ቤተ ክርስቲያን የአስታራቂነትና አንድ የማድረግ ሚና አላት። እንኳን እንደዚህ ችግሩ በግልጽ እየታየና ሀገራዊ ቀውሶችን እያስከተለ ይቅርና ችግር ከመፈጠሩ በፊትም ቢሆን ምንም እንኳን “መስማትስንስ ትሰማላችሁ ነገር ግን አታስተውሉም” ተብሎ እንደተነገረው ሰምቶ የሚያስተውል ትውልድ ቢጠፋም ሰላም የቤተ ክርስቲያን ታላቁ ጉዳይዋ ነው። አዘውትራ የምትሰብከው ዕለት ዕለት የምታስቀምጠው መሠረቷም ነው። ሁለቱ አካላት ማለትም መንግሥትም ሆነ ሕዝቡ ቤተ ክርስቲያንን ቢሰሙ ሀገራችን ለዚህ ችግር ባልተደረገች ነበር።

እንዲያው ነገሩን ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰው ልጅ ማንነት የምታስተምረው ትምህርት በራሱ በቂ ነው። መከባበርን፣ መተሳሰብን፣ በፍቅር መኖርንና መረዳዳትን ሰው ከሰው ያለውን ግንኙነት ይቅርና ከሥነ ምኅዳር፣ ከእንስሳት፣ ከአራዊት ወዘተ. ሁሉ ጋር ተስማምቶ መኖር እንደሚገባ የምታውጀው የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የተሠወረ አይደለም። ሚናዋን በዚህ መልኩ መቃኘት እንችላለን።

በአጭሩ ለማንሣት ቤተ ክርስቲያን የአስታራቂነትና አንድ የማድረግ ሚና አላት። እንኳን እንደዚህ ችግሩ በግልጽ እየታየና ሀገራዊ ቀውሶችን እያስከተለ ይቅርና ችግር ከመፈጠሩ በፊትም ቢሆን ምንም እንኳን “መስማትስንስ ትሰማላችሁ ነገር ግን አታስተውሉም” ተብሎ እንደተነገረው ሰምቶ የሚያስተውል ትውልድ ቢጠፋም ሰላም የቤተ ክርስቲያን ታላቁ ጉዳይዋ ነው።

***ሐመር፡-*** በቅርብ ቀን የሃይማኖት አባቶች በአካልም ተገኝተው ለማስማማት ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላም መግለጫ ማውጣታቸው ይታወሳል። ግን ብዙም ለውጥ አልመጣምና ተሰሚነታቸውን ያጡበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል?

***መምህር ግርማ ባቱ፡-*** ይህ በጣም መሠረታዊ የሆነው ጥያቄ ነው። በመጀመሪያ የቤተ ክርስቲያንን ድምፅ ለምን አልሰሙም? ሲባል ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ይመለከቷታል? እንዴትስ ይረዷታል? ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚሉት ነገርስ ምንድን ነው? የሚለው መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነው። ቀደም ሲልም መግለጽ እንደሞከርኩት እነዚህ ሰዎች አሁን እንዲህ ተካሮ ወደ ጦርነት ከመገባቱ በፊት ቤተ ክርስቲያን መጥፋት አለባት ብለው በግልጽ አነጋገር ፈርጀው አስቀምጠዋል። እስከመጨረሻው ድረስ መጥፋት አለባት ባይ ናቸው። መጥፋት አለበት ከሚሉትና እንደ ጠላት ከሚታይ ወገን የሰላምን ጥሪ ሊቀበሉ አይችሉም። በዋናነት ቤተ ክርስቲያንም ሆነች የሃይማኖት አባቶች ተሰሚነትን ያጡት ለምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ መልሱ እነዚህ አካላት አስቀድመው በጠላትነት ተፈርጀዋልና ተሰሚነትን ሊያገኙ አይችሉም የሚለው ነው።

ቤተ ክርስቲያን ደግሞ እውነታውን ስለምታውቅ ምንም ጠላት ቢያደርጓትም ሁል ጊዜም ሰላምን ትሰብካለች። ስለሰላም ጥሪ ማድረግ ደግሞ ካህናት ምእመናን ብለን መለያየቱ ይቅርና ለሁሉም የሚጠበቅበት ተግባር ነው። ምክንያቱም በአጠቃላይ ለሰው ልጅ አሁን ያለውን ጭፍጨፋና የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲመለከት ይህን አስከፊ ድርጊት ማውገዙ ተገቢ ነው። የመከላከያ ሠራዊት እየተባለ አሁን በሰፊው የሚነገረው ሀገር የሚጠብቅ ሕዝብን የሚታደግ ሠራዊት እርሱም ይቅርና ሰው በሰውነቱ እንዲህ ባለ ጭካኔ ሲገደል ቤተ ክርስቲያን ማውገዙ ትክልል ነው። ይህን ግን እነዚያ ወገኖች በምን አዩት ከተባለ አሁንም ከአንድ ወገን ወግኖ ለመቆም ነው። ይህ ከምን ጋር የተያያዘ ነው ስንል መጀመሪያ ከያዙት አቋም ጋር ቤተ ክርስቲያንን በምን አሰቧት በምን አዩአት ስንል በግልጽ የተናገሩት ካላይ ደጋግመን እንደ ተናገርነው መጥፋት አለባት የሚለውን አቋም ስለያዙ አሁንም ቢሆን የሰላም ጥሪዋን አይቀበሉም።

***ሐመር፡-*** በአሁኑ ሰዓት ይህን ጦርነት ከማረጋጋት አንጻር ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት የሚችለው ሚና ምን መሆን አለበት ይላሉ?

***መምህር ግርማ ባቱ፡-*** አሁንም የቤተ ክርስቲያን ሚናዋ አገልግሎቷ የታወቀ ስለሆነ ይህ ሆነ ተብሎ ጥረት አይቋረጥም፡፡ በችግር፣ በመከራ፣ በእሳት ውስጥም ቢሆን ጥረቱን መቀጠል አለባት፡፡ ቀደም ሲል አንድ አቅጣጫ ለመጠቆም ሞክረናል፡፡ እርሱም እነዚህ ወገኖች እግዚአብሔር ፈቅዶ ለሕግ ለፍትሕ ይቀርቡ ይሆናል፡፡ ግን መስሎት የሚከተል ደግሞ ስፍር ቁጥር የሌለው ብዙ ሕዝብ አለ፡፡ ይህንን ሕዝብ ማዳንም አሁንም የቤተ ክርስቲያን ቀጣይ ሚናዋ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያንን በዚህ በጠቆረ ፊት እና በተለየ ገጽታ መሳሉ እንዳለ ሁኖ ለራሳቸውም ሕይወት ለቀጣይም የሕይወት ዘመናቸው የሚበጀውን ነገር ለማወቅ የቤተ ክርስቲያን ሚና አሁንም ጠንክር ብሎ መቀጠል አለበት፡፡

ገፍቶ ማስተማር፣ እውነታውን ማሳወቅ፣ ይህ አገልግሎት መንግሥቱን ለመውረስና ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለመቀዳጀት ወይም ለሥጋዊ ድኅነት ብቻም ሳይሆን በታሪክም ሊወጡት የሚገባ፣ ይልቁንም እንደ ኢትዮጵያዊ አብሮ የመኖር ድርሻቸውንም ከማሳወቅ አንጻር ሥራው ጠንክር ብሎ መቀጠል አለበት እላለሁ፡፡ እንዲያውም ከቀደመው በተሻለ መልኩ መሠራት አለበት፡፡ ሕዝብ ከሕዝብ መታረቅ አለበት፡፡ የተለያዩ ወገኖች በፓርቲ ደረጃ የሚጠቀሱም በተለያየ መደብም ይጠሩ እንደ ሀገር ለመቀጠል የቤተ ክርስቲያን ሚና አሁንም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ነው እኔ የማስበው፡፡

***ሐመር፡-*** በግለ ሰብ ደረጃስ ምን ቢደረግ ብለው ይጠቁማሉ? ለምሳሌ ሰባክያነ ወንጌል፣ ዘማርያን፣ የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ወዘተ.?

***መምህር ግርማ ባቱ፡-*** መጀመሪያ መደረግ በሚገባው ጥንቃቄ ላይ የተወሰነ አስተያየት ሰጥቶ ማለፍ ጥሩ ነው፡፡ ጥንቃቄው ማለት ሰዎች ልብ ማለትም ያለባቸው ነገር ስለ አንድ ጉዳይ መናገርና ማራገብ መቻል ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ መቼና የት የሚለውንም ማየት በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ቤንዚን ይዞ ወደ እሳት መቅረብ አደጋው ከባድ ነው፡፡ ይህ እሳት የሆነ ዘመን ነው፡፡ በዚህ ወቅት ላይ የሚባለውንና የማይባለውን መለየት ትልቅ ዋጋ አለው ብዬ አስባለሁ፡፡ እኔ በዚህ ወቅት ላይ የብሔር ጉዳዮችን ማራገብ ልዩነቶችን ማቀጣጠል ምን ይፈይዳል? ብለን ብንጠይቅ ከፋይዳው ይልቅ ጉዳቱ ይከብዳል፡፡ መቼም ቢሆን ልዩነት ጥሩ ባይሆንም ከምንጊዜውም በላይ በዚህ ሰዓት የምንለያይበት ጊዜ አይደለም፡፡ ማተኮርና ጠንክረን መሥራት ያለብን ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ማስቀጠል የሚቻልበት ሐሳብ ላይ ነው፡፡ ይህን ደግሞ ማድረግ እንዲችሉ ሕዝቦቿን በአንድነት አስተባብሮና አስተሳስሮ የቀደመውን ጉልበት መመለስ የሚችሉበትን ሐሳብና አቅም ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡ እንደ ሰባክያን እንደዘማርያን እንደ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች እንዲሁም እንደ ኢትዮጵያዊነት በቡድን ወይም በግለሰብ መናገር የምችለው ከመቼውም በላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ጦርነቱና ጦርነቱን በተመለከተ የሚነገሩ ሐሳቦች ለትርጉም የተጋለጡ ናቸው፡፡ ሰዎች በተለያየ ሐረግ ሲገልጹ መታዘብ እንችላለን፡፡ በየማኅበራዊ ሚዲያው፣ የተለያዩ ጉዳዮች ይንጸባረቃሉ፡፡

ሁሉም በየብሔሩ የሚያደርገውን እንቅስቃሴና ልዩነትን የሚያሰፋውን ጉዳይ መናገርን ትቶ እንደ ሀገር በተለይ ደግሞ እንደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ የቤተ ክርስቲያን ባሕርይ ያልሆነው ጉዳይ ወደ ውስጣችን ሲገባ ይስተዋላል፡፡ በዚህ ሰዓት አጠንክረን መሥራት ያለብን ክርስቲያናዊ ማንነታችን በተለይም በምሥጢራት የተፈጸመውን ኅብረት በምሥጢራት ያደግንበትን እውነታ አስመልክቶ መሆን አለበት፡፡ እንደ ሰው ማሰብ ያለብንን ነገር ማጠንከር እንጂ ሌሎች ነገሮችን ማራገብ ወቅቱ ይፈቅድልናል ብዬ አላስብም፡፡ ሁሉም ወደዚህ መለስ ብሎ አንድነት ላይ ቢሠራ ሁሉም የቤተ ክርስቲያንን ዓላማ ቢያስፈጽም፣ ከግል ጉዳዮች ይልቅ ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ቢኖሩን እንኳ ወደዳር ብናቆያቸው አስፈላጊ ነው እላለሁ፡፡ አሁን ወቅታዊ ያልሆኑ ጉዳዮችም አብረው መጥተው የአገልጋዮች ፈተና በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ፈተና ሲሆኑ ይስተዋላልና ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል እላለሁ፡፡

***ሐመር፡-*** ሰዎች በብሔራቸው እየተገፉ ከመሆናቸው የተነሣ አጠቃላይ መንፈሱ ሕዝብን ከሕዝብ የሚነጥል እየሆነ ነውና ቤተ ክርስቲያን ከዚህ አንጻር ምን ማድረግ አለባት ብለው ያምናሉ?

***መምህር ግርማ ባቱ፡-*** አሁን ብዙ ወገኖች እየሰጡት ካለው አስተያየት እንነሣ፡፡ ቀደም ሲል እንዳልነው ዋናው የችግሩ ምንጭ ከደረቀ ርዝራዡ ይከስማል ወይም ደግሞ ይደርቃል የሚሉ አስተያየቶች በዚህ ሰሞን ተደጋግመው ሲነገሩ

ይሰማሉ። ግን በሀገራችን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ስናየው ችግሩ ከዚያ በላይ በጣም የሰፋ ይመስላል። ምክንያቱም ክፋቱን ከዋናው ምንጭ የወረሱት ሰዎች ሥራዬ ብለው የያዙትም ይመስላል። አሁን በተለይ ይህ የተጠቀሰው ችግር ማለትም ሰዎቹ በማንነታቸው ሲሳደዱ፣ ሲገደሉ በአጠቃላይ በርካታ ግፎችና በደሎች ሲደርስባቸው እንዲያው እነዚህ ሰዎች እኛ አይደለንም ቢሉ እንኳን በፍርድ በሕግ ጥላ ሥር ውለው ችግሩ ይከስም ይሆናል ወይም ይደርቅ ይሆናል ብለን ስናስብ የሚያጠራጥሩ ነገሮች አሉ።

ምክንያቱም ወራሾቹ ከአውራሾቹ በላይ ይዘው ለመቀጠል ያሰቡ ጠንክረው እየሠሩ ያሉም ይመስላል። ለዚህ ነው ቀደም ሲል የቤተ ክርስቲያን ሥራ ወይም ሚናዋ ምንድን ነው የሚለው ላይ ከጦርነቱ ማግስት እግዚአብሔር ፈቅዶ ጉዳዩ ሲያበቃ ከዚያ ማግስት ያሉ ሥራዎች ይህን በማመላከት ጠንከር ያሉ ሥራዎች መሠራት አለባቸው ያልኩት። ምክንያቱም ችግሩ በጣም ሰፍቷል፤ ተዛምቷል፤ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ የሚታይ ችግር ሁኗል። ስለዚህ በየክልሎቹ፣ ፍተሻ እንዲደረግ፣ ምን ያህል መሪዎች ማለትም ዋና ዋና የክልል ባለሥልጣናት፣ የየወረዳና የየአካባቢው ባለሥልጣናት እስከ ቀበሌ ድረስ ያለው መዋቅር መፈተሽ እንዳለበት የሚያመለክቱና የሚጠቁሙ ምልክቶች ናቸው። ስለዚህ ሰፋ ያሉ ችግሮች አሉ።

ስለዚህ ምንድን ነው መደረግ ያለበት? ቀጣዩ ሥራስ ምንድን ነው? ሲባል እውነት ለመናገር ለመንግሥት ባለሥልጣናትና ለፖለቲካ መሪዎች ብቻ እንዳንተው በውስጣችን ያለውንም መዘንጋት የለብንም። እንዲያውም ለእነርሱ ዕድሉን የሰጣቸውና ብርታት የሆናቸው በውስጣችን ያለው ችግርም ይመስለኛል። በእያንዳንዳችን ውስጥ የሠረጸውንና እየገፋ ያለውን ችግር እንደምንም በመፍታት አንድ ሆነን ቀሪውን ለሌሎች ማሳሰብ የሚኖርብን ይመስለኛል። እኛ ላይ ያለውን ችግር ከፈታን በኋላ ሌሎችን ደግሞ እስከ መንግሥት ድረስ በመድረስ ወርዶ ማነጋገር የመንግሥትንም አቋም መረዳትና እስከ ታች ድረስ የሚወርድ ሥራ መሥራት፤ ለተለየ ወገንና አካል መተውን ችላ ብሎ ቤተ ክርስቲያን ራሷ በኮሚቴም ይሁን ወይም ራሱን የቻለ አካል ተዋቅሮ ጉዳዩ ላይ ክትትል የሚደረግበትና ለቤተ ክርስቲያንም ይሁን ለሀገር የሚጠቅም ሥራ መሠራት አለበት ብየ አስባለሁ።

***ሐመር፡-*** በመጨረሻም እንዲያው ቀረ የሚሉትና ማስተላለፍ አለብኝ የሚሉት ሐሳብ ካለ ቢገልጹልን

***መምህር ግርማ ባቱ፡-*** ከጉዳዩ ስፋትና ውስብስብነት አንጻር ብዙ የምንታቀብባቸው ነገሮች አሉ እንጂ ብዙ የሚባሉ ጉዳዮችማ ነበሩ። የምንታቀብበት ምክንያትም የምንናገረው ሁሉ ለተለየ ትርጉም የመጋለጥ ዕድሉ የሰፋ ስለሆነ ነው። ይህንኑ ወደሌላ ወስደውና በሌላ መንገድ ቀይረው ለብዙ ዓላማ ሊያውሉት ስለሚችሉ በሚል ከብዙ ነገሮች እንድንታቀብ አድርጎናል እንጂ ከዚህም በላይ ብዙ የሚያስብሉ ነገሮች ነበሩ። በዋናነት ከተነሡት ጠያቄዎች አንጻር ግን የቀረ ያለ አይመስለኝም።

***ሐመር፡-*** መምህር ላካፈሉን ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስለሰጡን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን። እግዚአብሔር ያክብርልን።

***መምህር ግርማ ባቱ፡-*** አሜን እኔም ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ እግዚአብሔር ሁላችንንም ከዚህ መከራ ይጠብቀን።

**ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰው ልጅ ማንነት የምታስተምረው ትምህርት በራሱ በቂ ነው። መከባበርን፣ መተሳሰብን፣ በፍቅር መኖርንና መረዳዳትን ሰው ከሰው ያለውን ግንኙነት ይቅርና ከሥነ ምኅዳር፣ ከእንስሳት፣ ከአራዊት ወዘተ. ሁሉ ጋር ተስማምቶ መኖር እንደሚገባ የምታውጀው የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የተሠወረ አይደለም።**

# ግብረ ሰዶማዊነት

ክፍል ሁለት

## ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት

ዲ/ን ተስፋዬ አሰፋ

ውድ አንባብያን ባለፈው ዕትማችን ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት በሚለው ዓምዳችን ግብረ ሰዶማዊነትን በተመለከተ ክፈርል አንድን ማቅረባችን ይታወሳል:: ክፍል ሁለትን ደግሞ በአሁኑ ዕትማችን እናቀርባለን:: መልካም ንባብ::

### ዓለም አቀፍ የማስፋፍያ መንገዶች ምንድን ናቸው?

ማርሴል ክርክ እና ሀንተር ማድሰን የተሰኙ አሜሪካውያን የዚህ ድርጊት አስተባባሪዎች after the ball በተሰኘው መጽሐፋቸው ለማስፋፋት መጠቀም ያለባቸውን ዘዴ በትክክል አስፍረው ዛሬም ድረስ ተግባራዊ እየሆነ ነው:: (፲፱፻፹፱)

፩. ስለ አኗኗራቸው ምንም ነገር እንዳይነሣና እንዳይወራ ማድረግ::

፪. ቃሉን ደጋግሞ ለጆሮ ማለማመድ:- ዛሬ ቃሉ ሲነገር እንደ ነውር የምንደነግጠው ነገር ቀርቷል ይህ የእነሱ የሥራ ውጤት ነው:: ሚዲያን፣ መንግሥታትን፣ ታዋቂ ሰዎችን በመግዛት ወደ ፊት እየመጡ ነው::

፫. ግብረ ሰዶማውያን በዓለም የተጎዱ የተገፉ አድርጎ ማቅረብ:: የታቀደ ድብደባ እንዲደረግባቸው በማድረግ ዓለም እንዲያዝንላቸው ቁስላቸውን በማሳየት አማኝ ኀሊና መግዛት::

፬. ማኅበራዊ ፍትሕ እንደ ተነፈጋቸው አድርጎ ማቅረብ :- ጉዳዩን ከመብት፣ ከሰብኣዊ መብት (human right) አንጻር እንዲታይ መንግሥታትን መቃወም፣ ማሳመን፣ በአሜሪካና መሰል ሀገሮች ወንጀል መሆኑ እንዲቀር ከማድረግም ባለፈ ሰብኣዊ መብት እንደ ሆነ አድርጎ ማቅረብ:: united nations ካስቀመጣቸው የሰብኣዊ መብት ውሳኔዎች (human right declaration) አንዱ ቤተ ሰብ ለኅብረተ ሰብ ዋና ምሰሶ በመሆኑ ከፍተኛ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል የሚል አንቀጽ አለው:: ሆኖም ግን ግብረ ሰዶማዊነት ይህን የሚጻረር ሆኖ እናገኘዋለን::

፭. ዓለም አቀፍ የቱሪዝም፣ የስፖርት፣ የቱሪስት እንዲሁም ትልልቅ ኮንፈረንሶችን መጠቀም:- ኅዳር ፳፭/ ፳፻፬ ዓ.ም. የተካሄደው ICASA በሚል መጠሪያ የሚታወቀው ከተላላፊ በሽታዎች ጋር በተያያዘ የተደረገ ስብሰባን ምክንያት በማድረግ ስብሰባ ለማድረግ እንቅስቃሴ ጀምረው ነበር:: በሀገራችን ኢትዮጵያም በ፳፻፲፩ ዓ.ም. የቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናትን ለመጎብኘት በሚል ሰበብ ለመምጣት አቅደው አልተሳካላቸውም፤ ሌሎቹንም የስፖርት ውድድሮች፣ የቱሪስት መዳረሻዎች በመጠቀም ለመስፋፋት ይጠቀሙባቸዋል::

፮. ታዋቂ ሰዎችን፣ የሕክምና ባለ ሙያዎችን፣ የሃይማኖት ሰዎችን በገንዘብ የዓላማቸው ማስፈጸሚያ ማድረግ :- በጥናት የተደገፈ፣ እውነት የሚመስል መረጃዎችን በእነዚህ ሰዎች እንዲቀርቡ በማድረግ እሱ ይህን ካደረገ እኔም ብሎ ሰውን ለማሳመኛ ይጠቀሙበታል::

፯. ታዳጊ ሕፃናትን በመድፈር በዚህ ኀጢአት ማሳደግ:- ብቸኛ የሆኑ፣ ከቤተሰብ ፍቅር ያጡ፣ የገንዘብ ችግር ያለባቸው፣ በአእምሮ ሕመም የተጠቁ (ጉዲፈቻን ጨምሮ) ሕፃናትን በመድፈርና የማንነት ቀውስ ውስጥ እንዲገቡ ካደረጉ በኋላ ማንነቴ ነው ብለው እንዲያምኑ ያደርጓቸዋል ከዚህም ባሻገር ይህንን ዓላማቸውን በሌሎች ላይ እንዲያሰርጹ በተለያዩ ሀገሮች ያሰማሯቸዋል::

### ግብረ ሰዶማዊነት ባለንበት ዘመን ተፅዕኖው ምን ያህል ነው?

የአዲሱ ዓለም ሥርዓት አራማጆች (The new age movement) ግብረ ሰዶማዊነትን ከሰው ልጅ መብት ጋር በማገናኘት ሕጋዊ ዕውቅና መስጠቱን ተያይዘውታል:: ኀጢአት ነው፣ ጸያፍ ነው፣ ግብረ ገባዊ አይደለም፣ ተፈጥሮን ይጻረራል ከማለት ይልቅ ይህ የሰዎች ግላዊ መብት እንደ ሆነ፣ ድርጊቱን የሚቃወሙትም መብትን ተጋፊዎች እንደ ሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ:: ሳይንሱንም የራሳቸው መሣሪያ

ማድረግ ጀምረዋል፡፡ በማያልቁ የውሸት መላምቶች የወጣቱን አእምሮ ለመቀየር ግብረ ሰዶማዊነትን ለማበረታታት የጾታ አተያይ (sexual orientation) ተቃራኒ ጾታን ብቻ ሳይሆን ‹ሌላ የጾታ ዓይነት አለ› ብለው ለማሳመን ጥረት ያደርጋሉ፤ ያታቸውንም ይቀይራሉ፡፡

ሌላው በግሪክ እና በሮማ ሥልጣኔ ዘመን የነበረው የፍልስፍናው ዓለም በጥቂቱም ቢሆን ተፅዕኖው ተጠቃሽ ነው፡፡ የግሪክ ፍልስፍና አንድ ሰው ለቅዱስ ጋብቻ ስላለው አመለካከት የተለየ አስተምህሮ መኖሩ ይህን ኀጢአት ውስጥ ውስጡን ከቤተ መንግሥት ነገሥታት ጀምሮ ለማስፋፋት አስችሏል፡፡ በሩማንያ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የሆኑት አንቶን አዳአሙት philosophical aspect of homosexuality in ancient Greek በሚለው ጥናታዊ ጽሑፋቸው አፍላጦንም (ፕላቶም) ሆነ አርስጣጣሊስ (አሪስቶትል) ቆይተው በሐሳባቸው ቢፀፀቱበትም በጊዜው የነበረውን ማኅበረ ሰብ ያስተምሩት በነበረው ትምህርት ላይ እንዲህ ብለው ነበር የገለጹት «everything is allowed since it is natural, and what is natural goes beyond the frame of family, thus Greek love lives completely outside marriage and family - ምንም ነገር ተፈጥሮአዊ እስከ ሆነ ድረስ የተፈቀደ ነው፤ ተፈጥሮአዊ የምንለው ሐሳቡ ቤተ ሰብን ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ ያለፈ ነው፡፡ ይህ ማለት ፍቅር በግሪካውያን ዘንድ ከጋብቻ እና ቤተ ሰብን ሳያካትት ከዚህ ውጭ ነው» ብሏል፡፡ (Anton ADAMUT, Philosophical aspect of Homosetuality in ancient Greek, p 11 ) ይህ ደግሞ ቅዱስ የሆነውን ጋብቻ ከመቃወሙም በተጨማሪ ለፍትወታዊነት እና መሰል እንስሳዊ ተግባራት ውስጥ ራሳችኹን ዝፈቁ እንደ ማለት ነው፡፡

በዚህ ዘመን ያለ ወጣት በዚህ መሰል ፍልስፍና እንዳይወሰድ ማስተማር የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ነው፡፡ እነዚህ አካላት የታሪክ መዛግብትን በማዛባት የራስን ታሪክ መጻፍም ተያይዘውታል በግሪክ እና ሮማ ሥልጣኔዎች ወቅት የነበሩ ጥንታዊ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን ለመሰል ዓላማቸው በመጠቀም ያልነበረውን ነበረ፤ ያልሆነውን ሆነ ብሎ መጻፍም ጀምረዋል፡፡ ይህም የጥበብ አፍቃሪ የሆነው ወጣት ወደ ኋለኛው ዘመን ተመልሶ ዕውቀትን ሲፈልግ እገሌም ግብረ ሰዶማዊ ነበር፤ እከሌም እንዲህ ነበር የሚሉ መረጃዎችን በማካተታቸው በቀላሉ ግብረ ሰዶማዊነት ጽንሰ ሐሳብ ከታሪክ እና በጊዜው ከነበሩ ልሂቃን ሕይወት ጋር አስተሳስረው ዝነኞቹንና ታላላቆቹን በማድነቅ ወጣቱ ትውልድ ሐሳቡን እንዲቀበለው ማድረግ ሌላኛው መንገዳቸው ነው፡፡

ለማሳያ ያህል ዘጋርዲያን በተሰኘው ጋዜጣ ጀምስ ዳቪድሰን በተባለ ግለሰብ በፈረንጆቹ ፳፻፯ ላይ በጻፈው Mad about the boys በተሰኘ ጽሑፍ በታዋቂው የግሪክ የሥነ ጽሑፍ ሰው ሆሜር ሥራዎች ውስጥ አኪሊስ (Achilles) እና ፓትረክለስ (Patroclus) የተሰኙ ገጸ ባሕርያትን ደራሲው ባላስቀመጠበት መንገድ የነበራቸውን የጠበቀ ወንድማዊ ግንኙነት እነሱ በፈለጉት መንገድ የተለየ ትርጉም ሰጥተው ማስቀመጣቸው ጥንታዊ የታሪክ ድርሰቶችን ከላይ ላነሣነው ድብቅ ዓላማ ማስፈጸሚያ ለማድረግ የታቀደ ነው፡፡

> **በዚህ ዘመን ያለ ወጣት በዚህ መሰል ፍልስፍና እንዳይወሰድ ማስተማር የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ነው፡፡ እነዚህ አካላት የታሪክ መዛግብትን በማዛባት የራስን ታሪክ መጻፍም ተያይዘውታል በግሪክ እና ሮማ ሥልጣኔዎች ወቅት የነበሩ ጥንታዊ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን ለመሰል ዓላማቸው በመጠቀም ያልነበረውን ነበረ፤ ያልሆነውን ሆነ ብሎ መጻፍም ጀምረዋል፡፡**

ሌላው በዚህ ዘመን በታሪክ ምዕራፎች ውስጥ ተሰሚነት ለማግኘት ወጣቶችን በዚህ ኀጢአት ለመማረክ የሆሊውድ ፊልሞች ገና ከጅምሩ በፊልሞቻቸው የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት በከፍተኛ ሁኔታ ሲያስተዋውቁት ሲሠሩበት ኖረዋል፡፡ እ.አ.አ ፲፱፻፺ ወዲህ ግን ሊገመት በማይችል

ፍጥነት በየፊልሙ ውስጥ ሆነ ተብለው ተካትተዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ፊልሞች በዘመናት ታሪክ ውስጥ በተመልካች ዘንድ የሚፈጥሩት የአመለካከት ለውጥ ከባድ ነበር፤ አሁንም እየሠሩበት ነው፡፡ በንግድ ዕቃዎች፣ ቲሸርቶች፣ የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች፣ ዘፈኖቻቸው ላይ ዓላማቸውን ያስተዋውቃሉ፡፡ የራሳቸው ቀለም የበዛበት ባንዲራ አጽድቀዋል፡፡ እንደ አሜሪካ መንግሥት ባሉ መንግሥታት ውስጥ ደግሞ በሕገ መንግሥት ደረጃ የእርስ በእርስ ጋብቻቸውን አስፈቅደዋል፡፡

አሁን፣ አሁን በመድረኮቻቸው ላይ በግልጽ ግብረ ሰዶማዊ መሆናቸውን የሚመሰክሩ የራሳቸው ማንነት እንደ ሆነ የሚቆጥሩ ታዋቂ ሰዎች መስማት ከጀመርን ውለን አድረናል፡፡ ይህ ነገር በይነ መረብ (Internet) ላይ ረጅም ሰዓት አፍጥጠው በሚውሉ እና ነገ በሚፈጠሩ ሕፃናት አእምሮ ውስጥ የሚፈጥረው ግራ መጋባት እንዲህ ቀላል አይደለም፡፡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ በተቃራኒ አእምሯቸውን ለማይረባ ነገር አሳልፈው ስለ ሰጡት ይህን መሰል ነገር ማሰባቸውን ሳይሆን ኑሮአቸው እውነት እንደ ሆነ እና ማንነታቸውን (identity) ማመናቸው ሌላው ተግዳሮት ነው፡፡ አሜሪካ ውስጥ የሚገኙ አብዛኞቹ የፕሮቴስታንት አዳራሾች ግብረ ሰዶማዊነት ይሰበክባቸዋል፡፡ ነገ ከነገ ወዲያ ደግሞ እኛ ሀገር ውስጥ ያሉት ተከታዮቻቸው የዚህ ኃጢአት ዓላማ ማስፈጸሚያ የማይሆኑበት ምንም መተማመኛ አለመኖሩ ሀገራዊ ስጋት እንዲደቀንብን ያደርጋል፡፡ ሲያልፍም መንግሥታት በቤተ ክርስቲያን ላይ ተላላኪዎቻቸውን በገንዘብ በመግዛት የሚፈጥሩት ጫና መነሻቸው በእነሱ በኩል መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

## እንዴት እንከላከለው?

### አብርሃማዊ ምልጃ እና ሎጣዊ አርአያነትን በመከተል

ሰዶማውያንን መጽሐፍ ቅዱስ «ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኀጠአተኞች ነበሩ» ብሎ ነው ሚገልጻቸው (ዘፍ. ፲፫፥፲፫)፡፡ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር የምትጸልየው ስለዚህ ሁሉ ነው፡፡ የዚህ አካል የሆነው አበ ብዙኃን አብርሃም ስለ ክፋታቸው እግዚአብሔር እንደሚያጠፋቸው ስለ ተረዳ በበፊቱ ቁሞ «በውኑ ጻድቁን ከኀጠአተኛው ጋር ታጠፋለህን? ከተማይቱንም በእርስዋ ስለሚገኙ ኀምሳ ጻድቃን አትምርምን?» (ዘፍ. ፲፰፥፳፬) ከኀምሳ ጻድቃን ጀምሮ አሥር ደረሰ፡፡ ጻድቅ ሰው አልተገኘባትም፡፡ እንደ ሀገር፤ እንደ ቤተ ክርስቲያን ስለ እነዚህ ሰዎች ኀጢአት እንዳንጠፋ መጸለይ እነሱም በንስሓ እንዲመለሱ ወደ እግዚአብሔር በምሕላ መጮህ፤ ማልቀስ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ በመካከላቸው እየኖረ በድርጊትም በሐሳብም ከኀጢአት እንደ ተለየው ሎጥ ብርቱ የሆነ የክርስትና መሠረት ያስፈልገናል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በአመፀኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበርና በአመፀኞች ሴሰኛ ኑሮ የተገፋውን ያን ጻድቅ ካዳኑ፥ ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን በደለኞችንም ይልቁንም በርኵስ ምኞት የሥጋን ፍትወት እየተከታተሉ የሚመላለሱትን ጌትነቱንም የሚንቁትን እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዴት እንዲጠብቅ ያውቃል» ብሏል፡፡ ሳናውቀው ግብረ ሰዶማዊ ሐሳብን ከሰው ልጅ መብት፤ ከፖለቲካ ትርፍ፤ ከግል ጥቅምም አንጻር የምናይ ሰዎች ማሰባችን ከሎጥ ነፍስን ማስጨነቅ በላይ አይሆንምና መለየት ያስፈልገናል፡፡ (፪ጴጥ.፪፥፯-፱)፡፡

### ሕፃናትን በመጠበቅና በማስተማር

ሕፃናት አሁን ባሉበት የዕውቀት ደረጃ እና ከእኛ በተሻለ ዓለምን የሚረዱበት መንገድ ከእነሱ ጋር ቁጭ ብሎ ለመነጋገር የሚያስችል አይደለም፡፡ በሚያዩት ፊልም በሚሰሙት ሙዚቃ አእምሯቸው ተቀይሯል፡፡ ይህም በጓደኞቻቸውና በአካባቢያቸው ተጽእኖ የመጣ ስለ ሆነ ይህ የቴንም ያህል ጊዜ ይፍጅ የእነሱን ዓለም መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ከመናገር በፊት እናዳምጣቸው፡፡ የቀን ውሏቸውን መገምገምና ከእነርሱ ጋር በነፃነት መወያየት ያስፈልጋል፡፡ የቅድመ ጥንቃቄ ሕጎችን በተገቢው ሁኔታ እንዲገነዘቡ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ችግር ቢደርስባቸው እንኳን የድረሱልኝ ጥሪ እንዲያሰሙ የቤተ ሰቦቻቸውን እና የፀጥታ አካላትን ስልክ ቁጥር በቃላቸው እንዲይዙ ማድረግም አንዱ የመፍትሔ አማራጭ ነው፡፡ ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ብናበረታታቸው የሚባሉትን ሁሉ በፀጋ ከመቀበል ይልቅ ለምን የሚሉበትን አቅም ይፈጥርላቸዋል ፡፡ ዝም በል ዝም በይ ማለት ግን መፍትሔ አይሆንም ፡፡ በዋናነት ደግሞ ምንም ከባድ ቢሆንም ከሁሉ በላይ ግን ግብረ ሰዶማዊነት ምን እንደ ሆነ ቅዱሳት መጻሕፍትን እየጠቀስን በቀላል ቋንቋ ልናስረዳቸው፣ መሰል አመለካከት ያለውን ሰው የሚለዩበትንም መንገድ ልናሳያቸው ይገባል ፡፡ በተለይ ሕጻናትን ለትምህርት ውጭ ሀገራት ልከ

ማስተማር ልጆቹ ጠንካራ ሥነ ልቡና እና ግንዛቤ እስከ ሌላቸው ድረስ በዚህ መሰል ኀጢአት የመጎዳት አቅማቸው የከፋ ነውና ልናስብበት ይገባል፡፡

በጉድፈቻም ሆነ በሌሎችም ምክንያቶች ከሀገር የሚያስወጡ አካላት ዝንኞች ስለ ሆኑ፤ አቅሙ ስላላቸው አሳልፎ መስጠት እየተለመደ መጥቷል፡፡ ነገ ከነገ ወድያ ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለታቸውና ሕዝብና ሀገርን ያሳደገች ቤተ ክርስትያንን ማሰደባቸው የማይቀር ነው፡፡ ልጆቻቸውን ከቤተ ክርስትያን ሳያስቀሩ በግብረ ገብ ትምህርት አልፎም ተርፎም ለዲቁና ከዚያም ከፍ ለሚል የክህነት አገልግሎት ለአገልጋይነት ያበቁ ዲያስፓራ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ ሁሉ አደራቸውን ያልተወጡትን ደግሞ ቤት ይቁጠራቸው፡፡ አንድ ሕንዳዊ ወጣት ከሀገሩ ሲወጣ የሀገሩን ባሕልና ወግ ይዞ እንደ ሄደ ሁሉ ሲመለስም ይዞት ይመጣል፡፡ ይህ የወላጆቹ ተጽእኖ ነው፡፡ በእኛ ሀገር ይህ የማይታሰብ እስኪመስል ድረስ ቦላሌውን ጥሎ የሰው ቀሚስ አድርጎ ሻሹን ግጥም አድርጎ አስሮ ምኑም ሳይገባው ሰንሰለትና ጆሮ ጌጥ ማድረግ ሥልጣኔ ይመስለዋል፡፡ እኛም አይተን ዝም፤ ነገም ዝም ካልን ነውር የሆነ ነገርን የሚከለክለውን ኢትዮጵያዊ ባሕል አክብረን ማስተማር ካልቻልን ችግሩ ይከፋል፡፡

> **አንድ ሕንዳዊ ወጣት ከሀገሩ ሲወጣ የሀገሩን ባሕልና ወግ ይዞ እንደ ሄደ ሁሉ ሲመለስም ይዞት ይመጣል፡፡ ይህ የወላጆቹ ተጽእኖ ነው፡፡ በእኛ ሀገር ይህ የማይታሰብ እስኪመስል ድረስ ቦላሌውን ጥሎ የሰው ቀሚስ አድርጎ ሻሹን ግጥም አድርጎ አስሮ ምኑም ሳይገባው ሰንሰለትና ጆሮ ጌጥ ማድረግ ሥልጣኔ ይመስለዋል፡፡**

## የወንጀል ሕጎቻችን እንዲጠበቁ ግፊት ማድረግ

በጥንት አቴናውያን ሕግ በዚህ ኀጢአት የወደቀ፤ የተያዘ ሰው የመምረጥ የመመረጥ፤ በፍርድ ቤት ስለ ራሱ የመከላከል መብት የለውም፡፡ ( Douglas M.MacDowell, Athenian laws about homosexuality ,university of Glasgow ,p 23) ይህ ማለት በሕግ ደረጃ ዓለም አቀፋዊ ወንጀል ወይም ነውር ነው ማለት ነው፡፡ በሀገራችን ፲፱፻፺፮ በወጣውና ፲፱፻፺፯ በታተመው የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፮ ጠቅላላ ድንጋጌው ላይ ክፍል ፪ ግብረ ሰዶምና ለንጽሕና ክብር ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች ድርጊቶች በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር በዝርዝር ወንጀል መሆኑን እና የሚያስከትለውን ቅጣት ከ፲፰ ዓመት በታችና ከ፲፰ ዓመት በላይ ለሆነ ዕድሜ አስቀምጧል፡፡

በማኅበረ ሰቡ ዘንድ ኢ-ግብረ ገባዊ (ኢ- ሞራላዊ) መሆንን ከግምት ውስጥ አስቀምጦ ወንጀለኛው ለፈጸመው አስነዋሪ ተግባር ቅጣቱን የሚያከብዱ ጠቅላላ ሁኔታዎችን ለምሳሌ የተጎጅን የገንዘብ ችግር፤ የኀሊና ኃዘን፤ አሠሪው፤ ሞግዚቱ ከሆነ፤ ወይም ሥልጣኑን ተጠቅሞ አስነዋሪ ግብረ ሰዶማዊነት ከፈጸመበት ከ፩ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከባድ ሁኔታ ሲያጋጥም ከ ፲ ዓመት በማይበልጥ ጽኑዕ እሥራት ይቀጣል፡፡ ሕጉ «በቀላል እሥራት ይቀጣል» የሚለው ሐረግ ቅጣቱ ቀላል ከሆነ ለወንጀለኛ የሕግ መከራከሪያ ክፍተት ያገኛል፤ ድርጊቱንም አቅልሎ ለማየት አጋጣሚ ያገኛል፡፡ በተለይ አንቀጽ ፮ ቁጥር ፴፩ ላይ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ልጆች እና ፲፰ ዓመት ባልሞላቸው ላይ ለሚፈጸም ግብረ ሰዶማዊነት ቅጣቱ ከ ፲፭ አመት እስከ ፳፭ ዓመት የሚያስቀጣ ነው ይላል፡፡

ሕጎችን ባጠበቅናቸው ቁጥር ወንጀለኞች ቅጣቱን በመፍራት ሕጉን የማክበር አዝማሚያ ከፍ ያለ ነው፡፡ ከላይ ያየናቸው ቅጣቶች ከግብረ ሰዶማዊነት የወንጀል ክብደት አንጻር ቅጣቱ ያንሳል እንጂ አይበዛም፡፡

አሁን ባለው የግብረ ሰዶማውያን የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ከላይ የተቀመጠው ሕግ «በቀላል እሥራት ይቀጣል» የሚለውን ዓረፍተ ነገር ጨምሮ በቀላል እሥራት መባሉ በራሱ ለድርጊቱ ፈጻሚዎች የልብ ልብ መስጠት ነው፡፡ በሕጉ ላይ የሰፈሩት ቅጣቱን የሚያከብዱ ጠቅላላ ሁኑታዎች

የሰፈሩት ጉዳዮች ጠንካራ ቢሆኑም እርሱን ተከትሎ ግን ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት የሚለው ሐረግ ቅጣቱን የሚያከብዱ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንጻር ቅጣቱ የማይመጣጠን ሆኖ እናገኘዋለን። በተለይ አካለ መጠን ባልደረሱ ሕጻናት ላይ ለሚፈጸም ወንጀል የተቀመጠው ቅጣት ከወንጀሉ ክብደት አንጻር ትንሽ ነው። ዕድሜ ልክ የማይጠፋ መጥፎ ጠባሳ በሕፃኑ ላይ ያደረሰ አካል ዕድሜ ልክ የማይቀጣበት ምንም ምክንያት የለም። እነዚህ ሕጎች እንዲጠበቁ፤ እንዲሻሻሉ መንግሥት ካላደረገ፤ የሚመለከታቸው አካላት ካህኑ ካልጮሁ ግብረ ሰዶማውያን የሕጉን ቅለት ተጠቅመው ሕጋዊ ሰውነት ይዘው ነገ ከነገ ወድያ ፍርድ ቤቶችን እንደ ሌሎች ቀላል ወንጀሎች ቆመው የማይከራከሩበት ሕጋዊ ድጋፍ የማያገኙበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

ስለዚህ የወንጀሉን ክብደት በሚመጥን መልኩ ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል ። ኅብረተሰቡ የሕጉን መጥበቅ ተከትሎ ወንጀለኛን ማጋለጥ፤ ለፍርድ ማቅረብ የሚቻልበትን አቅም እንገነባለታለን። ይህ ካልሆነ ምንም እንኳ በዚህ ርኩሰት የተጠቃ አካል ወንጀሉ ቢፈጸምበትም ነገ የሚደርስበትን መገለል በመፍራት አደባባይ ወጥቶ እንደዚህ ተደረገብኝ ማለት ይከብደዋል። ነገር ግን በዚህም ምክንያት ሕጉ የሰጠውን ከለላ በመጠራጠሩ ልጁ ወይም ጎረቤቱ እንደዚህ ሆነ ብሎ ደፍሮ ስለማይናገር ወንጀለኛው በቀላል እሥራት ሊታለፍ የሚችልበት ዕድል ሰፊ ነው። በግልጽ ወንጀለኛነቱ እየታወቀ እገሌ እኮ እንደዚህ ነው እንደዛ ነው እየተባለ በሹክሹክታ ከማውራት ውጭ በአደባባይ እገሌ ይህን ፈጽሟል ማለት ከብዷል። ምክንያቱ ደግሞ በአንድ በኩል አጸያፊነቱን አስበን ዘግንኖን በሌላ መልኩ ግን ሕግ ባለበት ሀገር ፈርተን ነው ከማለት ውጭ ምን ልንል እንችላለን።

መፍትሔው በየጎዳናው ይህን ያደረጉ ወንጀለኞችን በተባበረ ክንድ ማጋለጥ፤ ለፍርድ ማቅረብ ነው። ይህንን ማድረግ አለመቻል ከሚመጣው ትውልድ ከመወቀስ አያድነንም። ሳይቃጠል በቅጠል የምንልበት ጊዜ አልፏል አሁን እንደሰደደ እሳት ሳያቃጥለን ድርሻችንን መወጣት ግዴታችን ነው። ኀሊና ያለው የትኛውም ሰው እንዲህ ዓይነት የወንጀል ድርጊት ሲፈጸም ዝም ብሎ አይቶ እንዳላየ ከማለፍ ወንጀለኛን ለፍርድ ማቅረብ ያስፈልጋል። እንደ ማኅበረሰብ እንደ ምእመን ማውገዝ ብቻ ሳይሆን ለጥቃት የተሰናዱ ቦታዎችን በማጋለጥ ለሕግ አቤት ማለት ይገባል።

በአጠቃላይ በሰው ዘር ማንነት ላይ የተቃጣው ይህ ርኩሰት ውስጥ ውስጡን እንደ ሰደድ እሳት ሲቀጣጠል እግዚአብሔርን የሚፈራ እና የሚያፍር ምእመን ባለባት ቅድስት ሀገር ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ከመተኛት ግንዛቤያችንን በማስፋት ልጆቻችንን፣ አካባቢያችንና ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅ ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው። ዛሬ በጅምሩ መከላከል ካልቻልን ችግሩ ከገዘፈና ከአቅም በላይ ከሆነ በኋላ ማስቆም ይሳነናል። የምዕራቡ ዓለም ዓላማውና ግቡም የእግዚአብሔር ሀገር፣ የክርስትና ደሴት የምትባለዋን ኢትዮጵያን ከሃይማኖቷ አስወጥቶ፣ የማይገባ ምግባር አሠርቶና ከእግዚአብሔር አጣልቶ እንዳልነበረች ማድረግ ነውና ከወዲሁ የከፋ ተልእኮውን አስቀድመን ልንረዳውና ራሳችንን ልንጠብቅ ይገባል።

**መፍትሔው በየጎዳናው ይህን ያደረጉ ወንጀለኞችን በተባበረ ክንድ ማጋለጥ፤ ለፍርድ ማቅረብ ነው። ይህንን ማድረግ አለመቻል ከሚመጣው ትውልድ ከመወቀስ አያድነንም። ሳይቃጠል በቅጠል የምንልበት ጊዜ አልፏል አሁን እንደሰደደ እሳት ሳያቃጥለን ድርሻችንን መወጣት ግዴታችን ነው።**

✝ ✝ ✝

# “እመኚ እንጂ አትፍሪ”

## ኪነ ጥበብ

*በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን*

የጽጌ ወቅት አልፎ የበጋው ወራት ከተተካ ሰነባብቷል፤ በዘመነ ጽጌ ፈክተው የነበሩ  አበቦችና ልምላሜ የተላበሱት ዕፅዋት ጊዜ ገድቧቸው ደርቀዋል፣ በአበቦችና ነፋሻማ አየር ታጅቦ ውስጣዊ ስሜትን በሐሤት ይሞላ የነበረው ጊዜ አልፎ ደረቅ ነፋስና የፀሐዩ ግለት ነፍስን ያስጨንቃል፡፡ ዕለቱ ሐሙስ እኩለ ቀን ነው፤ ፀሐይዋ አናት ላይ ስታርፍ ከጥንካሬዋ የተነሣ እንደ መርፌ አናት ትበሳለች፡፡

ጽዮን ከማንም ጋር ላለመገናኘት ራሷን አግልላ ከተሸሸገች ሰንብታለች፡፡ ዛሬም ውኃ ለመቅዳት ወደ ወንዝ ከሚወርዱ አንዳንድ ልጃገረዶች በስተቀር ማንም በማይንቀሳቀስበት ሰዓት በእኩለ ቀን የፀሐይዋን ሙቀት ተቋቁማ እንሥራዋን በጀርባዋ አዝላ ውኃ ልትቀዳ ብቻዋን ወደ ወንዝ ወረደች፡፡ ነገር ግን መንገዱን ከጀመረች በኋላ ተጨናነቀች፡፡

ጽዮን በዲፕሎማ ተመርቃ ካደገችበት ከቢቸና ከተማ  በዐሥር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝ የገጠር ቀበሌ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባስተማሪነት ትሠራለች፡፡ በትዳር ለመወሰን ካላት ጉጉት የተነሣ ጥያቄያቸውን ያለምንም ማንገራገር ብትቀበልም በየተራ የቀረቧት ሦስት ወንዶች ከቀረቧት በኋላ ከድተዋታል፡፡ ሦስቱም እሺ እስክትላቸው ድረስ ለእውነተኛና ዘላቂ ትዳር እንጂ ለጊዜያዊ ፍላጎት እንደማይፈልጓት ይነግሯታል፡፡ ይሁን እንጂ እሺ እንዳለቻቸውና  የትዳር ጥያቄያቸውን እንደተቀበለቻቸው ሲረዱ ለጾታዊ ግንኙነት ይጠይቋታል፡፡ እርሷ ደግሞ በሰንበት ትምህርት ቤት በተማረችው መሠረት ከትዳር በፊት ግንኙነት ኃጢአት እንደሆነ ተረድታለችና እንቢ ትላቸዋለች፡፡ በዚህ ምክንያት ከሦስቱም ሳትስማማ ቀርታ ተለያይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከሦስቱም ጋር አብራ ትታይ ስለነበር በማኅበረ ሰቡ ዘንድ እንደዘሙተኛ እየተቆጠረች መገለል ደርሶባታል፡፡ ራሷን መደበቅ የፈለገችውም በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ ውኃ መቅዳት ስታስብም ቀትር ላይ መሄድን የወሰነችውም ከሰው ዐይን ለመራቅ በወሰነችው ውሳኔ ነበር፡፡

ጽዮን ቀትር ላይ ወደ ወንዝ ስትወርድ “በእንዲህ ያለ ሰዓት ወጥቼ ጎረምሳ መጥቶ ቢደፍረኝስ?” እያለች ታወጣ ታወርድ ጀመር፡፡ በሌላ በኩል የፀሐይዋ ጥንካሬ ነጭ ላብ እያስወጣ ቁና ቁና ያስተነፍሳል፤ ልብስ ሁሉ አውልቃችሁ ራቁታችሁን ሂዱ ሂዱ ያሰኛልና ደረቷ አካባቢ ያለውን የቀሚሷን ክፍል በቀኝ እጇ ይዛ ታርገበግባለች፡፡

በዚህ ሰዓት ወንዝ ሲወርዱ ወረፋ የለም፤  ሰው አያይም፤ ሹልክ ብሎ ለመሄድና እንደ ልብ ሳይጋፉ ቀድቶ ለመምጣት የተሻለ ጊዜ ነው፡፡  ምንም እንኳን በዚህ ሰዓት የሚያስፈሩ ነገሮች ቢኖሩም ልጃገረዶች ግን እንዲህ ያለውን ሰዓት ይመርጡታል፡፡ ብቻቸውን እያንጎራጎሩ፣ የልብ ወዳጃቸውን በእንጉርጉሯቸው እያሞጋገሱ፣ እያሰላሰሉ በአካል አብሯቸው ባይኖርም በመንፈስ ከእርሱ ጋር እየተወያዩና፣ የልብ የልባቸውን እያወሩ በልዩ ተመስጦ ውስጥ ሆነው ውኃቸውን ቀድተው ይመለሳሉ፡፡ በመሆኑም ይህን ሰዓት እጅግ ይወዱታል፡፡

ጽዮን ግን እንደ ልጃገረዶች በእንደዚህ ያለ ሐሳብ ለመመሰጥ ሳይሆን ባሳለፈቻቸው የተደራረቡ የሕይወት ውጣ ውረዶች ውስጧ ተሰብሮ ከማንም መገናኘት አትፈልግም፤  በራሷ ዓለም ተንቀሳቅሳ መመለስ ትፈልጋለች፤ ባህሉን፣ ሥርዓቱን፣ የአካባቢውን ማኅበረ ሰብእ ሽሙጥና ምጸት መቋቋም ተስኗታል፡፡ ስለዚህ ሰው በማይበዛበትና ውኃ ለመቅዳት ወረፋ በሌለበት ሰዓት ሄዳ እንሥራዋን ሞልታ መመለስ ትፈልጋለች፡፡ በዚህ ልማድ ነበር እኩለ ቀን ላይ ውኃ ለመቅዳት ወደ ወንዝ የወረደችው፡፡

በያዘችው መጥለቂያ ከምንጩ እየቀዳች ወደ እንስራዋ ስትገለብጥ ድንገት አንድ ጎልማሳ ከሩቅ አስተዋለች፤ ጨነቃት፤ ሮጣ ማምለጥ አትችልም፤ ልሞክር ብትልም መንገዱ አንድ ብቻ ነው፤ ያውም እርሱ የቆመበት ብቻ፡፡ ከእርሱ በተቃራኒ ልሂድ ብትል ገደል ስለሆነ የሚታሰብም የሚሞከርም አይደለም፡፡ ታግላ ማሸነፍ አትችልም፤ እጅግ ተጨነቀች፤ በተመሰቃቀለና በተረባበሸ የሐሳብ ውጣ ውረድ ውስጥ ሆና ሳለች ይባስ ብሎ ጎልማሳው ወደ እርሷ እየቀረበ መጣ፡፡ ሰውነቷ ከወንዙ ዳር በቅላ ነፋስ እንደሚያርገበግባት ቂጠማ ተንቀጠቀጠ፡፡ ምርጫ ስላልነበራት የሚሆነውን ትጠባበቅ ጀመር፡፡

በአግባቡ ሰላምታ ሳይሰጣት "ውኃ አጠጪኝ?" ሲል ጠየቃት፡፡

ልትነፍገው ባትፈልግም ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠ መፍራቷ አሳበቀባት፡፡ ፍርሃቷን ለመቋቋም ጥረት እያደረገች በያዘችው የቅል ዋርማ ውኃ ቀድታ ልትሰጠው ስትል ከመፍራቷ የተነሣ የውኃ መቅጃው ከእጇ አፈተለከና ወደቀ፡፡ የውኃ መቅጃው የወደቀው ድንጋይ ላይ ስለነበር ከመሰበር አልታደገችውም፡፡ ይህን ሁሉ የምታሰላስልበት አቅምና መረጋጋት ስላልነበራት በያዘው በትር የመታት፣ የውኃ መቅጃዋንም ከድንጋይ ላይ ጥሎ የሰበረው መሰላት፣ እጅግ ስለደነገጠችም ድንጋዩ ላይ ወደቀች፡፡

በእርሷ ልቡና ውስጥ ያለው ስሜት እርሱ ውስጥ ባለመኖሩና እርሷ አስባው ለነበረው መጥፎ ድርጊት የተዘጋጀ ባለመሆኑ ከወደቀችበት እቅፍ አድርጎ አነሣትና

"አይዞሽ አትደንግጪ ለምን ትፈሪያለሽ? ደግሞስ ምንም ሳትባይ ለምን እንዲህ ትጨነቂያለሽ?" አላትና እርሷን አረጋግቶ የውኃ መቅጃው ጨርሶ ባለመሰባበሩ በሰባራውም ቢሆን ውኃውን ቀዳላትና አሸከማት፡፡

ከነበረባት ድንጋጤ ስትመለስ በስርቆሽ ዐይን ቀና እያለች ማስተዋል ጀመረች፡፡ መልከ መልካም ነው፣ አነጋገሩም ለስለስ ያለ ነው፡፡ "ለምን ፈራሁትና እንዲህ ተረበሽኩ" እያለች ራሷን ትወቅስ ጀመረች፡፡

እንስራዋን እንደተሸከመች ጉዟቸውን ቀጠሉ ቀስ እያለ "ስምሽ ማን ነው?" ብሎ ጠየቃት፡፡

"ጽዮን" አለችው፡፡

"መልካም ስም አለሽ" አላት፡፡

"በግብር የማይገለጽ ስም ምን ያደርግልኛል?" አለችው ፍርሃቷ በአግባቡ ከእርሷ ላይ ሳይወገድ፡፡

"ምን ማለት ነው?" ሲል እርሱም ጥያቄውን አስከተለ፡፡

"ገና ሕፃን እያለሁ ሰንበት ትምህርት ቤት ስንማር የኔታ መርሐ ጽድቅ 'ጽዮን ማለት ጸወነ ሥጋ ጸወነ ነፍስ ማለት ነው' ብለው አስተምረውን ነበር፡፡ እኔ ግን የኃጢአት፣ የዝሙት፣ የክፉ ሁሉ ነገር መጠጊያ እንጂ ስሜ እንደሚያመለክተው አይደለሁምና ስለዚህ ነው" አለች ሳታስበው ከውስጧ ያልጠበቀችው ኃይል እየገፋት ተናገረች፡፡

ጽዮን ቀጠለችና "እኔኮ የተጠላሁ፣ የተናቅሁ፣ ማኅበረ ሰቡ ያገለለኝ፤ ለጌታዬ ያልታመንሁ፣ ዝሙተኛ ነኝ እንጂ እንደ ስሜ መልካም ግብር የለኝም" አለች ተስፋ በቆረጠ ድምፀት፡፡

ጎልማሳውም በተራው "አየሽ ጽዮን፤ የሰው ልጅ መልካሙንም መጥፎውንም ሕይወት ያሳልፋል፡፡ አንቺ ደግሞ መንፈሳዊ ትምህርትም ተምረሻል፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፈ ምሳሌ 'ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል፣ ሰባት ጊዜ ይነሣል' (ምሳ.፳፬፥፲፮) ብሏል፡፡ ስለዚህ መውደቅ መነሣት ያለ ነው፡፡ ግን እንደወደቁ መቅረት ነው አደጋውና ተስፋ ሳትቆርጪ አሁንም ንስሓ ገብተሽ ተገቢውን ሕይወት መኖር አለብሽ" ደግሞስ መጽሐፍ "እመን እንጂ አትፍራ " ይል የለ (ማር ፭፥፴፮) እና አንቺም "እመኚ እንጂ አትፍሪ" አላት፡፡

ጽዮን ፈራ ተባም እያለች ያልጠበቀችውን መንፈሳዊ ምክር እያዳመጠች ሳለ ከአጠገቧ እየራቀ፣ እየራቀ፣ እየራቀ፣ ሄደ፡፡ በዐይኗ ብትከተለውም ልትደርስበት አልቻለችም፡፡ በመጨረሻም ከእይታዋ ተሠወረ፡፡ ድንጋጤዋ በትክክል አለቀቃትም፤ በሁለት መንታ ሐሳብ ተወጠረች አንደኛው ምትሐት መሰላት፣ "ቀትር ላይ ክፉ መንፈስ ከወንዝ ዳር ይገኛል" የሚለውን አነጋገር ማሰላሰል ጀመረች፡፡ ሰውነቷ መልሶ ተንቀጠቀጠባት፡፡ ክፉውን ሁሉ አሰበች፣ "በሰው ተመስሎ ሊያስተኝ ነበርን? ለነገሩማ ከዚህ በላይ ምን ሊያደርገኝ ኑሯል? ከወንዙ ላይ ጣለኝ እኮ" እያለች ከወንዝ ላይ የሆነውን ክሥተት እየመላለሰች ማስታወስ ጀመረች፡፡ ነገር ግን የተፈጠረውን ክስተት በደንብ ማስታወስ አቃታት፡፡

"ለመሆኑ ማን ነው እርሱ በእንዲህ ያለው ሰዓት ውኃ አጠጪኝ ያለኝ? እርሱ ማን ነው? ብወድቅ ያነሣኝ፣ ብደነግጥ ያረጋጋኝ፣ እንስራዬን የሞላልኝ፣ አንሥቶስ ያሸከመኝ እርሱ ማን ነው? ምን ዓይነትስ ቸር ቢሆን ነው? እኔ እንዲህ ስፈራው እርሱ ፍርሃቴን ያራቀልኝ እርሱ ማን ነው?" እያለች ውስጧን ጥያቄ በጥያቄ አጨናነቀችው፡፡

አንድ ነገር ግን መገመት ቻለች፡፡ በልጅነቷ ከሰንበት ትምህርት ቤት ስትማር የኔታ መርሐ ጽድቅ ያስተምሯቸው የነበረውን ታሪክ አስታወሰች፡፡ የእነ ርብቃን፣ የእነ ሲፓራን ታሪክ አስታወሰች፡፡ "ምን አልባት እግዚአብሔር ኃዘኔን አይቶና ተመልክቶ አጋር ሊሰጠኝ ይሆን" እያለች በመንታ ልብ ተጨናንቃ መልካሙንም፣ ክፉውንም እያፈራረቀች ታወጣ ታወርድ ጀመር፡፡

የኔታ መርሐ ጽድቅ በእነማይ ወረዳ ከቢቸና ከተማ ወጣ ብሎ ከሚገኘውና በተለምዶ አሮጌው ጊዮርጊስ እየተባለ ከሚጠራው ጥንታዊ ደብር የመጽሐፍና የቅኔ መምህር ናቸው። ደብሩ ጥንታዊና በርካታ ሊቃውንት የፈለቁበት ቢሆንም ስብከተ ወንጌሉን ለምእመናን ከማዳረስ አንጻር ግን ብዙም ያልተሠራበት ቦታ ነው።

"ቃለ ወንጌልን ለምእመናን ለማድረስ የሰንበት ትምህርት ቤት መስፋፋት አለበት" ብለው ያምናሉ።

በዚህም ምክንያት ቅዳሜና እሑድ ቊጥራቸው አናሳ ቢሆንም የሚመጡ አንዳንድ ሕፃናትንና የእርሳቸውንም የመጽሐፍ ተማሪዎችን እየሰበሰቡ ያስተምራሉ። ራሳቸው መዝሙር ያስጠናሉ፤ አንዳንዴ ተማሪዎቻቸውን መርሐ ግብር እንዲመሩ እያደረጉ በዕድሜያቸውም ሆነ በትምህርታቸው ያልበሰሉ ሕፃናትንም የሚያካትት ትምህርት ያስተምራሉ። ተማሪዎቻቸውም ከትርጓሜው በተጨማሪ የስብከት ዘዴውን እንዲለማመዱት የስብከት ተራ እየሰጡ እንዲያስተምሩ ያደርጋሉ። ጽዮን በሕይወት ዘመኗ የመጣባትን ፈተና ሁሉ በጽናት እንድታልፍ የረዳት ይህ የየኔታ መርሐ ጽድቅ ትምህርት ነበር።

ከምንም በላይ ግን አንድ ቀን የኔታ መርሐ ጽድቅ ስለ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ የተናገሩትን አንድ ታሪክ አስታወሰች። "ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ልጃገረድ ቀትር ላይ ብቻዋን ወደ አንድ ቦታ ስትሄድ አንድ ጎረምሳ አገኛትና አስገድዶ ሊደፍራት ሞከረ። እርሷም እንዲተዋት ብትማፀነው "እንቢ" አላት። በዚህ ጊዜ 'እባክህ ሰማዕቱ፣ ፈጥኖ ደራሹ ድረስልኝ' ብላ ስትለምነው በነጭ ፈረስ ተጭኖ ከየት መጣ ሳይባል ደረሰላትና ሊደፍራት ከነበረው ጎረምሳ ታደጋት። ስለዚህ እናንተም በጨነቃችሁ ጊዜ ሰማዕቱን አምናችሁ ጥሩት ፈጥኖ ደራሽ ነውና ይደርስላችኋል።" ብለው አስተምረዋቸው ነበር።

ጽዮን የየኔታ መርሐ ጽድቅን ትምህርት ከሰማችበት ዕለት ጀምሮ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ያላት መንፈሳዊ ፍቅር ጨመረ፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ ስም በልቧ ታተመ፣ በአንደበቷም ከመመስከር አልተቆጠበችም። በወር በወርም ጸበል ጸዲቅ እያዘጋጀች ትዘክራለች፤ ገድሉን በየወሩ ታነባለች።

ጽዮን ዛሬ የሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ ወርኃዊ የመታሰቢያ በዓል እንደሆነ ረስታለች። ሥራም በዝቶባት ስለነበር ያስለመደችውን ጸሎት አላደረገችም፤ ለዝክሩ የሚሆነውንም ጸበል ጸዲቅ አላዘጋጀችም። ይሁን እንጂ እንዲህ ያለ ሁኔታ ቢፈጠርም ምክንያቱ ትዝ አላላትም። የሆነውን ነገር ብቻ ግራ በተጋባ መንፈስ እያሰላሰለች ጉዞዋን ቀጥላለች።

ብቻዋን እያወራች አንዳንዴ ከሰው ጋር ያለች ሁሉ እየመሰላት ድምፅዋንም ጎላ አድርጋ እየተናገረች ቤቷ ደረሰች። እንስራዋን አውርዳ ካስቀመጠች በኋላ የጸሎት መጽሐፏን ያዘችና ወደ ጸሎት ቤቷ ገባች። የጸሎት ቤቷ በሥዕለ አድኅኖ ዙሪያዋን የተከበበች ለእርሷ ብቻ ለመስገድም እንድትመቻት አድርጋ ያዘጋጀቻት ናትና እጅግ ጠባብ ናት። ነገር ግን ዕለት ዕለት ሽቱ ስለምትረጫት በመዓዛዋ እጅግ ታውዳለች።

ጸሎት ቤቷ ስትገባ በልዩ ተመስጦ ውስጥ የመሆን ልምድ አላት። እንደ ልማዷም ቤቷን ዘጋችና የጸሎት መጽሐፏን ይዛ ድምፅዋን በተወሰነ መጠን ከፍ አድርጋ ዕንባዋን እንደ ጎርፍ እያወረደች የሰባቱን ቀን ውዳሴ ማርያም፣ አንቀጸ ብርሃን፣ ከሰማዕቱ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ገድል ውስጥ ሦስት ምዕራፍ፣ ከተአምሩ ሦስት ምዕራፍ አድርሳ ስትጨርስ አንድ ድምፅ ሰማች።

ቀና ስትል በአካል አይታይም ግን አሁንም ድምፁ ይሰማታል፣ ተረጋግታ የሚሆነውን ለመከታተል ወሰነች። "አይዞሽ ከክፉ ሁሉ የምጠብቅሽ እኔ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነኝ፤ አትፍሪ፣ ፈተናሽ ከባድና ውስብስብ ቢሆንም ከጎንሽ ነኝና አትፍሪ፣ ጸሎትሽን ወደ እግዚአብሔር አደርስልሻለሁ" አለና ድምፁ ተሠወራት።

ጽዮን የሆነውን ሁሉ ነገር በፍርሃትም፣ በጭንቀትም፣ በደስታም አሰበችው። "የማልጠቅም፣ እጅግ ታናሽ ስሆን እግዚአብሔር አሰበኝ፣ በሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ አማላጅነት ጎበኘኝ። ቅዱስ ጊዮርጊስ በዕለተ ቀኑ አሰበኝ" በማለት የደስታ ዕንባ እያነባች ረስታው የነበረውን ጸበል ጸዲቅ አዘጋጀችና ዝክሩን ዘከረች።

ይህ ሁሉ የሆነው "ዝክሬን እንድትዘክሪ፣ ገድሌን እንዳታስታጉዪ" የሚል መልእክት ለማስተላለፍ እንደሆነና ሁሌም ከጎኗ መሆኑን ለማስረዳት፣ መከራ ቢመጣባትም እንደማይለያት መሆኑን ተገነዘበች።

✠ ✠ ✠

# ጾመ ነቢያት በዓለም ማዕዘናት

## ከዓለም ማዕዘናት

ዲ/ን ኅሊና በለጠ

ከኅዳር 15 ጀምሮ የሚገባውን የነቢያት ጾምን መጾም፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚታወቅ ሥርዓት አይደለም፡፡ ሁሉም የኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን ጾም ይጾሙታል፡፡ ጾሙን የሚጾሙት ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ይህን ጾም ለመጾማቸው እንደ ዋና መሠረት የሚጠቅሱት ለጾሙ ፋሲካ የሆነውን የክርስቶስን ልደት በጾም ተዘጋጅቶ መቀበልን ነው፡፡

አብዛኞቹ ‹‹Nativity Fast›› ይሉታል፤ ‹‹ጾመ ልደት›› እንደ ማለት ነው፡፡ የቅዱስ ፊሊጶስ በዓል ከተከበረ በኋላ በመግባቱም ‹‹ጾመ ፊሊጶስ›› ተብሎ መጠራቱም የተለመደ ነው፡፡ በተለያየ አጠራር ብንጠራውም፡ ነቢያት የጌታችንን መውረዱንና መወለዱን ተስፋ በማድረግ አስቀድመው የጾሙት ጾም በመሆኑ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ስያሜው ‹‹ጾመ ነቢያት›› መባሉ የሚታወቅ እውነታ ነው፡፡

የባይዛንታይን አብያተ ክርስቲያናት ከኅዳር ፮ (Nov. 15) እስከ ታኅሣሥ ፲፭ (Dec. 24) በመጾም ልደተ እግዚእን በታኅሣሥ ፲፮ (Dec. 25) ያከብራሉ፡፡ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትን ጨምሮ አንዳንዶቹ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን ጾሙን ኅዳር ፲፱ (Nov. 28) ይጀምራሉ፡፡ የኅዳር ፲፱ ስንክሳርም ‹‹ወበዛቲ ዕለት ኮነ ጥንተ ጾመ ስብከተ ጌና ዘሮም ወአፍርንጊ ወሶርያ ወአርማንያ ዘእንበለ ግብጽ ወኢትዮጵያ ወኖባ - በዚችም ዕለት የሮም፣ የአፍርንጊ፣ የሶርያ፣ የአርማንያ ክርስቲያን ከግብጽ፣ ከኢትዮጵያ፣ ከኖባ በቀር የስብከተ ጌና ጾምን የሚጀምሩበት ነው›› ብሎ የተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት ጾሙን በኅዳር ፲፱ የሚጀምሩ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ አስቀድመን በጽሑፉ መጀመሪያ እንደ ገለጽነው ይህን የተመለከተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጾሙ በኅዳር ፲፭ እንዲጀመር ያዛል፡፡

ጾሙን የሚጾሙት ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ጸሎት፣ ንስሐና ምጽዋት አብረው በስፋት እንዲተገበሩ ያዛሉ፡፡ እንዲህ ከሆነም የልደተ ክርስቶስን ሱታፌና በረከት ለማግኘት ይበልጥ መዘጋጀት እንደሚቻል ይሰብካሉ፡፡ ከማንኛውም ሥጋ፣ ከወተት፣ ከዓሣ፣ ከቅባትና ከእነዚህ ውጤቶች ሁሉ መጾም እንደሚገባ ሁሉም ቢመክሩም፤ አንዳንዶቹ ወይን መጠጣትንም ከሰንበታት በስተቀር አይፈቅዱም፡፡ ዓሣና ዘይቶችን/ቅባቶችን በሰንበታት የሚፈቅዱም አሉ፡፡ ይህን በመሰለው ነገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትኅርምታዊ ምሳሌነት ለሁሉም ጎልቶ መነገር የሚችል ነው፡፡ የሚከለከሉት ነገሮች ሁሉ ሙሉ ጾሙ እስኪፈጸም የሚከለከሉ ናቸውና፡፡ አንዳንዶቹ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የወይን መጠጥን መከልከላቸው ግን የእነርሱም የትኅርምት ሥርዓት ቀላል እንዳልሆነ የሚያስተምር ነው፡፡

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በሰንበት ብቻ ሳይሆን፡ በጾሙ ውስጥ በሚያከብሯቸው በተወሰኑ በዓላትም ዓሣን፣ ወይንንና ዘይትን/ቅባትን ይፈቅዳሉ፡፡ እነዚህ የሚያከብሯቸው በዓላትም የወንጌላዊው ማቴዎስ ኅዳር ፯ (Nov. 16)፣ የሐዋርያው እንድርያስ ኅዳር ፳፩ (Nov. 30)፣ የሰማዕቷ ቅድስት ባርባራ ኅዳር ፳፭ (Dec. 4)፣ የገባሬ መንክራት ኒቆላዎስ ኅዳር ፳፯ (Dec. 6)፣ የአግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ ታኅሣሥ ፲፩ (Dec. 20) እና የሌሎች የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ‹‹ቅዱሳን›› ናቸው፡፡ (የተጠቀሱት የቅዱሳኑ የመታሰቢያ ዕለታት በኦሪየንታል ኦርቶዶክስና በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ቅዱሳኑ የሚታሰቡባቸው ናቸው፡፡ የግዴታ እኛ ቅዱሳኑን ከምናስብባቸው ቀናት ጋር አንድ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡) በአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በማዕርጋተ አጽዋም የጾመ ነቢያት ደረጃ ከዐቢይ ጾምና ከጾመ ፍልሠታ ቀጥሎ የሚገኝ ነው፡፡ ትኅርምቱም በዚያው ልክ ነው፡፡

የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ የስምዖን ጫማ ሰፊውን ታሪክ በማሰብ በጾሙ ላይ ሦስት ቀናትን ጨምራ ትጾማለች፡፡ ይህን የነቢያት ጾም በሌላ አጠራር ‹‹ጾመ ምጽአት (Advent Fast)›› ብለው የሚጠሩና የክርስቶስን የመጀመሪያ ‹‹ምጽአት›› የሚያስቡም ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል የአርመን ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ጾሙን በኅዳር ፲ (Nov. 19) ‹‹ጾመ ምጽአት›› ብላ ትጀምርና ታኅሣሥ ፳፰ (Jan. 6) የክርስቶስን ልደት ከማክበሯ በፊት ያለውን አንድ ሳምንት ‹‹ጾመ ልደት (Nativity Fast)›› ብላ ትጾማለች፡፡ (ምንጭ፡- www.oca.org, www.goarch.org, www.orthodoxwiki.org, www.stjohnsarmenianchurch.org)፡፡

ጥንታዊ መሠረት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ይህን ጾም መጾማቸው፡ ጾሙ ሐዋርያዊ መሠረት ያለው መሆኑን የሚመሰክር ነው፡፡ ይህም ከአምስት መቶ ዓመታት የዘለለ ታሪክ ለሌላቸውና ጾሙን ለማይጾሙት እንደ ፕሮቴስታንት ላሉት ቤተ እምነቶች ትምህርት መሆን የሚችል ነው፡፡

# ቤተ ክርስቲያን ለአእምሮ ሕመምተኞች ያላት አስተዋጽኦ



በዶ/ር እንግዳ ግርማ

## ፩. መግቢያ

የአእምሮ ጤንነት ችግር የአስተሳሰብ፣ የስሜት፣ የጠባይ እንዲሁም ሌሎች የአእምሮ ተግባራት መዛባት የሚያመጡት የጤና እክል ነው። ይህም በአንጻሩ ቀላልና ጊዜያዊ ከምንላቸው የውጥረት ስሜቶች እስከ ከባድ የአእምሮ መቃወስ የሚያካትት ነው። ምንም እንኳን ከፍተኛ የአእምሮ ሕመም ደረጃ ባይደርሱም ሌሎች የውጥረት፣ የጭንቀት፣ የእንቅልፍ ማጣት ወይም የጠባይ መቀየሮችም በጊዜያዊነት ወይም ከፍ ባለ መጠን በተደጋጋሚ ይከሠታሉ።

የአእምሮ ችግር መንሥኤዎች ብዙና የተለያዩ ናቸው። ሥነ ሕይወታዊ (Biological)፣ ስነ ልቡናዊ (Psychological)፣ ማኅበራዊ (Social) መንስኤዎች ብሎ መክፈል የተለመደና እስካሁን ተቀባይነት ያለው የአስተሳሰብ ማቀፍ ነው። ማኅበራዊ (social) መንሥኤ በሚለው ውስጥ ባህላዊ (cultural) እና መንፈሳዊ (Spiritual/Religious) ሁኔታዎችም ይካተታሉ።

የአእምሮ ሕመም ሲባል ራሱን የጣለ፣ የተዳደፈ፣ ቆሻሻ የሚለቅም፣ አደገኛ ሰው ማሰብ የተለመደ ነው። በርግጥ እጅግ በጣም ጥቂቱ የአእምሮ ሕሙማን ብቻ እንዲያ ያለውን የአእምሮ መቃወስ ምልክቶች ያሳያሉ። የሚበዙት ሕመሞች ምክንያት አልባ ጭንቀት፣ ድባቴ፣ እንቅልፍ ማጣት ወይም ከአእምሮ ዕድገት ጋር የተገናኙ ችግሮች ናቸው። በዐይን አይቶ ለመለየትም አይቻልም። ሁሉም ሊባሉ በሚችል ደረጃ ዘመናዊ የንግግር ወይም የመድኀኒት ሕክምና ያላቸው ቢሆንም አብዛኛው የማኅበረሰባችን ክፍል ወደ ጤና ተደራሽ አይደለም። በሀገራችን ኢትዮጵያ ከፍተኛ የአእምሮ ሕመም ካላቸው ሰዎች መካከል ከመቶ ውስጥ ሰማንያ ዘጠኝ የሚሆኑት ህክምና አያገኙም። (ምንጭ) በቂ ህክምና ማግኘት ባለመቻላቸው የአእምሮ ሕሙማን በጣም ብዙ የሕይወታቸውን ዘመናት በመታሰር፣ ተስፋ በመቁረጥና በመደብደብ እንዲሁም በብቸኝነት ያለሥራ ያሳልፏቸዋል። የቤተሰብ ኑሮና ብዙ የሀገር ንዋይ እንዲሁ እንደባከነ ያልፋል።

## ፪. ቤተ ክርስቲያን ለአእምሮ ጤና

### ሀ. የአእምሮ ጤንነትን በመጠበቅ

ስላለን የተደከመበት የማይመስለን የአእምሮ ደኅንነታችንን አስቀድመን እንደተመለከትነው ከሥነ ሕይወታዊ መሠረቶች ባሻገር ያሉ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ውቅሮች በብዙ ድካም የተዋቀሩ ናቸው። ለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ድርሻ ተወጥታለች። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ ምእመን በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ፣ በምግባር ላይ ትሩፋት አምላኩን ለመምሰል በጎ ዘር የተዘራበት እንደሆነ በማስተማር ወደ በጎነት፣ መልካምነት፣ ቅንነት፣ ቅድስና፣ ንጽሕና ወዘተ. እንዲያድጉ ከልጅነት ጀምሮ ዕለት ዕለት ታስተምራች። ይህም ልጆቿ በጎ ኅሊና እና አዎንታዊ አስተሳሰብ (Positive thinking) እንዲኖራቸው ትምክህታቸው በሆነ ከሃሌ ኵሉ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ እንደሚችሉ የሚያምኑ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። እንዲህ ያለው አዎንታዊ አስተሳሰብና ማድረግ እችላለሁ የሚለው እምነት ምእመናንን ከጭንቀት፣ ከውጥረትና ተስፋ ከመቁረጥ በብዙ መልኩ ይጠብቃል። ከዚህም ባሻገር ኦርቶዶክሳውያን በየማኅበረሰባቸው በእድር እንዲሳተፉ፣ ራሳቸውን ሳይኮፍሱም ሳያሳንሱም ከሌሎች ጋር በሰላም እንዲኖሩ ሆነዋል።

በጎ አስተሳሰብና አምላኩን መጠጊያ ያደረገ “ሁሉን ማድረግ እችላለሁ” የሚለው እምነት ምእመናን ድሃ ቢሆኑ ሀብታም፣ ሊቀ ቢሆኑ ደቀቅ፣ ከሰሜን ቢሆኑ ከደቡብ፣ ከምሥራቅ ቢሆኑ ከምዕራብ ያለምንም ፍርሃትና የበታችነት ስሜት በእኩል መንፈስ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረን ሁሉ በማክበር በኅብረት እንዲያመሰግኑ፣ በአንድ አንድ ሰንበቴ ማኅበር አንድ ጽዋ እንዲጠቱ አድርጓል። እንዲህ ያለው ኅብረት በደስታና በኀዘን፣ በድሎትና በእጦት በማንኛውም የኑሮ ውጣ ውረድ ሥነ-ልቡናዊና ማኅበራዊ ድጋፍ የሚገኝበት ሁነኛ መንገድ በመሆን ያገለግላል።

መናር ስለቸኝ፣ ራሴን አጥፍቼ አርፋለሁ፣ ለምን እኖራለሁ እና የመሳሰሉት የሚያስቆዝሙ ሐሳቦች በተለያዩ የአእምሮ ሕመሞች ምክንያት ወይም የሕይወትን ትርጉም በማጣት ይመጣሉ። ከዚህ በተጨማሪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰውን ልጅ የምድር ኑሮ ትርጉም ማስተማሯ ምእመናን የሕይወት ትርጉም እንዳይጠፋቸውና በቀቢጸ ተስፋ እንዳይኖሩ ትልቅ መሠረት ሆኗል።

ከዚህም በላይ የኦርቶዶክሳውያን ልጆች የሰብእና አወቃቀር ዋነኛ ማንጸሪያ ፈጣሪያቸውና አምላካቸው ስለሆነ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴዎቻቸው "ይህን እግዚአብሔር ይወደዋል" በማለት ራሳቸውን እንዲጠይቁ እና ከክፋትና ጥፋት እንዲጠበቁ ሆነዋል። ሌሎች ላይ ቅያሜ ከመፍጠር፣ ጫና ከማድረግ፣ ከመጉዳት ተጠብቀዋል።

ሌላው ትልቁ የቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ምሥጢረ ንስሓ ነው። ምእመናን ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው ባሻገር ስለጭንቀታቸው፣ የዕለት ተዕለት ተግዳሮቶቻቸው፣ ማኅበራዊ ውጣ ውረዶቻቸው፣ የቤተሰብ ሕይወታቸውን ከመምህረ ንስሓቸው ጋር ይወያያሉ። እነዚህን ሁሉ የሚያዳምጥ ጆሮ ማግኘቱ በራሱ ትልቅ ዕረፍት የሚሰጥ ነው። ለየተግዳሮቶቻቸው ጊዜ ሰጥቶ መመካከርና የመፍትሔ ሐሳብ ማምጣት መቻል ደግሞ ትልቅ መንፈሳዊ ሕክምና ነው። ጭንቀት፣ ውጥረትና ሌሎች የአእምሮ ጫናዎችና ሕመሞች በዚህ መልክ ሲታከሙ ኖረዋል።

ሰዎች ኀዘን በደረሰባቸው ጊዜ የሚጽናኑባት እጅግ ጠቃሚ ሥርዓት ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት። ኀዘን ጊዜ የሚወስድ እንደመሆኑ በየደረጃውና በየጊዜው በካህናትና በምእመናን የማጽናናት ሥራ ትሠራለች። በዚህም ሰዎች ከኀዘን ጋር የተገናኘ የአእምሮ ጭንቀትም ሆነ ሌላ ሕመም እንዳይከሠትባቸው ስትረዳ ቆይታች። ድንገተኛ አደጋ/ጥቃት የደረሰባቸውን በቃለ እግዚአብሔር ማጽናናት፣ የተቻለ ቁሳዊ ድጋፍ ማድረግ እና ምእመናን ላዘኑና ለተጎዱ እንዲደርሱ ማበረታታት የቤተ ክርስቲያን የዘመናት ተግባር እንደሆነ ይታወቃል። ሰዎች ከአሰቃቂ ክሥተት በኋላ ከፍተኛ የአእምሮ ውጥረት እንዳይከሠትባቸው እንዲህ ያለው ማኅበራዊና መንፈሳዊ አገልግሎት ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው። በሰሞኑም ደጋግመን እያየን ያለነው ይህንኑ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን የዘመናት ገጽታ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ለአእምሮ ደኅንነት የምታበረክተው አስተዋጽኦ በአደጋ፣ በሕመምና በጭንቀት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመልካሙም ጊዜ ጭምር ነው። እንዲህ ላለው የቤተ ክርስቲያን አበርክቶ ሰ/ት/ቤቶች ጥሩ ምስክሮች ይሆናሉ። የኦርቶዶክሳውያን ልጆች በሥነ ምግባር እንዲታነጹ፣ ሀገራቸውን እንዲወዱ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ለወላጆቻቸውን የሚታዘዙ እንዲሆኑ በሰ/ት/ቤት ተኮትኩተው ያድጋሉ። ወጣቶች ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ፣ ከሱስ ተጠብቀው፣ እርስ በእርስ እየተዋደዱ እንዲኖሩ በማድረግ ሰ/ት/ቤቶች የፈጠሩት ትልቅ የአዳጊዎችና ወጣቶች ኅብረት ብዙ ትውልድ የሚታደግ የአደባባይ ሀቅ ነው።

በመምህረ ንስሓ በኩል ከወላጆች፣ በሰንበት ት/ቤት በኩል ከአዳጊዎችና ወጣቶች፣ በስብከተ ወንጌል በኩል ከመላ ቤተሰቡ በመድረስ ሰላማዊ የክርስቲያን ቤተሰብ እንዲኖራቸው፣ ወላጆች ለልጆች ፍቅርና ክብካቤ እንዲሰጡ፣ ልጆች በሥነ ምግባር ታንጸው፣ ወላጆቻቸውን አክብረው እንዲያድጉ በማድረግ ወላጆቻችን ከጭንቀትና ከውጥረት፣ ልጆቻችን ከአስተዳደግ ጋር ተያይዘው ከሚመጡ ብዙ የአእምሮ ጤና እክሎች መታደግ፣ ወይም መቀነስ ሌላው የቤተ ክርስቲያን የሚታይ አስተዋጽኦ ነው።

በሥነ ልቡና ዓለም ብዙ ካጨቃጨቁ ጉዳዮች መካከል አንዱ ሃይማኖተኝነት (መንፈሳዊነት) ነው። በዘመናዊ የሥነ ልቡና እና የአእምሮ ህክምና ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ እየተጠኑ ካሉ ርእሰ ጉዳዮች መካከል አንዱ መንፈሳዊነት/ሃይማኖተኝነትና አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነት ያላቸው ውስብስብ ግንኙነት ነው። አሁን ባለው መረጃ መሠረት መንፈሳዊነት ለአማኞች ከፍተኛ የአእምሮ ሰላም ይሰጣል። ለአካላዊ ሕመም የመጋለጥ እድልን ይቀንሳል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆቿ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በርትተው እንዲኖሩ ማስተማር ዛሬ ሳይንስ ስላለ ሳይሆን በዘመኗ ሁሉ የአገልግሎቷ ማጠንጠኛ አድርጋ ስትፈጽመው የኖረችው ዋነኛ አገልግሎቷ ነው። መንፈሳዊነት ከሰማያዊ ጥቅሙ ሌላ እንደ ዳረጎት አእምሯቸውና አካላቸው የተረጋጋ ለሕመም ተጋላጭነታቸው የቀነሰ እንዲሆን ያደርጋል።

## ለ. በማከም/በፈውስ

ቤተ ክርስቲያን የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ ያሉ ምእመናን ዕረፍት

የሚያገኙባት ባለ መድኃኒት እንደሆነች እሙን ነው:: ከቀላል እስከ ከባድ የአእምሮ ሕመም ያለባቸውን ሰዎች እንደምሳሌ ብናይ በሥርዓተ ጸሎቱ፣ በስብከቱ፣ በመዝሙሩ የመንፈስ ዕረፍት፣ የአእምሮ መረጋጋት ያገኛሉ:: ይህንንም እንደ የቡድን ህክምና ልናየው እንችላለን:: ከዚህም በላይ በንስሐ አባቶች በኩል የየግል ጭንቀቶቻቸውን ምእመናኑ እንዲወያዩ እና እንዲፈቱ ታደርጋለች:: የቤተ ክርስቲያን ምክር ተስፋ በመቁረጥ፣ በከፍተኛ ኀዘን፣ በቤተሰብ አለመረጋጋት ውስጥ ለሚገኙም የጭንቀታቸው ማቃለያ የችግራቸው መፍቻ መንገድም ሆኖ ያገለግላል::

**ካህናት አባቶች ከተነሳሕያን ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት፣ በሚያናግሩበት ጊዜ ማድረግ ስላለባቸው ነገሮች፣ ስለሚወያዩባቸው ዋነኛ ፍሬ ሐሳቦች የሚያትት የሥልጠና መመሪያ ማዘጋጀት እና ማሠልጠን::**

በኢትዮጵያ ካሉ ከፍተኛ የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ሕሙማን የሚበዙት ወደ ጸበል ቦታዎች ይሄዳሉ:: ቁጥራቸው በዘመናዊ የህክምና ተቋማት ከሚገኙት በብዙ እጥፍ ይበልጣሉ:: ሁሉም ወደ ሀኪም ቤት ቢመጡ ያለው የአእምሮ ህክምና መሠረተ ልማት ከሚቋቋመው እጅግ የበዛ ይሆናል:: ስለዚህ የአእምሮ ሕሙማን ጸበልተኞችን አቅፋ በመያዝ ምግበ ነፍስ እየመገበች ታኖራቸዋለች:: የሱስ ሕመም ያለባቸው ወጣቶችን በቅጽሯ ቆይተው፣ መንፈሳቸውን አድሰውና አገግመው እንዲወጡ ትሠራለች:: ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰብ የሚጠቅሙ እንዲሆኑ ታዘጋጃቸዋለች:: እንዲህ ያለ ጉልህ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ከሕሙማኑ ባሻገር ወላጆችና ቤተ ሰቦችም ከፍተኛ ዕረፍትና የመንፈስ እድሳት እንዲያገኙ ያደርጋል:: ይህ ሁሉ የሚሆነው በሳይንስ ከምንረዳው በላይ ከሆነው የፈውስ አገልግሎቷ ባሻገር በቤተ ክርስቲያን እየተከናወነ ያለውን የሚመለከት ነው::

## ፫. ቤተ ክርስቲያን ለአእምሮ ጤና

ስንዱ እመቤት የሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን በኢትዮጵያ ለአእምሮ ጤና ያበረከተችው ተቀጥሮ የማያልቅ ነው:: መዋቅሯም ይህን ለማድረግ የተመቸ ነው:: ከዚህ የበለጠ ለማድረግ የተለየ አወቃቀር አይፈልግም:: ምእመናን ላይ መሥራትና ለሁሉም ዘርፍ ዘመኑን መዋጀት ይገባል::

### ሀ. ምእመናንን ማስተማር

ማንኛም ዓይነቱ ሕመም ልንታመም እንደምንችለው ሁሉ የአእምሮ ሕመም ሊያመን ይችላል:: የአእምሮ ጤና መቃወስ በተለየ መልኩ የደካማነት ወይም የኃጢአት ምልክት አይደለም:: ስለዚህ ምእመናን ማንኛውም አካላዊ ሕመምን እንደሚያዩት እንዲረዱት ማድረግ የሕሙማን መገለልና ሥቃይ ይቀንሳል::

ወደ ህክምና ቦታ ወይም ቤተ ክርስቲያን የመምጣት እድላቸውን ይጨምራል:: ይህን ውጤት ለማምጣት ስለሕመምና ደዌ በተነሣበት አጋጣሚ ሁሉ ስለ አእምሮ ሕመም ማስተማር አስፈላጊ ነው:: በቅዱስ መጽሐፍ በብዙ ሥፍራዎች የተጠቀሱትን የአእምሮ ሕሙማን የምሕረት ባለቤት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ሳይጸየፋቸው ፈውስን እንዳደረገላቸው እያነሡ ማስተማር ምእመናን ማግለልን እንዲጸየፉ ይረዳል::

ከዚህ በተጨማሪ ሁሉን ማዳን የሚችለው ክርስቶስ በልዩ

ልዩ መንገዶች እንደሚፈውስ፣ ዘመናዊው ሕክምናም የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ፣ ምእመናን እየተጠመቁ መድኃኒት መውሰድ እንደሚችሉ፤ መድኃኒት እየወሰዱ ባሉበት ጊዜም አስቀድመው መጠመቅና ከተጠመቁ በኋላ መድኃኒቱን መውሰድ እንደማይከለከሉ ማስገንዘብ ያስፈልጋል። የቤተ ክርስቲያን ልጆች ወይ በመድኃኒት አልያም በጸበል ከሚል ፉክክርና ድርቅና ወጥተው፤ እግዚአብሔር በልዩ ልዩ መንገድ እንደሚፈውስ ተረድተው እንዲጠቀሙ ማበረታታት ይገባል።

## ለ. ምሥጢረ ንስሓ

ንስሓ ለድኅነተ የተሰጠን የቸርነት በር ነው። እጅግ ብዙ ምእመናን በዚህ የምሥጢር በር እየገቡ ከአምላካቸው ጋር የተለየውን ኅብረት ይመልሳሉ። ለምእመናን የአእምሮ ደኅንነት ስላለው ፋይዳ ከላይ በአጭሩ ለመጥቀስ ሞክረናል።

ይህን ለምእመናን መንፈሳዊም ሆነ ምድራዊ ሕይወት ወሳኝ የሆነ ምሥጢር አሠራሩን ማዘመን ብዙ ክርስቲያኖችን የበለጠ ተጠቃሚ ማድረግ ነው። የምእመናንን የንስሓ ሕይወት የሚከታተል ክፍል ማቋቋም፣ ምእመናን በንስሓ ሕይወት እንዲጠቀሙ ማበረታታት ቀዳሚ ተግባራት ሊሆኑ ይችላሉ። ካህናት አባቶች ከተነሳሕያን ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት፣ በሚያናግሩበት ጊዜ ማድረግ ስላለባቸው ነገሮች፣ ስለሚወያዩባቸው ዋነኛ ፍሬ ሐሳቦች የሚያትት የሥልጠና መመሪያ ማዘጋጀት እና ማሠልጠን። ከመንፈሳዊው ጥበብ በተጨማሪ በዘመናዊው የንግግር ህክምና (Psychotherapy) በጥናት የተረጋገጡ መንገዶችን መጠቀም የሚችሉ ብዙ ካህናትን ማፍራት ያስፈልጋል። ብዙ በቀቢጸ ተስፋ ያሉ ወንድሞችና እኅቶችን የበለጠ ለመርዳት ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

## ሐ. የሱስ ማገገሚያ ሥርዓት መዘርጋት

ወጣቶች በየጸበል ቦታ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ምግብ እየተመገቡ "አምጣ አምጣ" የሚላቸውን የሱስ ስሜት ተቋቁመው ይቆያሉ። ሥርዓት ተደንግጎለት በሱስ ለተጎዱ ጸበልተኞች በተለየ መልኩ ድጋፍ የሚያደርግ ቢሆን ደግሞ እጅግ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል። በልዩ ልዩ ሱስ የተጠመዱ ወንድሞችና እኅቶችን መንፈስ የሚያንጽ፣ የተጠና እና በየደብሩ/ገዳሙ የተቀናጀ የስብከተ ወንጌል፣ የውይይት፣ የንግግር ሕክምና እና የመዝሙር ክፍሎች ያሉት ሥርዓተ ትምህርት መቅረጽ ውጤቱ የሚለካና በየጊዜው የሚሻሻል ኦርቶዶክሳዊ ወጣቶችን የመታደጊያ መንገድ እንዲሆን ይረዳል። እንዲህ ባለው መንገድ ታንጸው የወጡ ወጣቶች ከሱስ ከማገገማቸው በላይ ለቤተሰብ፣ ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ይሆናሉ።

## መ. የጸበል ቦታዎች

ክርስቲያኖች በየአድባራቱና በየገዳማቱ ተሰባስበው በመጠመቅ ድኅነተ ሥጋ ድኅነተ ነፍስ ለማግኘት ይለምናሉ፤ ይማልላሉ። ይሁንና ጥቂት በማይባሉ ጊዜያት ይህ የሚሆነው ካላስፈላጊ ሥቃይና እንግልት ጋር ነው። ጸበልተኞቹ የአእምሮ ሕሙማን ለግርፋት እና ለሰንሰለት እስራት ይዳረጋሉ። በአስጠማቂዎች እጅ ይደበደባሉ። ብዙዎች የጸበል ስፍራዎች በቂ የውኃና የንጽሕና መጠበቂያ ቦታዎች የሏቸውም። በአንዳንዶቹ ገዳማትና አድባራት ምእመናን ከመሀል ከተማ ባልተናነሰ የቤት ኪራይ ኑሯቸው ይናጋል። እነዚህን ችግሮች መቅረፍ የጸበል ቦታዎች ተቀዳሚ ሥራ መሆን አለበት። እግዚአብሔርን ብሎ ቤተ ክርስቲያን ተጠግቶ ያለ ሕመምተኛ ተጨማሪ ሕመምና እንግልት ሊደርስበት አይገባም።

ጸበልተኞች ከመጠመቅ፣ ከጸሎትና ከመንፈሳዊ አገልግሎት በተረፋቸው ጊዜ ቁጭ በሎ ከማውራት፣ ዝም በሎ ከመቆዘም ወይም ለክፉ ሐሳብ ማደሪያ ከመሆን እንደየአቅማቸው በሥራ እንዲያሳልፉ ማድረግ ለገዳማቱ ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይገባል። ለአብያተ ክርስቲያናቱ ከሚኖረው በጎ ትሩፋት ባሻገር ጸበልተኞች የመዳን ሂደታቸውን እንዲያፋጥኑ፣ ወደ መደበኛ ሕይወታቸው ሲመለሱ ለሚኖራቸው የሥራ ሕይወት ዝግጅት እንዲያደርጉ ያግዛል።

✞ ✞ ✞

# ቅጽል

## አቡጊዳ የግእዝ ትምህርት

በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

ውድ አንባብያን በባለፈው ዕትማችን ስለ ወገን አመልካች ቅጽልና ስለ አኃዝ ቅጽል ምንነት ተመልክተናል፡፡ የቤት ሥራ መስጠታችንም ይታወሳል፤ በአግባቡ እንደሠራችሁትም ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ለማረጋገጥ ያህል እንደሚከተለው መልሱን አስቀምጠናል፡፡

፩. በሚከተሉት ቃላት ምዕላድን በመጨመር በነጠላና በብዙ፣ በሴትና በወንድ ወገን አመልካች ቃላትን (ቅጽሎችን) መሥርቱ፡፡

| ተ.ቁ | ስም | ለነጠላ ወንድ | ለነጠላ ሴት | ለብዙ ወንድ | ለብዙ ሴት |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ገሊላ | ገሊላዊ | ገሊላዊት | ገሊላውያን | ገሊላውያት |
| ፪ | ቅድም | ቀዳማዊ/ ይ | ቀዳማዊት/ይት | ቀዳማውያን | ቀዳማውያት |
| ፫ | ሣልስ | ሣልሳዊ/ይ | ሣልሳዊት/ይት | ሣልሳውያን | ሣልሳውያት |
| ፬ | ሀገር | ሀገራዊ | ሀገራዊት | ሀገራውያን | ሀገራውያት |
| ፭ | ሐሳብ | ሐሳባዊ | ሐሳባዊት | ሐሳባውያን | ሐሳባውያት |

፪. ውድ አንባብያን የሚከተሉትን ቁጥሮች ለዕለታት ሲሆን እንዴት መጠቀም እንደምንችል በፊደል በመጠቀም (አኀዝ ቅጽሎችን) መሥርቱ፡፡

፲፮፣ ፲፯፣ ፲፰፣ ፲፱፣ ፳፣ ፳፩፣ ፳፪፣ ፳፫፣ ፳፬፣ ፳፭፣ ፳፮፣ ፳፯፣ ፳፰፣ ፳፱፣ ፴

፲፮= ዐሥሩ ወሰዱሱ፤ ፲፯- ዐሥሩ ወሰብዑ፤ ፲፰- ዐሥሩ ወሰሙኑ፤ ፲፱- ዐሥሩ ወተሥዑ፤ ፳- እስራ፤ ፳፩-እስራ ወአሚሩ፤ ፳፪-እስራ ወሰኑዩ፤ ፳፫-እስራ ወሠሉሱ፤ ፳፬-እስራ ወረብዑ፤ ፳፭-እስራ ወሐሙሱ፤ ፳፮-እስራ ወሰዱሱ፤ ፳፯-እስራ ወሰብዑ፤ ፳፰-እስራ ወሰሙኑ፤ ፳፱-እስራ ወተሥዑ፤ ፴-ሠላሳ፡፡

ውድ አንባብያን የቤት ሥራውን በዚህ መልኩ ሠርታችሁት ከሆነ ትክክል ናችሁ፡፡ በዚህ ዕትማችን ደግሞ ለዚህ ክፍል የመጨረሻ የሆነውን ግልጠ ዘ ቅጽልን እንመለከታለን፡፡

ግልጠ ዘ ቅጽል ፡- ይህ የቅጽል ዓይነት ግልጠ ዘ የተባለው "የ" ተብለው የሚፈቱትና፣ በግስ ላይ ተጨምረው ስምን እንዲገልጽ በግስ ላይ የሚቀጸሉት ወይም ግስን ቅጽል እንዲሆን የሚያደርጉት አገባቦች በግልጥ ስለሚታዩ ነው፡፡

ግልጠ ዘ ቅጽል የሚባሉት ዘ፣ እንተ እና እለ ናቸው፡፡ ባለፉት ዕትሞቻችን የቅጽል ዓይነቶችን ስንመለከት መምህር አስበ ድንግል ግእዝ ልሳነ ኢትዮጵያ በተሰኘ መጽሐፋቸው ገጽ ፳ ላይ የውስጠ ዘ ዓይነቶችን "ግልጠ ዘ እና ውስጠ ዘ" ብለው እንደሚከፍሏቸውና በውስጠ ዘ ቅጽል ምድብ ውስጥም የሚዘረዘሩትን ተመልክተናል፡፡ ግልጠ ዘ ቅጽሎች በሚለው ምድባቸው ደግሞ የሚዘረዝሯቸውም ከላይ የተገለጹትን ማለትም "ዘ" ን፣ "እንተ" ን እና "እለ" ን ነው፡፡

አለቃ ኪዳነ ወልድም መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ በተሰኘ መጽሐፋቸው (ገጽ ፹፬-፺፩) በመጀመሪያ ዘርና ነባር ብለው በሁለት ከከፈሏቸው በኋላ በእያንዳንዳቸው ደግሞ ሌሎች ንኡሳን ክፍሎች እንደሚዘረዝሩ ጠቁመናል፡፡ ነባር ቅጽሎች ብለው ከሚዘረዝሯቸው መካከል ግልጠ ዘ የሚባሉት ቅጽሎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ግልጠ ዘ የሚባሉት "ዘ" ፣ "እንተ" እና "እለ" እንደሆኑ ይዘረዝራሉ፡፡

መምህር ኀይለ ኢየሱስ መንግሥት የልሳነ ግእዝ መማሪያ ብለው ባዘጋጁት መጽሐፋቸው ግልጠ ዘን ግልጠ (የ) ብለው ይሰይሙትና ሲገልጹትም "ዝንቱ ዘመደ ቅጽል እንዘ ይወድቅ መልዕልተ ግስ ይከሥትዎ ለስም፡፡ (ስሞችን የሚገልጽ ማለት ነው፡፡) ብለው ያስረዱና በዝርዝር ሲያስቀምጧቸውም "ግልጠ (የ) ቅጽላት ዘይትበሀሉ "እንተ" ፣ "ዘ" ወ "እለ" ውእቶሙ፡፡" (ገጽ ፺፭) በማለት ይጠቅሷቸዋል፡፡

ከላይ መምህራኑ በገለጹት መሠረት ግልጠ ዘ የሚባሉት

"እንተ"፣ "ዘ" እና "እለ" ናቸው:: ግልጠ ዘ የተባሉበት ምክንያት አንድ ግስ ቅጽል እንዲሆን የሚያደርጉት እነዚህ አገባቦች ወይም ቃላት በአካል ግሱ ላይ ተጨምረው ስለሚታዩ ነው:: በአገልግሎት ደረጃ የተወሰነ ልዩነት ስላላቸው ልዩነታቸውን አንድ በአንድ እንመለከታለን::

"ዘ" ይህ ቅጽል ለአንድ ለብዙ ለሴት ለወንድ ይቀጸላል:: ወይም ይህ አገባብ የተጨመረበት ግስ ለአንድና ለብዙ፣ ለሴትና ለወንድ መቀጸል ይችላል:: ምሳሌ፡-

- ዘተንሥአ እሙታን አምላክ ውእቱ::
- ዘነሥአት ዕፍረተ ብእሲት ተመይጠት መንገለ ቤታ::
- ዘነበቡ ትንቢተ ነቢያት ውእቶሙ::
- ዘይቀድሓ ማየ አንስት ወረዳ መንገለ ቀላይ::

"እንተ" ይህ ቅጽል ከቊጥር አንጻር ለአንድ ብቻ ሲሆን ከጾታ አንጻር ግን ለሴትና ለወንድ ይቀጸላል:: ወይም ይህ አገባብ የተጨመረበት ግስ ለአንድ (ለነጠላ ቁጥር) ብቻ ሆኖ ለሴት ለወንድ መቀጸል ይችላል:: ምሳሌ፡-

- ዘ ውእቱ ሕፃን እንተ ያፈቅሮ አቡሁ::

-ዛቲ ይእቲ መርዓት እንተ ታፈቅር ብእሲሃ::

"እለ" ይህ ቅጽል ከቊጥር አንጻር ለብዙ ብቻ ሲሆን ከጾታ አንጻር ግን ለሴቶችም ለወንዶችም ይቀጸላል:: ወይም ይህ አገባብ የተጨመረበት ግስ ለብዙ ቁጥር ብቻ ሆኖ ለሴቶች ለወንዶች መቀጸል ይችላል:: ምሳሌ፡-

-ቡሩካን ውእቶሙ አበው እለ ሠርዑ ለነ ሥርዐተ::

-አንስት እለ ነሥኣ መኃትዊሆን ተሰብሓ በፈጣሪሆን::

ውድ አንባብያን ከላይ የቀረበው ትምህርት ግልጽ እንደሆነ ተስፋ እናደርጋለን:: ከላይ የቀረበውን ትምህርት መሠረት አድርጋችሁ ግልጠ ዘ ብለን በዘረዘርናቸው ቅጽሎች በእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ዐረፍተ ነገሮችን ሥሩባቸው::

"ዘ"

"እንተ"

"እለ"

✞ ✞ ✞

## ልቤን አስጎንብሰው

ካዘመመ አንገት ጀርባ

እንደ ዐለት ተገትሯል

ከተንበረከከ ጉልበት መሀል

የኩራት እርምጃን ይሻል

ላዩን በነጭ አሸብርቆ

በጥርሴ ፈገግታ አስውቦ

ውስጥ አካሌ ከሰል መስሏል

በጨለምተኝነት ተከቦ

በዓይኔ ምሕረትን ይጣራል

ይመስል ቅን የለበሰ

ክፋት እየሸረበ

ዓለም ኃጢአት እያሰሰ

የስሜት ምሪት ነውና

የአንገት ወደፊት ማዘመም

አምላክ ልቤን አጎንብሰው

ያን የማይታይ መዝገብ::

*በወርቅነሽ ቲፋ*